# ከጋምቤላ እስከ ሁመራ!

## ለሱዳን መሬት ከተሰጠ ይመጣል መከራ!

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው!
All rights reserved

መጀመሪያ ታተመ መጋቢት 2001 ዓ.ም
ሲያትል ዋሽንግተን
አሜሪካ

Copyright 2009 Amare Afelae Bishaw.
First edition March 2009
Printed in U.S.A

Published by Gugsa Magazine
P.O.BOX 492
Seattle WA 98111
U.S.A

የደራሲው መልዕክተ ማጥን ቁጥር
P.O.BOX 492
Seattle WA 98111
U.S.A

ከአማረ አፈለ ብሻው!
Amare Afelae Bishaw.

## ክፍል አንድ

### ማውጫ

ምዕራፍ 1 ምስናጋ እና መታሰቢያ ገጽ 2-4
ምዕራፍ 2 ፈር አስጨባጭ ገጽ 5-6
ምዕራፍ 3 በታሪካችን እንኩራ እንጅ አንፈር ገጽ 7-9
ምዕራፍ 4 ለአንባቢያን ከፀሐፊይ ገጽ 10-17

## ክፍል ሁለት

ምዕራፍ 1 የኢትዮጵያ ታሪክ ከፍጥረት እስከ ልደት ገጽ 18-21
ምዕራፍ 2 የኢትዮጵያ ታሪክ ከክርስቶስ ልደት እስከ እስልምና ሃይማኖት ምስረታ ገጽ 22-25
ምዕራፍ 3 ከእስልምና ምስረታ እስከ ንግሥት ዮዲት ገጽ 26-30
ምዕራፍ 4 ከንግሥት ዮዲት እስከ ዘመነ መሳፍንት ገጽ 37-40
ምዕራፍ 5 ከዘመነ መሳፍንት እስከ አጤ ምኒልክ ገጽ 40-47
ምዕራፍ 6 አጤ ምኒልክና የኢትዮጵያ ደንበር መደናበር ጅመራ ገጽ 47-57

## ክፍል ሶስት

ምዕራፍ 1 የኢትዮጵያ ዳር ደንብር በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ገጽ 58-65
ምዕራፍ 2 ባለሥልጣናች በጎንደር መሬት ሲሰጡ ማቀድ ገጽ 66-85
ምዕራፍ 3 ደርግና ዳር ደንበር ገጽ 101-106
ምዕራፍ 4 ዳር ደንበር በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ዘመን ገጽ 107-108
ምዕራፍ 5 ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን ሊሰጥ ነው ገጽ 109-116
ምዕራፍ 6 በድንበር ብቻ ከተጻፉት ለማስረጃ ገጽ 119-122
ምዕራፍ 7 የኢትዮጵያ ድንበር ኮሚቴ የድምጽ ሠነድ ገጽ 127-142

## ክፍል አራት

ምዕራፍ 1 የታሪክ ቅኝት ስለ ወልቃይት ገጽ 146-150
ምዕራፍ 2 ወልቃይት ወደ ትግሬ ሲከለል ጎንደሬዎች ዝም አሉ ገጽ 151-163
ምዕራፍ 3 "ትግርኛ በመናገሩ ብቻ በጥላቻ እንዲታይ ሆኖአል ገጽ 168-170
ምዕራፍ 4 ለወልቃይት የጎንደር ልጆች ገጽ 173-177
ምዕራፍ 5 ትግሬ ነን ላላችሁ የወልቃይት ልጆች ገጽ 177-186

## ክፍል አምስት

ምዕራፍ 1 ለወያኔ ደጋፊዮዎች የትግራይ ልጆች ገጽ 187-195
ምዕራፍ 2 ወያኔና የትግራይ ሕዝብ አንድ አይደለም ገጽ 195-202
ምዕራፍ 3 የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ! ገጽ 202-207
ምዕራፍ 4 ይድረስ ለድርጅቶች ገጽ 208-213
ምዕራፍ 5 የኢትዮጵያ ምሁራን ገጽ 214-222
ምዕራፍ 6 እንደ ቀይ ባህር ዓባይንና አጋዴን እንዳናጣ ገጽ 223-230
ምዕራፍ 7 የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ደረፍ? ገጽ 231-233
ምዕራፍ 8 ጠቅላላ ሠነድ ገጽ 234-238



## ምዕራፍ 1

## ምስጋና

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን! ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ዓለም ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው! የጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች ም/ 2 ቁ/10 "በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል" ይላል። በዚህ በስደቱ ዓለም የተለያዩ ችግሮች ሲደርስብን ልዑል እግዚአብሔር ሰዎችን እየላከ ችግራችን ይቀርፍልናል። እንዴ ይሆናል ብዬ ባላሰብኩት በሕልሜ እንኳን በማላልመው መንገድ የሞራል ውድቀት ደርሶብኝ እግዚአብሔር በጥበቡ ጥሪትን ልኮ አስወገደልኝ። እናት ስም ስታወጣ "ጥሪት"አለች የእኔ ዓይነት ማዕቀብ ሰዎች ሲደርስባቸው ጥሪት ጭንቀታችን እንደፈታህ ለአንተም ልዑል እግዚአብሔር አይለይህ። ይህን መጽሐፍ በምጽፍበት ወቅት በማናችውም ጉዳይ በማማከር የተባበሩኝ ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛውና አቶ ፈንታሁን ጥሩነህ፥ ወይዘሮ የካባ ሲሳይ እምባው፤ ላደረጋችሁልኝ ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ።

የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ የተባለውን መጽሐፍ ያስመረቁልኝ ወይዘሪት ድንበር ነሽ ደበብና አቶ ደሴ ታደሰን፤ አመሰግናለሁ። ይህን መጽሐፍ ለአንባቢ ያደረሱልኝ አቶ ደሴ ታደሰ፤ አቶ ክንፈ ተሰፋየና አቶ ሹመት ጉዳይን ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉት ወዳጆን ከልብ አመሰግናለሁ።

አቶ አያናዝጊ አ|ወልቃይት የተባለውን ሊያሳትሙት የጻፉትን መጽሐፍ እንድጠቀምበት ስለፈቀዱልኝ አመሰግናለሁ። መጽሐፍ ለሚጽፍ ሰው አንድ ገጽ ሠነድ ይጠቅማል። ስለዚህ መጽሐፍ፤መጽሔትና ጋዜጣ፤ በመስጠት ብቻ ሳይሆን መጽሐፍት ያዋሱኝን ጭምር አመሰግናለሁ። በተለይ አቶ ብርሃኑ ጣሰው፤ አቶ መልኩ በላይነህ፤አቶ አባይነህ መሸሻ፤ አቶ ሞገስ መርሴ ዔአዘን፤ ወይዘሮ በላይነሽ ተክለ ሃይማኖት፤ አቶ አበበ ድባዩ፤ ሊቅ ዶ/ር ጌቱ ገላየ፤አቶ ሰሎሞን አንተነህን ከልብ አመሰግናለሁ። እናንተ ውድ ወገኖቼ ጠቃሚ ሰነድ ባትልኩልኝ ኑሮ ይህን መጽሐፍ ጽፌ ለአንባቢ ማቅረብ አልችልም ነበር። በድጋሜ ከልብ አመሰግናለሁ።

ሌላው በአሜሪካ አገር ካሉት ኢትዮጵያውያን መደበሮች ዩስተን ቴክሳስ ማሩ ግሮሰሪን ከልብ አመሰግናለሁ። ምክንያቱም ሒሳቡን በተሉ ስለሚልኩልኝ ነው ሌሎች መደበሮች ግን በየሳምንቱ ስልክ እየደወልኩ መጠየቁ ስላሰለቸኝ" ይጥቅማችሁ" በማለት የተውኳቸው ብዙ ናቸው። እንኳን አስበው ሂሳብ ሲልኩ ቀርቶ በተደጋጋሚ ተጠይቀው ሂሳብ የማይከፍሉ ናቸው።

## መታሰቢያ

ይችን ከጋምቤላ እስከ ሁመራ የምትለውን መጽሐፌን ከዚህ ለሚከተሉት ኢትዮጵያውያን! መታሰቢያ ትሁናቸው:: በኢትዮጵያ የሚኖሩ ወገኖቻችን ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት መሬት ለሱዳን ሊሰጥ በማሰቡ መሬታችን አንሰጥም ብለው ከሱዳን ወታደርና ከወያኔ ወታደር ጋር ተታኩሰው ለሞቱትና ታስረው ለሚሰቃዩት ንብረታቸውን ለተዘረፉት ቤታቸውን እንዲለቁ ተደርጎ በችግር ለሚሰቃዩት!

ከአገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን 1999 ዓም ጀምረው የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚሽን በሚል ተደራጅተው ዜናውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ በማድረግና ሠላማዊ ሰልፍ በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ ዳር ደንበር ለማስከበር ለተዘጋጁት ኢትዮጵያውያን!

የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ለባዕድ መሰጠቱን በዓለም ዙሪያ ላሉ ኢትዮጵያውያን በመግለጽና የሀገሪቱን ታሪክ ያውቃሉ የተባሉትን ምሁራንና በደንበር ከተማና ገጠር ንዋሪ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን ሱዳን ውስጥ ከታሰሩበት ቦታ በስልክ አነጋግረው ችግራቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቅላቸው በማድረግ የታገሉ የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮንና የጀርመን ድምጽ የራዲዮ ጣቢያ የአማርኛ ዜና ዘጋቢዎችና ሠራተኞች! የግል የዜና አውታሮችና (ፓል ቶክ) አዘጋጆች! ስለደንበሩ ለደከሙ ኢትዮጵያውያን!

ለጄኔራል ነጋ ተገኝና ለኮሎኔል አስናቀ እንግዳ፤እንዲሁም ለአቶ አሰፋ ጫቦ! ለጋንቤላው ተወላጅ ለአቶ ኦባንግ! እንዲሁም ደግሞ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና መሠረቱን ዶግማና ቀኖናውን ለያይተው ለሚያስተምሩ ለአባ ወልደተንሣይ አያልነህና በስደት ዓለም ላሉ የቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎች! የወንጌል ገበሬዎች! በመጨረሻ ለዳኛ ወይዘሪት ብርቱካን ዲመቅሳ እና ለሥልጣነ ሕዝብ ለዲሞክራሲ ሲታገሉ ደማቸው ለፈሰሰው ኢትዮጵያውያን መታሰቢያ ትሁናቸው::

በሃይማኖት ሆነ በሕግ መጽሐፍት
እንዳንዋሽ ነበር ትእዛዛት ቀደምት
እውነት ተደብቃ ውሸት ተከብራለች
ካልዋሸሽ ተብላ ብርቱካን ታስራለች
ይታወቅ እውነቱ ንገሪያቸው እትስሟቸው ጤና
ሁልግዜም ደህና ሰው አላሉሽምና
አለኝ ብሩኅ ተሥፋ በኢትዮጵያ አገሬ
ጭማቂ እጠጣለሁ ከብርቱካን ፍሬ::



## ምዕራፍ 2
## ፊር አስጨባጭ

ይህን ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሳሁበትን ምክንያት ቅድሚያ ላብራራ ይፈቀድልኝ:: 2000 ዓም ላይ የዳ/ዊ አጤ ቴዎድሮስ የ140 ዓመታቸው መታሰቢያ <u>አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ</u> የተባለ መጽሐፍ ለመጻፍ ጀምሬ በማጠቃለል ላይ ሳለሁ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ሁኔታ መነሳት ጀመረ:: ይህን የድንበር ጉዳይ ከመጽሐፉ ውስጥ በአንድ ክፍል ለማጠቃለል አስቤ ስጀምር መጽሐፉ ትልቅ ሆነብኝ:: በዚህ ወቅት አቶ ፈንታሁን ጥሩነህን ስለ ሁኔታው አማከርኳቸው እርሳቸውም "ድንበሩን በተመለከተ ራሱን ችሎ በአንድ መጽሐፍ ቢወጣ ይሻላል:: የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ለብቻው ይውጣ" አሉኝ:: እኔም ከዚያ በኋላ መልቀምና መልክ እንዲይዝ ማስተካከል ስጀምር ብዙ ወራት ወሰደ::

የኢትዮጵያ ችግር ከአደር አደር እየባሰ እንጂ እየተሻሻለ ባለመምጣቱ የነበራትን ገናና ታሪክ ሳነብ አለቅሳለሁ:: በተለይ ነባሩን ታሪኳን ስመለከት ሰላም ይነሳኛል:: አገር የሚመራው ድርጅት ስልጣኑን ለማሰንበት ሲል ብቻ የኢትዮጵያን ከጋንቤላ እስከ ሁመራ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሊሰጥ መሆኑን የተለያዩ የዜና አውታሮች የንፋስ ድምጽ ሬዲዮ ዘግበዋል::

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድነት ተነስቶ ዳር ደንበሩን ማስከበር ይኖርበታል:: እንዲሁም በሃይማኖት ምክንያት የሚደረገው ጠብና ግድያ ማቆም ይኖርበታል የሚል እምነት አንጸባርቋል:: ይህ መጽሐፍ ግለሰቦች በተናገሩትና በጻፉት ላይም ነጥቦችን በማንሳት በሰነድ አስደግፎ መልስ ይሰጣል::ጠቅለል ባለ መልኩ ድርጅቶችን ሆነ ምሁራንን መንቀፉን ዘግቧል:: በመጨረሻ ግን የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ይውደቅ ብሎ ጥያቄ አቅርቦ ያልፋል::

አንባቢያን ለማስገንዘብ የምፈልገው ነገር ቢኖር እኔ የምጽፈው አንዱን ቡድን ለማስደሰት ሌላውን ቡድን ለማስከፋት አይደለም:: መጽሐፉን ብትገዙት ባትገዙት እኔ ግድ የለኝም:: እኔን ደስ የሚለኝ ነገር መጽሐፉ ከማተሚያ ቤት ወጥቶ ከተወሰኑ አንባቢያን እጅ ከገባ በኋላ ትልቅ ደስታ ይሰማኛል:: የእኔ ትርፍ የተሰማኝን መግለጽ የሀገሬን ጉዳይ መግለጽ ነው:: ሌላው ሳሳስብ የምወደው ነገር ቢኖር ይህ መጽሐፍ በቋንቋ ጥራት በቃላት አመራረጥ ረገድ ከታየ እኔ ለዚህ ዓይነት ብዙም አልሰነድበትም:: ለእኔ ጥራትና ብቃት ብዬ የምወስደው በያንዳንዱ ምዕራፍ በዋቢ ሠነድ መዝግቦ ማቅረብን ነው:: ሌሎች ጊዜውም የሰው ኃይልም ኑሮአቸው ለአንባቢ ማራኪ አድርገው ያቀርባሉ:: ለዚህ እኔ አልሆንኩም::

መጽሐፉ ይሸጥልኛል በሚል ወይም እኔ እገሌን አስደስታለሁ በሚል ለመጻፍ ስላልተነሳሁ የብዙ ሰዎች ስም ሊነቀፉ ይችል ይሆናል። ይህ ነቀፌታ ለተረዳው ቂመኛ ነቀፌታ ሳይሆን ጤነኛ ነቀፌታ ነው። ለወደፊቱ መንቃቀፍ ትምህርት እንዲሆነን በር ይከፍታል የሚል እምነት አለኝ። ባይገርማችሁ ከሚያኮርፉት መካከል ተነቃፊው ብቻ ሳይሆን የተነቃፊው ባልንጀራና ቤተሰብ ነኝ ባዩ ነው። በውጭ አገር በአሜሪካ ስንኖር የኢትዮጵያ ታሪክና ሁለመናውን ጠብ ርግፍ አድርገን ከተውነው ውለን አድረናል። ነገር ግን መተቻቸትና መነቃቀፍን በሰዓት ስብሰባ ሆነ ግብግብ አለመገኘትን በተመለከተ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሁሌም ተሎ አይመጣም አልያም ደግሞ እርሱ ማነው እኔንና እኛን የነቀፈ እንላለን ለምን?።

ይህ ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የተባለው መጽሐፍ በ5 ክፍልና በ30 ምዕራፍ የተከፈለ ሲሆን በእርግጥ አንዳንድ ምዕራፍ ረዘም ይላል። እኔ ከሌሎች ደራሲያን ጥቅስ ስወስድ መጽሐፉ በታተመበት ማዕረግና ስም እመዘግባለሁ። ከዚያም አንድን መጽሐፍ ከመጽሐፌ በፊት የደራሲውን ስም ከጻፍኩ በኋላ በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ "---"ሲሉ ጽፈዋል እያልኩ እጽፋለሁ። ሁለተኛ ያንን መጽሐፍ ከሌላ ምዕራፍ ላይ ጥቅስ ስወስድ መጽሐፉን እንጂ የደራሲውን ስም አልጠቅስም። 65 ገጽ ከሆነው መጽሐፍ ይባላል። መጣጥፍ ደግሞ ከ5 ገጽ እስከ 64 ገጽ ያለው ይሆናል። ከ1 ገጽ እስከ 4 ገጽ በራሪ ወረቀት ይባላል። ጥቅስ እስካልተወሰደ ድረስ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው።

አንባቢያን ማሳሰቢያ ከጎንደር ወደ ትግሬ የተከለሉትን ወረዳዎችን በተመለከተ ጠቅለል ባለ መልኩ "ወልቃይት" እያልኩ እጽፋለሁ። ወልቃይት የጎንደሬው ብቻ ሳይሆን የአማራው አባት ዋና ባድማ ስለሆነ ወልቃይት እያልኩ እጽፋለሁ። ወልቃይት ሰፊና ትልቅ አገር የነበረ በመሆኑ ሌሎችን ወረዳዎች ቀርቶ የአማራውን ሕዝብ አጠቃሎ ሊይዝ የሚችል አገር በመሆኑ ወልቃይት እያልኩ እጽፋለሁ። እንዲያውም ወልቃይት ያለ ሕግ ከጎንደር ወደ ትግሬ የተከለለ በመሆኑ በጎንደር ያሉትን ወረዳዎች ብቻ ሳይሆን ከወሎ ወደ ትግሬ የተከለሉትን ወረዳዎች ሳይቀር ያጠቃልላል። ምክንያቱም ከወሎ ወደ ትግሬ የተወሰዱት ወረዳዎች ያለ ሕግ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል። ሌላው መጽሐፍ በጎንደር ላይ ጠበቅ አድርጎ የያዘ ይመስላል። እኔ ጠብቤ ለመሄድ ፈልጌ ሳይሆን 1ኛ ሁኔታው የተከሰተበት በመሆኑ 2ኛ ደግሞ ሰነዶች የበዙበት በመሆኑ እንጂ በሌላ አለመሆኑን ለአንባቢያን አሳስባለው።

መልካም ንባብ አማረ አፈለ ብሻው!



## ምዕራፍ 3
## በታሪካችን እንኩራ እንጅ አንፈር!

አባ ቀውስጦስ የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ <u>ይግባኝ ለክርስቶስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 58 "ምን አልባት ሳይሰሙን ምን አደከመን እንል ይሆናል። ነገር ግን እነሱ ሰሙም አልሰሙም እኛ መናገር አለብን። ፀሐይ የሚሞቀኝ የለም ብላ ከመውጣት፣ወንዝም የሚጠጣኝ የለም ብሎ ከመፍሰስ እንደማያቋርጥ ሁሉ መምሕራንም የሚሰማን የለም ብለን ዝም ማለት የለብንም" ሲሉ ጽፈዋል። "መምሕራንም የሚሰማኝ የለም ብለን ዝም ማለት የለብንም" የሚለውን ጥቅስ ስወስድ እራሴን መምሕራን አድርጌ ቆጥሬ እንዳልሆነ እንድትገነዘቡልኝ አደራ እላለሁ። የጥቅሱ መዝጊያ ስለሆነ ለመጨረስ ፈልጌ ነው። የብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ አባባል ደግመን ደጋግመን ማለት ላልሰሙት ማሰማት ይኖርብናል። ጉዳዩ የማንነት መሰረት በመሆኑ ነው።

ይድነቃቸው ተሰማ፥ <u>ሰምና ወርቅ ተሰማ እሸቴ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 41
"ባለስልጣኖቹ እስኪያስቡበት
መናገራችሁን እንዳትተውት"
ሲሉ ጽፈዋል። ዓላማችን ከግቡ እስኪደርስ ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ጠንክረን መግፋት እንዳለብን ያመለክተናል። እኔም ተስፋ ሳልቆርጥ የኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ ቋንቋ ትውልዱ እንዲያውቅ ያቅሜን በምጽፈው መጽሐፍ መግቢያ ሁሌም አንርሳ ማለቴን አልተውም። አንድ አይነት ኮትና ሱሪ ለብሳችሁ ሼሚዝና ክራባት ከሌለው መልካም ቆዳ ጫማ ለብሳችሁ የእግር ሹራብ ከሌለው ያምራል? የፈለግነውን ያህል ብንሰለጥን ያለ የራስ ታሪክና ባሕል ቋንቋ ሊኮራ አይቻልም። ለአንባቢያን የማሳስበው ሁሌም አንድ ነገር አለ! ያም ቋንቋችን፥ባህላችን የማንነት መለያችንን ማክበር የአገራችን የኢትዮጵያን ስም አረቦች "ሀበሻ" አውሮፓውያን "አቢሲኒያ" የሚሉንን ፈጽመን መቀበል የለብንም። አገራችን ስሟ ኢትዮጵያ እንጂ የውጭ ሰዎች በሰጡን ስም አንጠቀም! እያልኩ የታሪክ ማስረጃ እየጠቀስኩ ሳሳስብ ቆይቻለሁ። ዛሬም አሳስባለሁ።

ዶ/ር ሒሩት ወልደ ማርያም <u>ሐመር መጽሔት</u> 15ኛ ዓመት ቁጥር 16 የካቲት/መጋቢት 2 ሽህ ዓም ገጽ 21 "እኛ ሁሉን ነገር ከውጭ ሲመጣ ነው የሚያምረን ልክ የሚመስለን ይኼን ዝቅተኛ አመለካከት ማስወገድ አለብን። ለራሳችን ለሀገራችን ለሕዝባችን ለዕውቀታችን ለሃይማኖታችን ለባህላችን ቀና በጎ የሆነ አመለካከት እንዲኖረን ያስፈልጋል። ራሳችን በራሳችን ካላከበርን ሀብታችንን ታሪካችንን በጥንቃቄ ካልያዝን ማንም አያከብረንም። ሌላውም የሚከብረን የራሳችን ስናከብር ነው" ብለዋል። በእርግጥ በተለይ ለዘመናዊ

የእምነቱ አማኞች ባህልን፣ሃይማኖትን ማክበር እንደ ባዕድ አምልኮ ስለሚቆጥሩት እኛም ይህን እየሰማን ማስተጋባት የለብንም።

መምሕር ብሩክ ገብረ ሊባኖስ ማደስ ወይስ ማፍረስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 103“ ኢትዮጵያውያን ፕሮቴስንታስት ስለታሪክና ቅርጽ ጥላቻ ያደረበት አንድ ኢትዮጵያዊ ፓስተር በአንድ ፕሮግራም ላይ ሲጸልይ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ የታሪክና የቅርጽ የባህልና የሥርዓት ፍቅር ከዚህ ሕዝብ አእምሮ ታስወጣ ዘንድ በኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ ብሎ ጸለዩ” ሲሉ ጽፈዋል። የኢትዮጵያን ታሪክና ቋንቋ ባህል እኛ አክብረን ሌሎች እንዲያከብሩ ማስተማር ይኖርብናል። በእርግጥ በዛሬው ዘመን በተለይ በውጩ ዓለም ያለን ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ሳይቀር በግዕዝ ቋንቋ ከመጻፍ በፈረንጅ ቋንቋ የሚጽፉ ብዙ ናቸው። በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ የቤተ ክህነት ተማሪዎች ማክበርና ማስከበር ያለባቸው ግዕዝ ቋንቋን መሆኑን ረስተው ወይም ዘንግተው ሲጽፉ የሚታዩ በፈረንጅ ቋንቋ ነው። ካህናትና የቤተ ክርስቲያን መምሕራን ጉራማይሌ ቋንቋ መጠቀም ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ይህ ሊታሰብበት የሚገባ በውጭ አገር ያላችሁ ሆናችሁ በአገር ቤት ያላችሁ የቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር ስትነሱ ጥሪት ባለ በአማርኛ ካስተማራችሁ ምዕመናኑ እናንተንም ሊያከብራችሁ ይችላል። ሕዝበ ክርስቲያኑም ባህሉን ቋንቋውን እንዲያከብር ይሆናል። ነገር ግን ሕጻናትን ለማስተማር ከሆነ በሚገባቸው ቋንቋ አስተምሯቸው።

ለምሳሌ “እርቶዶክስ” ሃይማኖት ተከታዮች ነን ማለት ምን ማለት እንደሆነ በጥሞና ልናጤነው ይገባል። ሌሎች አርቶዶክስ አማኞች ታቦት የላቸውም። ለምሳሌ የግብጽ አርቶዶክስ ሃይማኖት ካህናት ሆኑ ጳጳሱ አይገረዙም። ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጾሞች አሉ በሌሎች አርቶዶክሶች የእኛን ያክል ጾም የላቸውም።የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶዎች ደግሞ አሪትን ከወንጌል አጣምረን የምናመልክ ነን። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብለን ልንጠራ ይገባናል ይላሉ። ከዚህ መጽሐፍ ጥቅስ እስካልተወሰደ ድረስ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እያልኩ እጽፋለሁ የኢትዮጵያ ቀመር የራሳችን ሲሆን ከኖህ ጀምሮ የመጣ አቆጣጠር ነው። የሰው ወርቅ አያደምቅ! እንደሚባለው ነው እንጂ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የኢትዮጵያን 2000 ዓም በዓል (ምሊንየም) መከበር ይኖርበታል ብለው እያከበሩት ባሉበት ወቅት እኛው ኢትዮጵያውያን የራሳችን የቀን መቁጠሪያ ማክበሩን ትተነዋል። ለምሳሌ አንድ ወዳጄ መጽሐፍ ሜጋ ማከፋፍያ ገዝተው ልከውልኛል። በመርሳት ደረሰኙ ከመጽሐፉ ውስጥ አብሮ መጥቶ ስመለከተው በኢትዮጵያ ቀን ሳይሆን የተጻፈው በጎርጎሬዎስ ቀን መቁጠሪያ ነው ለምን?

ሜጋ ማከፋፈያ ኃ/ተ/የግ/ማኅበር ደረሰኝ ቀን 22/3/08 ይላል። በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ አገር በቀል የሆነ ድርጅት የሚያዘጋጀውን ደረሰኝ በአገሩ የቀን መቁጠሪያ ማዘጋጀት ሲገባው እንዴት ቅኝ ገዥ በሆነው የጎርጎሬዎስ



የቀን መቁጠሪያ (ካላንደር)ደረሰኝ አዘጋጅቶ እየጻፉ ሕዝቡ ማንነቱን እንዲረሳ ያደርጋል? ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ላሳስብ እወዳለሁ። አባቶቻችን የሚሉት አባባል አለ ያም “መንገድ በምን ይቀራል” ይላሉ። ለምሳሌ መንገድ ከሚሄዱ ሰዎች መካከል አንዱ ልጠዳዳ ብሎ ሲቀር ባልንጀሮቹ ብዙ ጎዳና ሕደዋል። ይህ ሊጸዳዳ ወደ ኋላ የቀረው ሰው ከእነዚህ ሰዎች ለመድረስ ልቡ እስኪጠፋ መሮጥ አለበት። አለበለዚያ ብቻውን ይሆንና ለብዙ አደጋ ይጋለጣል። አንድ ነገር በጊዜው ሊታረም ካልቻለ ከዋለ ካደረ ሰተቶች በዝተው ኋላ ለመመለስ ችግር ይሆናል። የቀን መቁጠሪያችን ሆነ ግዕዝ ፊደላችን እህንግዜ አጥብቀን መያዝ ይኖርብናል። ጊዜ ከተሰጠው ከዋለ ካደረ “እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ” እንደተባለው እንዳንሆን እናስብበት።

አስቻለው ከበደ ክርክቢዴል ሳዶፍ ኢትዮጵያና የሰማይ ኃያላት በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 52 “በግዕዝ ሰብዕ ማለት ሰው ማለት ሲሆን በኦሮመኛ ሰባ ጉዳ ማለት ሕዝብ የሚል ትርጓሜ ይሰጣል። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚተነትኑት በግዕዝ ሰብዕ የሚለው የሰው መጠሪያ ቃል ሰብዐ (ሰባት) ከሚለው ቁጥር የተወሰደ ሲሆን ይህም የሰው ተፈጥሮ ከአራት የመሬት ባህሪ (መሬት+ውኃ+ንፋስና እሳት)እና ከሶስት የመለኮት ባሕሪ (ነቢባት ሃያዊትና ልባዊት) በአጠቃላይ ከሰባት ባህሪ የተፈጠረ መሆኑን ለማመልከት ነው። እያንዳንዱ የግዕዝ ፊደላት ለምሳሌ ከሀ ግዕዝ እስከ ሆ ሳብዕ ያለው የፊደል ቆጠራ በሰባቱ ቀናትና በሰባቱ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ተመሳጥሮ የተቀናበረ መሆኑን ነው” ሲሉ ጽፈዋል። የራስን ታሪክ ማወቅ ይጠቅማል። ጥቅሙም ለራስ ብቻ ሳይሆን እልፎ ለጎረቤት ልጅ ይሆናል። ቀስ እያለ ከጎረቤት ወደ መንደር ከመንደር ወደ ደብር ከደብር ወደ ምክትል ከምክትል ወደ ወረዳ ከወረዳ ወደ አውራጃ ከአውራጃ ወደ ክፍለ ሀገር ከክፍለ ሀገር ወደ ሐገር ይዘመታል። ስለዚህ የራስን ቋንቋ ታሪክና ባህል ሃይማኖት መጠበቅ ስልጥንና እንጂ ኋላቀርነት አይደለም።

አለቃ ታየ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 6 “ታሪክ መማርና ማወቅ ለብዙ ነገር ይጠቅማል። መጀመሪያ የድንቁርና ዕውርነት ዓይን ይከፍታል። ሁለተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት የፍጥረቱንም ብዛትና የልዩ ልዩ ወገንንም ዓይነት የዓለምንም ታላቅነትና ሰፋት ያይበታል። ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ እስከ ዘመን የሆነውን ሁሉ ነገር ሲማር ጥንት እንደ ተፈጠሩ አስቀድሞ እንደ ነበረ ሁኖ ያውቃል። በዓለም ያሉን ልዩ ልዩ ሕዝብ አገራቸውና ጠባያቸውን ያምላኮቻቸውን የመንግሥታቸውን ሥርዓትና አኗኗራቸውን በታሪክ ሲመለከት ሲመረምር ሲያስተውልም በቤቱ ተቀምጦ ዓለም ሁሉ ዙሮ መርምሮ እንዳየ ሰው ይሆናል” ሲሉ ጽፈዋል።

## ምዕራፍ 4
## ለአንባቢያን ከፀሐፊው!

ከዚህ በፊት በጻፍኳቸው መጽሐፍት በተለይ አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች በተባለውና የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፎቼ ላይ አንባቢያን አንዳንዶች አልተደሰታችሁም። በእርግጥ አንድ ግለሰብ ሁሉንም ሊያስደስት አይችልም። አስተያየታችሁን ለጻፋችሁልኝ እጅግ በጣም ከልብ አመሰግናለሁ። ነገር ግን ጓደኞቻችሁ አንብበው የነገሯችሁን ይዛችሁ እናንተ ሳታነቡት ለጻፋችሁልኝ አንባቢያን አክብሮት የለኝም። ተውሳችሁ ሆነ ገዝታችሁ ገጽ በገጽ ጠንካራ ጎኑንና ደካማ ጎኑን ገምግማችሁ ለጻፋችሁልኝ አንባቢያን በድጋሜ ከልብ አመሰግናለሁ። አንባቢዮቼ የተቀየማችሁበት በሁለት ምክንያት ነው።

"1ኛው የኤርትራን ካርታ ከኢትዮጵያ ካርታ አውጥተሃል
2ኛው ወያኔንና የትግሬን ሕዝብ በአንዳይን አትቶ ትላለህ" የሚሉ ናቸው።

1ኛውን አስተያየት በተመለከተ ምዕራፍ ከፍቼ መልስ ልሰጥበት አልፈልግም ነበር ነገር ግን በብዛት የመጣው አስተያየት በመሆኑ መልስ አስፈለገው። 2ኛውን አስተያየት በተመለከተ ክፍል 5 ምዕራፍ 2 እንድታነቡ እላለሁ። ወደ 1ኛው አስተያየት ልመለስና የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድ ናቸው። ደጋው የኤርትራ ሕዝብ ከጎንደር ደንቢያ ቋራ፤ በተለይ ብሌኑ ከጎጃም አገው ምድርና ከወሎ ሰቆጣ የሄደ ሲሆን ሌላው የሀማሴኑ ሕዝብ ደግሞ ከትግራይ አጋሜ የሔደ ነው። ራሳቸው ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፍወርቅ ትግሬ ናቸው። ነገር ግን በታሪክ አጋጣሚ ቅኝ ገዥዎች ከቀደም ጀምሮ በምጽዋ ብቅ እያሉ ስለቆዩ ሕዝቡን ባንዳ አድርገውታል። ይህ አባቶቹ ባንዳ የሆነ ትውልድ በ4ኛው አጤ ዮሐንስ ዘመን እነራስ ወልደ ሚካኤል የግብጽን ጦር መርተው የመጡ ናቸው። ከዚያም ግብጽ በ4ኛው አጤ ዮሃንስ ጀግንነት ተደብድቦ ሲባረር ባንዶች አፈሩ። ኋላም ጣልያን ቀስ በቀስ መግባት ሲጀምር ሁኔታው ልውጥውጥ እያለ ይሄድ ጀመር። ጣሊያን መላ ባሕረ ነጋሽን ተቆጣጥሮ ስሟን ኤርትራ ብሎ ጠራት። ከዚያም በአድዋ ጦርነት ድል ሲሆን ጣልያን ባለበት ቆመ። በዚህ ወቅት የባህረ ነጋሽ ሕዝብ ባንዳ ያልሆነው ከቄስ እስከ ነጋዴ ወደ ኢትዮጵያ እየመጣ ይኖር ጀመር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ እንደ ዜጎቹ ቆጥሮ እያስተማረ አንሮአቸዋል። በኤርትራ የነበሩ ከ4ኛ ክፍል በላይ አይማሩም ነበር። ከዚያም ወታደርነት እንጂ ሌላ ክፍት ስራ አልሰጣቸውም። በ1928 ዓም ጣልያን የአድዋን ደም ለመመለስ ወደ ኢትዮጵያ ሲዘምት ኤርትራውያን ታጥወቅ ኢትዮጵያን ወግቷል። ከሚገርማችሁ ነገር ቢኖር እነዚህ ኤርትራውያን ከጦርነቱ ሲመቱ ጣልያኖች አይቀብሯቸውም ነበር።



ጳውሎስ ኞኞ የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 129 "በጦር ሜዳ የወደቁትን የኢጣሊያኖችን ሬሳ ብቻ ጥቁር ተወላጆች እያነሱ እንዲቀብሩና የጥቁሩን ሬሳ እንደወደቀ እንዲተውት ከኢጣሊያ አለቆቻቸው ጥቁር ወታደሮች ታዘዙ። ሹምባሽ አንዶም ተስፋጽዮን ወደ ኢጣሊያዊው አለቃቸው ቀርበው ጥቁሮች ከነጮች ጋር አብረው ጎን ለጎን እየተዋጉ ሁሉ በቀብር ጊዜ ለምን ልዩነት ይደረጋል? ብለው ጠየቁ። ይህ ጥያቄ በኢጣሊያኖች ዘንድ እንደ ድፍረት ስለተቆጠረ ሹምባሽ አንዶም ተቀጡ። ሹምባሽም ሌሊቱን አምልጠው ከኢትዮጵያውያን ጋር ተደባለቁ። ከዚህ በኋላ ብዙ ኤርትራ ተወላጆች ከኢጣሊያ እየከዱ ወጡ" ሲሉ ጽፈዋል። ኤርትራውያን ከጣሊያን እየከዱ ወደ ኢትዮጵያውያን የተቀላቀሉት ቀንበር ጠቦባቸው እንጂ ለኢትዮጵያ ነፃነት ብለው አልነበረም። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ኤርትራውያንን እንወዳቸው ነበር። ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ በ1929 ዓም የጣሊያ ጦር እጃቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁ ምህረት የጠየቁ ከሳይ የተጠቀሰው ከጣልያን ከድተው ከርሳቸው ጋር ለነበሩ ኤርትራውያን ነበር።

ሀዲስ አለማየሁ ትዝታ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 187 "1ኛ ከኢጣሊያ ጦር ሠራዊት አምልጠው በዚያ ጊዜ ከራስ እምሩ ጦር ጋር የነበሩትን ኤርትራውያን ከሌሎች የራስ ሠራዊት አባሎች የተለዩ ቅጣት እንዳያገኛቸው ሙሉ ምህረት እንዲደረግላቸው" የሚል ጥያቄ ነበር ያቀረቡት ሲሉ ጽፈዋል። ኤርትራውያንን በተመለከተ ምን ራስ እምሩ ብቻ ራስ ካሳ በማይጨው የጦር ግንባር ላይ ቅድሚያ የሚመጡት ኤርትራውያን ወታደሮች በመሆናቸው በእነሱ ላይ ጥይት መተኮስ ልባቸውን ያቆስለው እንደነበር በ1929 ዓም በስደቱ ወቅት ለአንድ የፈረንሳይ ተወላጅ ለአጤ ኃይለ ሥላሴ ጥያቄና መልስ ሲያደርግላቸው ራስ ካሳም እንዲሁ የሰጡት መልስ አለ። ያን በፈረንሳይኛ ተጽፎ የነበረ መጽሐፍ በቅርቡ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለንባብ ቀርቧል።

ጸሐፊ ማርሴል ግሪዮል ተርጓሚ ሳቀች አክሊሉ የንጉሠ ነገሥቱ ትውስታ በ1929 ዓም በተባለው መጽሐፍ ራስ ካሳ በገጽ 59 "የመጀመሪያውን አጥቂ ኃይል መትተው የሚጋርዱ የኤርትራ ወታደሮች ከዚያ ቀጥሉ መሣሪያ ታግዘው የሚዋጉ የመንግሥት ወታደሮች ቀጥሎ ደግሞ ከፊተኞቹ እጅግ የከፋ የሚመስሉና ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ ብቅ የሚሉ ፋሺስቶች ናቸው። ፋሽስቶች ከሌሎቹ ቋሚ ወታደሮች በበለጠ ሁኔታ ጦርነቱን በጋለ መንፈስ ተሚልተው ያካሂዱታል። ተራ ወታደሮቻቸውን መስራት የማይፈልጉትን ሥራ ሁሉ እንዲሰሩ የሚያስገድዱዋቸው ይመስላል። እነኚህ ቋሚ ወታደሮች ምንም እንደ ፋሽስቶቹ ብዙ ፍላጎት ባይኖራቸውም ከኤርትራውያኑ የበለጠ ፍላጎት ነበራቸው። እጅግ የበረቱት ከኋላ በመሆናቸው የፊተኞቹን ወደፊት ይገፏዋቸው ነበር። ይህም አመዳደብ በነጮቹና በኛ መሀል የደም ወንድሞቻችንን አስመርተው ጣልቃ በማስገባታቸው እነዚህን ማጥቃት ልባችንን ያውከው ነበር። እንዲህ ያለውን ድርጊት ማወዳደር የሚቻለው በጣሊያኖቹ ፊት ሕፃናትና ሴቶችን እንደማሰለፍ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የታሪክ መጽሐፍት በጥሞና ሳስተዋለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤርትራውያንን እንወዳቸው ነበር። ይህ ሁኖ ጣልያን በኢትዮጵያ አርበኞች

ተደብድቦ ሲደክም የሁለተኛው ዓለም ጦርነት አውሮፓ ተጀምሮ ስለነበር ትንሽ ርዳታ እንግሊዞች አድርገው ጠላት መባረሩ አይካድም፡፡ እንግሊዞች አስመራ ላይ በነበሩበት ወቅት የኤርትራ ሕዝብ ወደ ኢትዮጵያ መቀላቀል ይፈልግ እንደነበር ታሪክ ዘግቦታል፡፡

ሹመት ሲሻኝ የኤርትራ ሕዝቦች የአንድነት ትግል በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 8“ ከኢትዮጵያ ጋር እንቀላቀል የሚለው ጥያቄ በአገሩ በሰፊው የተሰራጨ መሆኑን በመጥቀስ ጉራራ ውስጥ ይሰራ የነበር አንድ አሜሪካዊ ተመልካች ለፕሬዝዳንት ሩዝቬልት በመጋቢት 1935 ዓም በጻፈው ማመልከቻ ላይ በኤርትራ የሰሜን ጠረፍ ላይ የሚገኙት ጎሳዎች እንኳ ሳይቀሩ ኢትዮጵያውያን ነን ብለው ቆመዋል፡፡ በአስመራ፤በምጽዋ፤በከረንና በሌሎችም ከተማዎች ውስጥ ያሉ ሱቆች የኃይለ ሥላሴን ፎቶግራፍ በግድግዳው ያልሰቀለ የለም፡፡ ራሱ የእንግሊዝ አስተዳደርም ቢሆን ይፋ በሚያወጣቸው መግለጫዎች አይጥቀሰው እንጂ በውስጥ ሪፖርቶቹ የአብዛኛው ሕዝብ ምኞት ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድ መሆኑን ያረጋግጣሉ በ1936 ዓም አጋማሽ ላይ ብርጋዴር ሉንግሪግ ወደ ሉንዶን ባስተላለፈው ዘገባ ላይ የተማረው ወጣት እንዳለ የአንድነት ታጋይ ነው፡፡ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች እንዲሁም በተዋህዶ አገር ሰፊ ገበያ እናገኛለን ብለው ተስፋ የሚያደርጉ ነጋዴዎችም ለአንድነት ቆመዋል ይላል” ሲሉ ሊቀ ጠበብት ሹመት ሲሻኝ ጽፈዋል፡፡ ኤርትራውያን ይህን ብለው በመነሳታቸው በታላቁ የድርድር ዲፕሎማት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ጥረት 700 ሰዓት ገለፃ በማድረግ 300 ሰዓት በአውሮፕላን ተጉዘው የተባበሩት መንግሥታት ወኪል እንዲልክ ሁኖ ሕዝቡ መዋሕድን መርጦ ሳለ (ፌዴሬሽን) የሚለውን ቢያስቀምጥባቸውም በራሳቸው የተጣለባቸውን በጥሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲቀላቀሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍቅር አያቸው እንጂ አላገለላቸውም፡፡ የአጤው መንግሥት ከፍተኛ የሆነ ተቋም መስርተው እነሱን ለማስደሰት ጥረት አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ልማት እያደረገ ኤርትራውያን ከአረብ አገሮች ጋር ተለጣፊ ሁነው ጀበሃን መሰረቱ፡፡

አበራ ለማ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 13 ሰኔ 1992 ዓም ገጽ 16 “ከ300 በላይ የሚሆኑ የመንግሥት ወታደሮችን በተለያዩ ውጊያዎች ላይ ማርኮ አሊጊደር በሚባል ሥፍራ በአሰቃቂ ሁኔታ አስሮ ለረዥም ጊዜ አቆይቷቸው ነበር፡፡ እኛ ወደ ተሰነይ እያጠቃን መጠጋታችንን ሲያውቅ እነዚያን ምርኮኞች ወታደሮች በሙሉ ከእስር ቤት አውጥቶ እጅና እግራቸውን እያሰረ በመትረየስ አጨዳቸው፡፡ ቀጥሎም ቤንዚን እያርከፈከፈ አቃጠላቸው፡ ጀብሃ ይህን ዘግናኝ እልቂት ከፈፀመ በኋላ የጋሽን ድልድይ በፈንጂ አፈራርሶ ሸሽቶ ጠበቀን ያንን እልቂት በዓይኔ አየሁ፡፡ እመራው በነበረው የጋዜጠኞች ቡድን አማካኝነት ድርጊቱን በካሜራ ቀረፅን ቆስለው የተረፉ 2 ወታደሮችን ቃል መጠየቅ አደረግንላቸው፡፡ ሙሉ ዘገባውን ሠርቼ ለሬዲዮ ስርጪት አቀረብኩ፡፡ ቢሮክራሲው የሻጥር እጁን ጫነበትና ከስርጭት አገደው፡፡ እኔና የቅርብ አለቃዬ አቶ የወንድወሰን ዓለሙ ሃዘናችንን ውጠን ቀረን” ሲሉ ጽፈዋል፡፡ ይህን የመሰለ ሌላም ታሪክ መጥቀስ ይቻላል፡፡



ግዴይ ባህር ሹም አሞራ በተባለው መጽሐፋቸው ሻዕቢያ ምርኮኛን ከጎድጓዳ መሬት ላይ አጠራቅመው በርሃብና በጥማት ሲደክሙ አሞራው እየበላቸው የሞቱ መሆናቸውን ጽፈዋል፡፡

ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ ሞት የተፈረደባቸው 17 ሺህ የኢትዮጵያ ሠራዊት አይ ምጽዋ የተባለውን መጽሐፍ እንብቤ አንጀቴ አሯል ከኤርትራውያን ጋር በቅቶኛል፡፡ ስለዚህ ከእነሱ ጋር መራቁን እንጂ መደጋገፉን በእኔ እምነት አልፈልግም፡፡ የተማረኩት የኢትዮጵያ ወታደሮች የኤርትራን መንገድ እንደሚቆፍሩ

ሻለቃ ስለሽ ፍሰሃ አንድነት ለአንድነት በተባለው መጽሐፋቸው ጽፈዋል፡፡ ወያኔና ሻዕቢያ ጦርነት ውስጥ ከገቡ ጀምሮ በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያንን ለመውሰድ ሻዕቢያ ያላደረገው ጥረት የለም፡፡ ዶ/ር ቅጣው እጅጉ እንደነገሩኝ “የኤርትራ መንግሥት ወያኔን ለመጣል የምትፈልጉ ከሆነ የተማረኩትን ወታደሮች አሰልጥነን እስከ ትጥቃቸው እኔም ያስለጠናችኋቸው ወታደሮች የት አሉ ብዬ ስጠይቅ መንገድ ከሚሰሩበት ወስደው አሳዩኝ፡፡ ከገላቸው ላይ ልብስ የሚታየው ከተፈጥሮ አካላቸው ላይ ብቻ ሲሆን ጫማና ከናቲራ የላቸውም፡፡ ለምን ልብስ እንደማያለብሷቸው ስጠይቅ የደርግ ወታደሮች በመሆናቸው ነው” አሉኝ ሲሉ ነግረውኝ ነበር፡፡

በተለይ የማቀርባቸው ወገኖቼ ወደ አስመራ የሚያደርጉትን ጉዞ አጥብቄ ተቃውሜ ነበር፡፡ ያን አንጱን በዓለም አንቱ የተባለውን ምሁር ሳይንቲስት እንጅነር ቅጣው እጅጉ አላግባባን ብሎ የነበረው ከሻዕቢያ ጋር ተቀራርቦ የጦር መሳሪያ ተቀብሎ ምርኮኞችን ይዞ ኢትዮጵያን ከወያኔ ነፃ ማውጣት ይቻላል በሚለው አመለካከታቸው አለመደገፌ ነበር፡፡ ዛሬ ጋሽም አኩርፈው አያናግሩኝም፡፡ ያቀያየመን የግል ግጭት ኑሮን ሳይሆን ሻዕቢያ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ሊሆን አይችልም በማለቴ ነው፡፡ ከሊቅ ዶ/ር ቅጣው ጋር በያዘው እምነቱ ባንግባባም በሌላው ግንኙነታችን ጨርሰን አልቆረጥነውም ነበርና በ1994 ዓም ዋሽንግተን ዲሲ በነበረው የኳስ ጨዋታ ወቅት ከመሄዳችን በፊት ከሰዎች ጋር እንዳገናኛቸው ጠየቁኝ፡፡ አኳዮ ከሚኖሩ ከአቶ መልኩ በላይነህ ጋር ኢትዮጵያን አስመልክቶ ሰንወያይ እርሳቸው“ በቅርቡ የመሰረትነው ድርጅት አለ ብለው እነ ዶ/ር ስለሽ አያሌው ሲሉ ሰምቻለሁ” ሲሉኝ እኔም “የትጥቅ ትግል አያስፈልግም እላለሁ ደግሞ ከሻዕቢያ ጋር ተገናኝተው ነው እንጂ ዶ/ር ቅጣው፣ የመሰረቱት ድርጅት አለ፡፡ ከሰዎች ጋር አገናኘኝ እያሉ ጠይቀውኛል ” ስላቸው አቶ መልኩ “ከነዚህ ሰዎች ጋር ከተገናኙ ምናልባት ለወደፊቱ ሁለገብ የሚለውን ዓላማ ወደ ሰላማዊ ትግል ሲቀይሩ ይችሉ ይሆናል እናገናኛቸው አሉኝ፡፡ እኔም አሳቡን ሲቅ ዶ/ር ቅጣው ስነግራቸው በጣም ደስ አላቸው፡፡

ዋሽንግተን ዲሲ ስንደርስ ቀነ ቀጠሮና ሰዓት ተወሰነ፡፡ ዶ/ር ቅጣው እጅጉ ካረፉበት ሆቴል ሆነ ስብሰባው፡፡ ከዚያም 1ኛ ዶ/ር ስለሽ አያሌው 2ኛ አቶ መልኩ በላይነህ 3ኛ አቶ ክንፈ ተሰፋዬ ሁነው መጡ፡፡ አቶ ክንፈ ዶ/ር ስለሽ

ድርጅት ደጋፊ ይሆን አይሁኑ አላውቅም አንድም ቃል አልተነፈሱም። ዋሽንግተን ዲሲ የሚኖሩ የዶ/ር ስለሽ ድርጅት ባልደረባ አቶ ዘነበ፤ ቆየት ብለው መጡ። እኒሁ አቶ ዘነበ አስመራ ደርሰው የመጡ ናቸው። አቶ መልኩና እኔ አገናኝ ስለሆን እኔ "ዶክተር እንጅኔር ሳይንቲስት ቅጣው እጅጉ ይባላሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ሊቀ መንበር ናቸው" ብዬ አስተዋወኩ። አቶ መልኩ ደግሞ "ዶር ስለሽ አያሌው ይባላል" ብለው የድርጅት ስም አልጠሩም። አቶ ዘነበ ቆይተው መጡ ተሉ ሄዱ። ዶ/ር ቅጣው ወዲያው የድርጅታቸውን መርሃ ግብር ከቦርሳቸው አውጥተው ሰጡ። በነ ዶ/ር ስለሽ አያሌው፤ በኩል የድርጅት ስም ሆነ መርሃ ግብር የለም። ድርጅታቸው ማን እንደሚባል ቅድሚያ ማስተዋወቅ ነበረባቸው ግን አላደረጉም። ዶ/ር ቅጣው ድርጅታችሁ ማን ይባላል አላሉም።

ውይይት ከመጀመሩ በፊት "እኔ ይቅርታ ዶ/ር ስለሽ እንዳዩት ዶ/ር ቅጣው ከእናንተ ጋር የፈለጉት ለመወያየት ነው። የድርጅታቸውን ስም ሆነ መርሃ ግብር ሰጡአችሁ። ነገር ግን እናንተ ድርጅታችሁ ማን ይባላል። መርሃ ግብሩ መተዳደሪያ ደንቡን ለእርሳቸውም ስጡ? ብዬ ተናግሬ ሳልጨርስ ዶ/ር ስለሽ "የድርጅቱ ፕሮግራም ይሰጣል" ብለው ዘጉት። መነጋገር ያለባቸው ሁለቱ በመሆናቸው እኛ አድማጮች ሆን። ታዲያ ዶ/ር ቅጣው "እናንተምኮ ሀሳብ ስጡን" ብለው ወደኛ ውይይቱን አመጡት "እኔ በበኩሌ ቅድም የጠየኩት የድርጅት መርሃ ግብር በነዶ/ር ስለሽ በኩል አልተሰጠም! የድርጅታቸው ስም ማን እንደሚባል አልነገሩንም ሌላው እኔ ሊቅ ቅጣው እንደምታውቀው በግሌ የትጥቅ ትግል ለኢትዮጵያ አያስፈልግም እላለሁ በተለይ ከሻዕቢያ ጋር የሚደረገው ግንኙነት ለኢትዮጵያ አጥፊ ነው" ብዬ ተናግሬ ሳልጨርስ ዶ/ር ስለሽ፤ "ሻዕቢያም ለኢትዮጵያ ቅዱስ ነው! ወያኔን ያለ ትጥቅ ትግል መጣል አይቻልም" አሉ። ከዚያም 6 ሰዓት ሙሉ ውይይት ተደርጎ ካንድ ወር በኋላ ሊገናኙ ተስማምተው ተለያየን። ዶ/ር ስለሽ ከግብር አበሮቻቸው ጋር ተሰብስበው ዋሽንግተን ዲሲ ጠበቁአቸው። በዚህ ቀን ዶ/ር ቅጣውን ብር የሰጡአቸው መሆናቸውን ለእኔና ለአቶ መልኩ ነግረውናል። ይህ የነዶ/ር ስለሺ አያሌው ድርጅት ስሙ ሳይታወቅ ከስሚል። ይህን ታሪክ ላነሳበት የፈለኩበት ምክንያት ምስጢር ለማውጣት ፈልጌ ሳይሆን እኔ ኢትዮጵያ ከሻዕቢያ የምታገኘው ጥቅም የለም ያለ ድህነት በቀር? የሚል አመለካከቴ ዛሬም አልተቀየረም።

ሻዕቢያን ካልደገፍክ የምትሉኝ ወዳጆቼ በእሳት የተቃጠሉትን አሞራ የበላቸው ራቁታቸውን ቀን ፀሐይ ማታ ብርድ የሚፈራረቅባቸውን ወገኖቼን የሞቱት የተሰቃዩት አልበቃ ብሎ ሌላ ለኢትዮጵያ ስቃይ እናምጣ እንዴ? የኢትዮጵያ ሕዝብ በኤርትራ ምድር ደሙ ፈሷል ይህን ያደረገው ወገኖቻችን ናችሁ ብሎ እንጂ በሌላ አይደለም። ሌላው ቀርቶ ከመቶ 98 እጅ የሚሆነው የትግራይ ሕዝብ በ1984 ዓም ንብረቱን ብቻ ሳይሆን ጥርሳቸው ወልቆ የተባረሩት ወገኖቻችን ማስታወስ እፈልጋለሁ በእኔ ዓይን ኤርትራን የማየት እንደ ጎረቤት አገር አድርጌ ነው። የኤርትራን ካርታ ቆርጬ ያወጣሁት ወድጄ አይደለም። እነሱ እኛ ሰላም እንዳናገኝ በጎሳ እንድንከፋፈል አድርገዋል። በእነሱ አገር 9



ጎሳዎች ሲኖሩ ለአንዱ እንኳን እንዲደራጅ አልፈቀዱለትም። ነገር ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር እንዲደራጅ ሲገፉ ኑረዋል። ቀደም አይደለም ዛሬም ይህን ዓላማቸውን እያስፋፉት ናቸው ስለዚህ በእኔ እምነት ከዚህ በፊት አንድ ነን ብለን ገድለውናል ወገኖቻችሁ አይደለነም ካሉን ጨርሰን ልንርቃቸው ይገባል።

<u>የመጽሐፌ አንባቢ</u> ሲጽፉልኝ እንዲህ ብለዋል "እንኳን ዛሬ ቀደም ሲል ተመስርቶ የነበረው ጀብሃ የኤርትራን ክርስቲያኖች ሲገድላቸው ነበር። ዛሬ እስላሞች እየተስፋፉ ናቸው። የእስላም አክራሪዮች በትንሿ ኤርትራ አይደለም በትልቋ ኢትዮጵያም አክራሪነትን ለማስፋፋት የሚያደርጉትን ተንኮል ይጠፋሃል አልልም። ታዲያ የኤርትራ ክርስቲያኖች ሲደበደቡ እኛ ኢትዮጵያውያን ዝም ብለን ልንመለከት ነው?" ሲሉ ጽፈዋል። አባቴ ልበል ወንድሜ አልያም ወገኔ ልበልና መልስ ልስጣቸው "ወደሽ ተተደፋሽ ቢገፉሽ አይከፋሽ" ነው። ልክ ነው እርሶ እንዳሉት ጀብሃ ሲመሰረት ጀምሮ ክርስቲያኖችን መፍጀቱ ይታወቃል ራስ አስራተ ካሳም ክርስቲያኖች ማለቃቸው አሳዝኖአቸው ነበር አቶ ኢሳያስንና ሌሎችን ወደ ጀብሃ ጎራ የላኳቸው። ነገር ግን አቶ ኢሳያስና ባልንጀሮቻቸው በዚያው ሰምጠው ቀሩና ሻዕቢያን መስርተው እንዸሆ ለኢትዮጵያ ጠላት ሁነዋል። ወገኖቻችን ናችሁ ብለን ስንሞት ኑረናል ለወደፊቱ ኤርትራውያንን እስላሞች ቢያጠቋቸው ከሮማ ወታደር መጥቶ ይርዳቸው እንጂ በእኔ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘምቶ መሞት ቀርቶ በኤርትራ ምክንያት ውሃ እንኳን እንዲጠማው አልፈልግም። ወገናችን ናቸው ባሉን ወቅትማ የኢትዮጵያ ንብረት በኤርትራ ምድር ፈሷል። ስለዚህ በእኔ እምነት አሰብንና አፋርን የኤርትራን ሕዝብ ለይቼ ነው የማያቸው።

ኤርትራንና አሰብ አስተዳደርን በተመለከተ ልዩነት አላቸው። ኤርትራውያን እኛ ወገኖቻችን ናችሁ ስንላቸው እነሱ አይደለነም ብለው ወግተውናል። የአሰብ አስተዳደር ወገኖቻችን አፋሮች ግን እንኳን ሰው ግመሉ የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ያፈቅራል የሚሉ ወገኖቻችን የአፋርን ሕዝብ ለመርዳት መጣሩን አምንበታለሁ። የአፋር ሕዝብ ወገኔ ያለውን መርዳት ትተን እንዴት ኤርትራውያንን ወገኖቻችን አይደላችሁም ያሉትን ለማገዝ እንስለፋለን? እኔ በበኩሌ የማውቃቸው ኤርትራውያን ባልንጀሮቼን የማያቸው እንደማንኛውም የሰው ልጅ እንጂ እነሱ ዛሬ ከወያኔ ጋር ተጣልተው ወያኔን በመጥላቱ የሆዴን አውጥቼ አልነግራቸውም። የማወጋቸው ሌላ ለላውን ነው። ስለዚህ ከዚህ መጽሐፍ፡ ሳይም ቢሆን እምነቴ ኤርትራ ወደድነም ጠላነም አገር ሁናለች። የተባበሩት መንግሥታት 184ኛ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት 53ኛ አገር መሆንዋን ባምንም ቅሉ ወገኔ የሚለኝን የአሰብ አስተዳደር የአፋርን ሕዝብ ግን ከኤርትራ ሕዝብ ለይቼ ማየት እንዳለብኝ አምናለሁ። ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፈወርቅ ከጀብሃ ተለይተው የራሳቸውን ድርጅት ከመሰረቱ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ተናግረው አያውቁም። እንዲያውም በ1983 ዓም ኤርትራን ከመቆጣጠራቸው በፊት አውሮፓ ውስጥ የተናገሩት "ለኢትዮጵያ የ100 ዓመት የቤት ስራ ሰጥጫታለሁ" ብለው ነበር። የኢትዮጵያን ሕዝብ

አንድ ሁኖ እንዲኖር አይፈልጉም:: ከወያኔ ጋር በ1990 ዓም ከተጣሉ ወዲህ ደግሞ አፍቃሬ አማራ ሁነው መጥተዋል:: ዛሬ የኢትዮጵያ ጥቅም ሲቀርባቸው ደግሞ በአውሮፓና በአሜሪካ የሚኖሩትን ግለሰቦች በጎሳ ስም እየሰበሰቡ ማደራጀታቸው እየታወቀ "አንዲት ኢትዮጵያ" የሚል መጽሔት አውጥተዋል:: ከኤርትራ ጋዜጠኞች ጋር ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ ያደረጉትን ቃለ መጠየቅ በሶስት ቋንቋ ተጽፎ በቅንጅት ወቅት የሞቱትን ኢትዮጵያውያን ሥዕል ይዞ የወጣው መጽሔት ያነበበ በትክክል እውነት መስሎት የእርሳቸው አሽከር እንደሚሆን ግልጽ ነው::

ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ ሓንቲ አንዲት (ዋን ኢትዮጵያ) በተባለው መጽሔት 2000 ዓም ገጽ 3 " ክፍፍሉን ምክንያት ለማድረግ ሕገ-መንግሥት ነው:: ሕዝብን በብሔር ብሔረሰብ ከፋፍሎ በክልል መወሰን ከዚያ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም:: እውነት ነው:: በብሔር ብሔረሰቦች የነበሩና አሁንም ያሉ ናቸው:: ብሔረሰቦችን በክልል ደረጃ ለይቶ በማደራጀት ሕዝብን መከፋፈል የታየው ግን በወያኔ ስርዓት ነው" ሲሉ ተናግረዋል:: ይህ ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፍወርቅ የተናገሩት ትክክለኛ ነው:: ነገር ግን ይህን መመሪያ ነድፈው የሰጡ እርሳቸው ናቸው:: በእርግጥ ሌላም እውነተኛ ታሪክ ተናግረዋል ገጽ 2 "ወያኔ መጀመሪያውኑ ትግራይን ነፃ አወጣለሁ የሚል ፕሮግራም ይዞ የተነሳ ነው:: ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ፕሮግራም ነበረው ወይም መላዋን ኢትዮጵያ የሚመለከት አጀንዳ ይዞ የተነሳ ነው ሊባል አይችልም:: ይህንን ታሪክም የሚረሳው አይደለም" ሲሉ ተናግረዋል:: ትክክል ነው:: ወያኔን በመጀመሪያ መክረውና አደራጅተው ከአረብ አገር የመጣላቸውን ስጦታ ችረው አደራጅተዋል:: ነገር ግን ወያኔ ለሪፓፐሊክ መንግሥት ምስረታ ሳይሆን ለብሔር ነፃነት እንዲታገል ዓላማውን እንዲቀይር ማድረጋቸው አይካድም ይህን ወያኔዎችም አልካዱም ያምናሉ::

<u>የህወሓት ኮሚኒስት ሃይል የ10 ዓመት ጉዞ ግምገማ</u> ሐምሌ 1977 ዓም ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 22 "የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ይባል የነበረው ድርጅት የትግራይ ጥያቄ የብሔር ጥያቄ ሳይሆን የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው:: መንገሻ ስዩም የትግራይን ሕዝብ ትግል ሊመራ ይችላል የሚል አቋም ይዞ በቀረበበት ወቅትም መንገሻ የትግራይ ሕዝብ ጠላት እንጂ መሪ ሊሆን አይችልም ጥያቄውም የብሔር ጥያቄ እንጂ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አይደለም ብሎ ተቃውሟል:: የተጠቀሱት ስህተቶች በ1969 ዓም መጀመሪያ አካባቢ ተሻሽሎ በወጣው የህወሓት ፕሮግራም በመሰረቱ ታርሟል" ሲል ጽፏል:: ሕዝቡን በብሔር ማደራጀት የሚባለውን ግን የመከሩ አቶ ኢሳያስ ናቸው:: የተነደፈውን ሕገ መንግሥት በመጀመሪያ ጥሩ ነው ብለው ተናግረው ነበር:: ይህ ሕገ መንግሥት የፀደቀው ሚያዝያ 25 ቀን 1986 ዓም ሲሆን ጥር በ1987 ዓም አሜሪካ መጥተው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን የሚወክል ሕገ መንግሥት ተመስርቷል ብለው ደግፈው ተናግረው ነበር:: ነገር ግን በግንቦት 1990 ዓም ደግሞ ሳረብ አገሮች የሰጡት ቃለ ምልልስ ተመልከቼ በወቅቱ የማያፍሩ ከተስካር እንዝፈን አሉ በሚል ጹሑፍ በሳተናው ጋዜጣ ታትሟል::



ጌታቸው ረዳ <u>ዜጋ መጽሔት</u> ስስተኛ ዓመት ቁጥር 8 ሰኔ 1994 ዓም ገጽ 6 " የኢትዮጵያን መበተን እያወሩ በታኞችን አያስጎምጁ:: ለአንድነት ኃይሎችም ስለመበተንዋ መርዶ እየነገሩ የሚጫወቱትን የማስፈራራት ጨዋታ አሽብር ዳርጌን ተው አቁም በሉት እንዳሉት አያቱ እኔም አቁም! ልበልዎት? ይህች ትበተናለች ትፈርሳለች የምትባል ቃል ለብዙ ዓመት ከአፍዎ አልጠፋ አለችምሳ? የጤና ይሆን? በእኛ በኩል ኤርትራ ትምጣ ትሂድ ጭንቀታችንን ዱሮ ጥለነዋል:: ሕዝባችን ናችሁ ስንላቸው ባዕዳን እና ጎረቤታሞች ነን ይሉናል! የወደብ የይገባናል ጥያቄ ስናቀርብ ደግሞ መሬቷን እንጂ እኛን ሕዝቦቿን አይፈልጉነም እያሉ ይከሱናል:: መጨበጫ መያዣ ስላጣንባቸው የኤርትራ መምጣትና መሂድ ከእንግዲህ ወዲህ ባጭር አማርኛ ጭንቀታችን አይደለም:: ቢፈልጉ ደግሞ ÷አይዋኒንና÷ በዓድዋ ትግርኛ ቁርጦን ይወቁ ማለት ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን ምዕራፍ ከመዝጋቴ በፊት አንድ ነገር ጣል ሳደርግ እፈልጋለሁ:: በምጽፈው መጽሐፍ ሁሌም ቢሆን የትጥቅ ትግል መጥላቴና በተለይም ከሻዕቢያ ጋር የሚደረገውን መረዳዳት አልደግፍም:: ብታምኑም ባታምኑ ሻዕቢያ ለወያኔ ያልሆነ ለሌሎች በተለይም "አድገ" አህያ ሲለው ለነበረው ለአማራው ሕዝብ ሊሆን አይችልም:: አስታውሱ በ1965 ዓም የኢሕአፓ የመጀመሪያው ከአረብ አገር ሰልጥኖ የገባው በሻዕቢያ ሜዳ ነበር:: ሻዕቢያ ኢሕአፓን የጠየቀው "ኤርትራ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው በል" ብሎ ነበር:: ኢሕአፓም አለስት ይህን በመቀበሉ ምክንያት ግማሾች ተበሳጭተው አዲስ አበባ የገቡ መሆናቸውን አቶ ተስፋዬ መኮንን ይድረስ ለባለ ታሪኩ በተባለው መጽሐፍ ጽፈውታል:: ውለው አድረው ሻዕቢያ ደግሞ ወያኔን መስርቷል:: ከዚያም በወያኔ ኢሕአፓን አስመትቶ ወያኔን የእርሱ የጥይት ማብረጃ አድርጓል:: ኢሕአፓ ከሁለት ሲከፈል ኢዴህን መስርተው እነ አቶ ጌታቸውና አቶ ታምራት ሳይኔ የወያኔ የጥይት ማብረጃ ሁነዋል:: እንደዚያ ተደርጎ ደርግ ወድቆ ወያኔ በገባው ቃል ኪዳን መሰረት ኤርትራን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የሰጣቸውን ጠልቶ ሌሎችን በተለይም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ እምነት ያላቸውን ድርጅቶች ይደግፋል ማለት ዘበት ነው:: ለሻዕቢያ ከወያኔ የሚሻለው ፈጽሞ ሊኖር አይችልም:: ስለዚህ ከሻዕቢያ ጋር ተጠግቶ ሕዝብን ማስጨረስ ትክክል አይደለም ብያለሁ:: እኔ ይህን በማለቴ አንዳንዶች ጠላት ነህ ተብዬ ልፈረጅ አይገባም::

# ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ 1

## የኢትዮጵያ ታሪክ ከፍጥረት እስከ ልደት

ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ለመጻፍ ስጀምር የኢትዮጵያን ረጅም ታሪክ ነካክቼ ነው ወደ የመጽሐፉ መነሻ የምደርሰው። ሁሌም ተመሳሳይ መልዕክት አስተላልፋለሁ። ኢትዮጵያ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምራ ያለች አገር መሆንዋን ማሳሰብ ደስ ይለኛል። ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ሚሊዮን ዓመታት እድሜ ያስቆጠረች አገር ናት። የሀገራችን ታሪክ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጀምሮ አሁን ካለንበት ለመድረስ የበቃችው በአባቶቻችን ቆራጥነት ነው።

(ቀደሰ) ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ ሁሉም ሁሉን ይወቅ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 13“ የሰው ዘር የተፈጠረው መጀመሪያ በኢትዮጵያ እንጂ የዚያን ጊዜም ሰው እንደሚያምነው በኢየሩሳሌም እስያ አይደለምና በዓባይ ሸለቆና በእየቆላው ይፈለግ ብል የቂል መሣቂያ ሁኘ ለብዙ ቀን ቆየሁ። ይህ በተነገረ ከ30 ዓመት በኋላ ሉሲ ተገኘች። ዐባይን ሸለቆ ግን ከመሪዎች ብዙዎቹ ስለማይወዱት እስካሁን አጥኝ ቡድን ባለመላኩ ቀኑን እንደኔ ትብኒቱን ይቆጥራል። የግብጽን መንግሥት የመሠረቱት ጠቢባንም ያስተማሩ ኢትዮጵያዊያን ናቸው በሚል ርዕስ ተነሥቼ ለመተግበር ከዛሬ 22 ዓመት በፊት የውጭ ርዳታ ጠይቄ ከዩንቨርስቲህ ድጋፍ ካገኘህ እንረዳሃለን የሚል መልስ በማግኘቴ የኛን ዩንቨርስቲ ብጠይቅ መሪዎች በቅናትና በጥመት ተጠምደው የድጋፍ ደብዳቤ ባለመጻፋቸው ሳላረጋግጠው አረጀሁ” ሲሉ በ1987 ዓም ጽፈዋል።

ኢትዮጵያ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምራ ያለች አገር ናት። ኢትዮጵያ ዓለም ከተፈጠረ ጀምራ ያለች አገር አይደለችም የምትሉ ካላችሁ እኛ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያውያን የተጻፈን ማመን ከተቸገርን ፈረንጆች ወደው ሳይሆን የታሪክ ሐቅ አስገድዷቸው ሊበድቁት ያልቻሉት ድንቅነሽ ሉሲ በዓለም ከተጠራቀመው የሰው ልጅ አጽም ግንባር ቀደም መሆንዋን መስክረዋል። አሁን በቅርቡም በኢትዮጵያዊው ከርሰ ምድር ተመራማሪ ሰላም ከእርሷ የሚልቅ አጽም ተገኝቷል። ይህን ማመን ካቃታችሁ ውሃ ፈሳሽ ነው ቢባሉ ውሃ አይፈስም የሚሉ ነጩን ጥቁር ጥቁሩን ነጭ የሚሉ ሰዎችን ማሳመን አይቻልምና ልባችሁን አምላክ መልሶ በታሪካችሁ የምትኮሩ ያድርጋችሁ እላለሁ።

የሰው ዘር ከኢትዮጵያ ወደ ኤስያ እስራኤል በከብት እርባታና በሌላ ሁኔታ ተስፋፍቷል። ሰሙቲክ ቋንቋ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ የመጣ አስመስለው



አንዳንድ የታሪክ ሰዎች ሲጽፉ ኑረዋል። ነገር ግን በቅርቡ በብልጽግና በሳይንስ ጥናት የተደገፈ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ጀምሮ በጥቂት ኢትዮጵያውያን የተጻፈው ትክክለኛ ታሪክ በመሆኑ መጻፍ ይቻላል። ሊቀ ጠበብት ማርቆን በርገር ብላክ አቴና በተባለው መጽሐፋቸው ሰሙቲክ ቋንቋ ከአፍሪካ ከኢትዮጵያ ጣና ላይ ተነስቶ በዓለም መሰራጩቱን ጽፈዋል። የጥቂት ኢትዮጵያውያን የታሪክ መጽሐፍ ውድቅ አልሆነም። በአረብ አገር ከግድብ ላይ የተገኘው ጹሑፍ ፊደል ቅርጽ ኢትዮጵያውያን የጻፉት እንጂ ሌሎች የጻፉት አይደለም። ዛሬ ሰልጥነናል የሚሉት ሕዝቦች ገና ቅጠል ለብሰው በሚሔዱበት ወቅት ኢትዮጵያ ስለ ሥልጣኔ ሕዝብ ዲሞካራሲ ታውቅ ነበር።

ለምሳሌ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ለ100 መቶ ዓመታት በተከታታይ 10 ዓመት ብቻ መንገሳቸው ለምን እንደሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪዎች ሳይተነትኑበት መቅረታቸው ይገርማል። የአክሱሙን ታሪክ እንለፈው ከተባለ ከ912 ዓም እስከ 1261 ዓም የነበረው የዛጉዌ ነገሥታት የላሊበላውን ታሪክ በምንመረምርበት ወቅት 40 ዓመት ሲሞላው አጤ ሥልጣኑን አስረክቦ ይሔዳል የሚለውን ለምን የኢትዮጵያ የታሪክ ተመራማሪዎች ሳያጤኑት ቀሩ? የኢትዮጵያ ታሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት ብዙ ጥበብ የነበረበት የሃይማኖት ግንዱ የተመሰረተበት ነበር። ለምሳሌ ከሙሴ በፊት እምነት በኢትዮጵያ ነበር ይህ ማለት በሕገ አበው “እኛን የፈጠረ አንድ አምላክ አለ” ብለው ያመልኩ ነበር። በዚህ ወቅት ካህን ራጉኤል ወይም ዮቶር የሚለውን ያጤኗል።

ኦሪት ዘጸአት ም/3ቁ 1“እንሆ ሙሴ የምድያም ካህን የሆነውን የዐማቹን የዮቶርን በጎች ይጠብቅ ነበር” ይልና ም/ ዘጸአት ም/ 18/ቁ 1 “የምድያም ካህን የሆነው የሙሴ ዓማት ዮቶር እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር መርቶ ባወጣቸው ጊዜ ለሙሴና ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገላቸውን ነገር ሁሉ ሰማ ስለዚህም በእርሱ ዘንድ ትቶአት ሂዶ የነበረችውን የሙሴን ሚስት ሴፓራን እንዲሁም ከሙሴ የተወለዱትን ጌርሽምና ኤሊዓዘር የተባሉትን ሁለቱን ልጆችውን ይዞለት መጣ” ይልና ሙሴ በፍርድ ሥራ አልችል ብሎ ስለተመለከተው እንዴት ዳኞችን መምረጥ እንዳለበት መክሮት ከስራ ላይ ያዋለው መሆኑን ከገለፀ በኋላ ደግሞ ኦሪት ዘኀልቁ ም/12 ቁ /1“ሙሴ ከኩሽ ነገድ የሆነች ኢትዮጵያዊት ሴት በማግባቱ ምክንያት ሚርያምና አሮን በሐሜት” የነቀፉት መሆናቸውን ጽፏል። ከላይ ዘጸአት ም/3ቁ1 ላይ የምድያም ካሕን የሚለው ምድያም የምትባለው በጎጃም ክፍለ ሀገር አገው ምድር አውራጃ ናት።

ዶ/ር ኃይሌ ወልደሚካኤል አብረኖት በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 3 “የአባይ ሸለቆ የዓባይ ወንዝ ውጤት ነው። የዓባይ ሸለቆም የመጀመሪያው ጉልህ ማኅበራዊ ህይወት የተደራጀበት፤ የተፈጥሮ ክስተቶች ግንዛቤ ያገኙበትን የሰው ልጅ ጉልህ የሃይማኖት፤የፖለቲካ ፤የኢኮኒሚ፤የሥነ ምግባርና የሳይንስ ሥርዓትና ሚስጥር የለየበትና በየፈርጁ ያደራጀበት ነው። መደበኛ ግብርና ማለትም ከብት ማርባት፤ አዝርዕት መዝራት፤ የመገልገያና የማመምረቻ መሣሪያዎች ማምረት አልባሳት መሥራት ከብቶችን በወተት፤ በሥጋ፤ በትራንስፖርትና በእርሻ ምንጭነት መጠቀም በመስኖ እርሻ መገልገል በውሃ

መጓጓዝ በአንድ አምላክ ማምለክ የጽሑፍ ባህል ማመንጨት የሃይማኖት ካህናት ማፍራት አስከሬን ማቆየት የጂኦሜትሪን ሳይንስ ማዳበር ወዘተ የተመሰረተበት ሁሉ ብልጫታዎች መጀመሪያ የታዩት በዓባይ ሸለቆ ውስጥ ነው:: በሌላ አነጋገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ በተናጠል ሳይሆን በተደራጀ መልክ ከተፈጥሮ ጋር በውል የታገለበትና በኋላም የሰው ልጅ ከራሱ ጋር መታገል የጀመረበት በዓባይ ሸለቆ አካባቢ መሆኑ ተረጋግጧል" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ ሊሆን የቻለው ኖኅ ከመርከብ የወጣውም በኢትዮጵያ ነው::

መምሕር ፍስሐ ጽዮን ካሣ፣ መርኖ አዳም ወግዕዝ አዳምና ግዕዝ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 59 "ኖኅ ከነልጆቹ ከመርከብ ከወጣ በኋላ የተቀመጠው በምድረ ኢትዮጵያ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: አንባቢያን አንዳንዱ አዲስ ታሪክ አንድ ሰው ደጋግሞ ሲጽፍ ልብ ወለድ መስሎ አንዳንድ ሰዎች ሊቀበሉት አይችሉ ይሆናል:: ታሪክ በታሪክነቱ ካየነው ግን ይዘገያል እንጅ እውነቱ መውጣቱ አይቀርም:: ስለዚህ ኖኅ ከመርከብ የወጣው በኢትዮጵያ መሆኑ ብዙት ያላቸው የታሪክ መጽሐፍት ዘግበውታል::

ያሬድ ግርማ ኃይሌ የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 124 "ኖህ ለዘመናት እንደቆዬ ሚስቱ እሜቴ አይከል ስትሞትበት በጭልጋ ምድር እንደቀበራት ትውፊታዊና ሌሎች መረጃዎች ኖህም ከሚስቱ ተለይቶ ከኖረ በኋላ በጎንደር ከተማ ሲሞት በመቃብሩ ላይ ምንጭ ፈልቆ በርካታ ሰዎችን ይፈውስ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: እኚህ ደራሲ አራራት የሚባለው ተራራ ያለው ዘጌ አውራጃ ውስጥ መሆኑንና ተራራውን የጎበኙ መሆናቸውን ጽፈዋል:: ቁርክ ያለው ተራራ በዓለም ካሉት 26ኛ መሆኑንና ኖህ ከመርከብ የወጣው በኢትዮጵያ መሆኑን አስረግጠው ጽፈዋል:: ባይገርማችሁ ሌላም ታሪክ ልጥቀስ ያም የኖህ መርከብና የጎንደር ፋሲል ግንብ አሰራር አንድ አይነት መሆኑን ሳይቀር ጽፈዋል:: አንዳንድ አባቶችና አፈ ታሪኩ ደግሞ በጎጃም አገው ምድር አውራጃና በዘጌ አውራጃ ጎንደርን አልፎ ዋልድባ ድረስ የሃይማኖት መመስረቻ አድርገው ይቆጥሩታል:: ለምሳሌ የሃይማኖት መምህራን ይህን ታሪክ ጠንክር አድርገው እያስተማሩ ናቸው::

ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀድሽ በ1997 ዓም ታህሳስ 29 ቀን ጎንደር አደባባ ኢየሱስ/ ባለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሲያስተምሩ "የጎንደር ጃንተከል ዋርካውና የፋሲል ግንብ ግምጃ ቤት ማርያም ቤት አደባባይ ኢየሱስ አሰራሩ ጌታችን በተወለደበት በናዝሬት ይመስላል" ሲሉ አስተምረዋል:: በሃይማኖት መምህራን በኩል እንዲህ እያስተማሩ ነው:: ወደ ነበርኩበት ልመለስና ይህ ከሆነ ጀምሮ የሰው ዘር ከላይ እንደተጠቀሰው በታሪክ የአባይ ዙሪያ መነሻቸው መሆኑ ታውቋል:: ከተማቸው ሜርዊ ይባል ነበር:: ይህም ዛሬ ገሉ ያልተገኘበት ሲሆን ይህ ከተማ ከ74 ነገሥታት መካከል በተለይም ከ50ኛው ነገሥታት ጀምሮ በከፍተኛ እውቀት የሞላበት ነበር::

ዛሬ ሜርዌ አልያም ሜርዊ ሌላም ሌላ እየተባለ የሚጠራው ረጅም ዘመን የነበረው ከተማ እንደነበር ተረስቶ ከ880 ዓመተ ዓለም ጀምሮ በተመሰረተው



በአክሱም ከተማ ብቻ ተወስነን የቀድሞውን ታሪክ ለማወቅ ጥረት አልተደረገም:: ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል ሲነግሱ ከዘውዳቸው ላይ የዘንዶ ምልክት ያደርጉ ነበር:: የሩቁን ትተን የቅርቡን ታሪክ ስንመረምር ከንግሥት ሳባ በፊት በኢትዮጵያ የነገሡት 73 ሲሆኑ እርሳቸው 74 መሆናቸውን ሁነዱ ሲያስረዳ እርሳቸው ሲነግሡ ዘውዳቸው የዘንዶ ምልክት ያለው ነበር::

ታዲያ ኢትዮጵያውያን እምነት ስለነበራቸው የዓለም መድኃኒት ጌታ የሚወለደው በእስራኤል መሆኑን ይነገራቸው ስለነበር እርሳቸው በ1013 ዓመተ ዓለም ነግሠው ሳል በሀገሪቱ እንቱ የተባሉ ነጋድራስ ታምሪን በቻይናና በሕንድ ንግዱን ሲነግዱ ኑረው ሲመለሱ በእስራኤል በኩል በመመለሳቸው የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ ተመልክቶ በመምጣቱ ብልህ ንጉሥ ተወልዷል ብሎ ሲነግራቸው ሲያድጉ የሰሙት የዓለም ጌታ መስሎአቸው ብዛት ያላቸው ንጉሦችና ንግሥቶች አስከትለው በ1010 ዓመተ ዓለም እስራኤል ሄዱ:: ከዚያም የዓለም መድኃኒት መሆኑን በእንቆቅልሽ ጥያቄ አዋክበውት አለመሆኑን አሳምነዋል:: ታዲያ ሴት መሆን አይቀርም እርሳቸውም ንግሥት ሳሆየም ሁለቱም አርግዘው ተመለሱ::

ንግሥተ ሳባ እብነለሐኪም የኋላውን ምኒልክ ሲወልዱ ንግሥት ሳሆየ ዛጉዌን ወልደዋል:: ሁለቱም ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ወደ ኢየሩሳሌም አባታቸውን ሊጠይቁ ሔደው እብነ ለሐኪም የቤተ መንግሥቱን ሲማሩ ዛጉዌ ደግሞ የቤተ መቅደሱን ትምህርት ተምረው 12 ሺህ እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን ጽላተ ሙሴን በመያዝ ወደ ኢትዮጵያ መጡ:: እብነ ለሐኪም ቀዳማዊ አጤ ምኒልክ ተብሎ 75 ንጉሥ ነገሥት ሁነው በኢትዮጵያ ሲነግሡ "እንደ አባቴ እንጂ እንደናቴ አልነግሥም" ብለው ከዘውዳቸው ላይ የአንበሳ ምስል ማድረጅ የተጀመረው በ982 ዓምተ ዓለም ወዲህ ነው:: በሃይማኖት በኩል ይህን ሲመስል አገር በማስተዳደር በኩል ደግሞ ጠንካራና አይበገሬ ጀግኖች ነበሩ:: በትምህርት እድገት ያላቸዉ ቢሆኑ ኑሮ ከ70 መርከብ በላይ የነበራቸው ነጋድራስ ታምሬ በዓለም ላይ እየዞሩ የሚነግዱ ሀብታም አይሆኑም ነበር:: ስለዚህ ኢትዮጵያ ጠንካራና ሀብታም አገር ነበረች::

## ምዕራፍ 2

## የኢትዮጵያ ታሪክ ከክርስቶስ ልደት እስከ እስልምና ምስረታ

ታህሳስ 29 ቀን 1 ዓም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ናዝሬት ሲወለድ በኢትዮጵያ ነግሰው የነበሩት እጨ ባዜን ናቸው:: በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያን "የአይሁድ ንጉስ የተወለደው ወዴት ነው" እያሉ የእጅ መንሻ ይዘው ወደ እስራኤል አምርተዋል:: እነዚህ የጌታችን መወለድ እውቀው ኮከቡን እየተከተሉ የሄዱት ኢትዮጵያውያን ከ4 ቦታ የተነሱ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ዛሬ ባለው የጎሳ አባቶች መሆናቸውን የታሪክ ሠነዱ ዋቢ ነው:: ቀደም ሲል በግዕዝ የተጻፉ ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍት ነበሩ:: እነዚህ መጽሐፍት ምናልባት በድርቡሽ ጦርነት ወቅት ወደ ሱዳን የተወሰዱ ይመስላል:: እነዚህን መጽሐፍት ሱዳን አግኝተው ወደ አማርኛ እየተረጎሙ እያሳተሟቸው ነው:: ሱዳን ውስጥ የተገኙትን መጽሐፍት ዛሬ ባለቤታቸው መሪ ራስ ኤ ኤም አማን በላይ ናቸው:: እኒህ አባት ቀደም ሲል በኢትዮጵያውያን የተጻፉትን መጽሐፍት "እንጌ እንደጻፈው" እያሉ እያሳተሙአቸው ነው::

መሪራስ አማን በላይ <u>ጉግሣ መጽሔት</u> 3ኛ ዓመት ቁጥር 1 ሐምሌ 1993 ዓም ገጽ 29 "እጨ ባዜን በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ በነገሡ በ8ኛው ዘመን መስራቅ በኩል ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ ኮከብ ወጣ:: መስቀለኛም የሆነ በሩቅ እግርና እጁን ዘርግቶ የቆመ ሰው የመሰለ ነበረ:: ብርሃኑ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ሰሜን መስዕ ያመለክት ነበር:: ይህ ኮከብ ለኢትዮጵያውያን የጌታን መወለድ ያበሰረ:: 1ኛ በዚህን ጊዜ በደሸት ከተማ ጎንጅ ጎጃም የሚቀመጠው በተስፋ ሲጠባበቅ የነበረው አጎሻ ጃቦን ዮጵ የሚባለውን የግዮን ብጫ ወርቅ እንቁዮጳዝዮን እንቁዮጳ ግዮን የሚባለውን ሉል ድንጋይ የወርቅ ሐመልማል ማለት ወርቁን እንደሰፌድ ሆኖ የተሰራውን ይዞ በሰሩ ሶስት ንጉሶችን አስከትሎ ከጣና ደሴት ተነስቶ ኮከቡ ወደሚያመለክትበት ምድር ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: አጊሻ ሻቦ አማናቱ ሲማር አማራ ጎግ 2ኛ ከአናርያ ዙባ ከተማ የሚቀመጠው የመደባይ ጎግ የደንጊና የሰገል የማጂና የአርመን ንጉሥ መጋል ከኤውላጥ ንጉሥ መካድሺ ከአቢል ንጉሥ እውር ከአፋር አፍሪካ ንጉሥ ሙርኖ ጋር ሆኖ ከወርቅ ሐመልማል የተሰራ መጎናፀፊያ እጀጠባብ የሰንደል እንጨትና እጣን ከርቤም የከበረውን ሉል ወርቅ ይዞ ኮከቡ ወደሚያመለክተው ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም በጥንቱ ናግራ ኤደን በዛሬው የመን አድርጎ ጉዞውን ቀጠለ:: የገዳዲ ልጅ ሰፋ የአሮሞ ጎግ::"

"3ኛ ከዋይዝ ከተማ በተርሴስ ደሴት በዛሬው አፋር የሚቀመጠው የአዜባውያን አዛል-አዳል የአፍርሴካውያን ንጉሥ አጋቦን በኢንአ ጌዜር ከአውባው ንጉሥ ሳዱንያ ሀጂሶን ባል ሜሌክ ኢቡል ሰላም ከሳባ ከተማ



የሚቀመጠው አርስጣ ጋር ሆነው ወርቅና እጣን ከርቤም ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም ቀይ ባሕርን ተሻግረው በምስራቅ በኩል ወጥቶ ብርሃኑ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገውን ኮከብ አይተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: አፈርስካ አፈርስካውያን የሆኑ እነዚህ ንጉሦች ሁሉም የንጉሥ ዘውድ የደፉ ናቸው:: ለእነዚህ ለአስራ ሁለቱ ንጉሦች የበላያቸው በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አክሱም የሚቀመጠው ንጉሠ ነገሥት እጨ ባዜን ነው:: እነዚህ ንጉሦች በግመሎቻቸውና በፈረሶቻቸው ከምድራቸው የእህልና የወርቅ የከርቤና የእጣን አይነቶችና ልዩ ልዩ ልብሶች ገፀ በረከቶች ይዘው የንጋቱ ኮከብ ብርሃኑን ለሚያመለክታቸው የሠላም ንጉሥ ጋዳ ገፀ በረከት ለማቅረብ ጉዞ ቀጠሉ" ሲሉ ጽፈዋል:: ከዚህ በላይ በታሪክነታቸው ከተጻፉት ጥቅስ ተወስዷል:: ይህን የሚደግፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይኖር ይሆን?

<u>መዝሙረ ዳዊት</u> ምዕራፍ 72፥9 "በፊቱም ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ፤የተርሰሴና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን አበርክተው ይሰግዱለታል" ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ስጦታ የሚያበረክቱ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ልብ አምላክ ዳዊት ተናግሯል:: ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ ኢትዮጵያውያን ቀደም ጀምረው በህገ አበው አንድ አምላክ አለ ብለው ያመልኩ ስለነበር ነው:: ለዚህም ነው <u>ትንቢተ አሞጽ</u> 9፥7 "የእሥራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም" ብሎ ሊናገር የቻለው እንደዛሬው ትውልድ ሳይሆን የዱሮ አባቶቻችን አምላክን ያከብሩ በመሆናቸው ነው:: በማቴዎስ ወንጌል 2፥2 "የከዋክብት ተመራማሪዎች ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ" ይላል:: ምንም ይሁን ምን ለኢየሩሳሌም ምስራቅ ኢትዮጵያ እንጂ ሌላ አገር ሊሆን አይችልም:: ስለዚህ ሰብዓ ሰገል ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን በሚመለከት ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስና ከዚህ በታች ስማቸውን የምጠቅሰው የታሪክ መጽሐፍት ዋቢ ናቸው::

1ኛ መሰረተ ስብሀት ለአብ ትውፊታዊ ሐሳብ ዘመንና ታሪክ ገጽ 36
2ኛ ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም ክርስትና በኢትዮጵያ ገጽ 52
3ኛ ቃለ አዋዲ መጽሔት ቁጥር 2 ሚያዝያ 1990 ዓም ገጽ 5

<u>የማቴ 2</u>፥ 13 "የከዋክብት ተመራማሪዎች ከሄዱ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገለጦ ሄድሮስ ሕጻኑን ለመግደል ስለሚፈልገው ተነስና ሕጻኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ ግብጽ አገር ሽሽ እስከምነግርህም ድረስ በዚህ ቆይ አለው" የተባለው ይደርስ ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈ ነበር:: እመቤታችን ድንግል ማርያምና ዮሴፍ መቅደላዊት ማርያም ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል:: የነበሩበትም በዛሬው ጣና ውስጥ ነበር:: ቀደም ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ በትንቢት ተጽፎ ነበር:: ለምሳሌ <u>መዝሙረ ዳዊት</u> 68፥ 31 "የሰላም መልእክተኞች ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያም ፈጥና እጆቻችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የተባለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያ መምጣቱን ሲያብራራ ነው::

አዋልድ መጽሐፍት የምንላቸውም ይህን ጠቅሰውታል።አቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ከድንግል ማርያም ተወልደህ ሄሮድስ ሊገልህ በፈለገህ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደህ በጣና ደሴት ለዓራት ዓመት ስትኖር ኢትዮጵያን ባርከህ በጎንህ የፈሰሰውን ደምና ውሃ በሊቀ መልአኩ በቅዱስ ዑራኤል አማካኝነት በሀገሪተቷ ላይ ረጭተህ ተራሮቿን ባርከህ ወንዞቿዋን ቀድሰህ የእህል በረከት ይውረድላት ወተትና ማር የሚፈስባት አገር ትሁን ብለህ ኢትዮጵያን ለእናትህ ለማርያም ዓሥራት አድርጌ ሰጠሁሽ ስትል ቃል ኪዳን የገባህላትን አስበህ በደላችንን ይቅር ብለህ ከረሃብ ከበሽታ ከጦርነት አድነህ ሰላምና ፍቅርን አንድነትን እንድትሰጠን እንለምንሃለን። ዮሴፍ ማርያም እና ሰሎሜ ኢየሱስ ክርስቶስን ይዞ ከሄሮዶስ በሸሹ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው መኖራቸው ከላይ ተገልጿል ኢትዮጵያ የሰው ልጆችን ሳይሆን የዓለም መዳህኒት ጌታችን ያስተናገደች አገር ናት። ከዚህ ከፍ ተብሎ የተብራራው ጌታችን መዳህኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢትዮጵያ መጥቶ መኖሩን በተመለከተ በታሪክ መጽሐፍት ተገልጿል።

1ኛ ዋልድባ በሀገረ እግዚአብሔር አቢሲንያ የአርበንታት ገዳም ታሪክ ገጽ 17
2ኛ አለቃ አያሌው ታምሩ ወላዲት አምላክ በኢትዮጵያ ገጽ 48
3ኛ መራሪስ አማን በላይ መጽሐፈ ሱባኤ ዘበአማን ካልዕ እየሱስ ክርስቶስ በኢትዮጵያ ገጽ 406-411-413
4ኛ መምህር አለማየሁ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሃ ገጽ 18
5ኛ ዘመድኩን በቀለ ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ ገጽ 22

ክርስትና ሃይማኖት ማለትም ጥምቀት በኢትዮጵያ ያስተማረ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት አስተምረዋል። በኢትዮጵያ የመጡት ሐዋርያትም 6 መሆናቸውን የታሪክ መጽሐፍት ዋቢ ናቸው። ይህን የምዘረዝረው አንባቢያን እንዳይጠራጠሩ በታሪካቸው እንዲኮሩ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የምጠቅሳቸው የታሪክ መጽሐፍት ሐዋርያት በኢትዮጵያ መጥተው ማስተማራቸውን የሚገጸውን ይሆናል።

1ኛ አምበር መስቀልየ በዲበ መስቀል፤መስቀሌን በመስቀለኛ ላይ አኑር ገጽ 64
2ኛ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት ከመጀመሪያው እትም ገጽ 86 ከሁለተኛው እትም ገጽ 108
3ኛ አባ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 21
4ኛ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ትምህርተ ክርስትና ገጽ 149
5ኛ የኔሰው አስረሴ ትቤ አክሱም ሙኑ አንተ ገጽ 67
6ኛ አባ ተሥፋ ስላሴ ሞገስ ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የይሁዳ አንበሣ ነው ገጽ 100
7ኛ መምሕር ቸሬ አበበ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽናት 1 መጽሐፍ ገጽ 96

ለምሳሌ አንዳንድ የበስማም ቂሶችና የአውሮፓ ሰዎች ክርስትና ሃይማኖት የተሰበከው በውጭ ሰዎች አስመስለው ይጽፋሉ። ነገር ግን ትክክል አይደለም። ክርስትና ሃይማኖት የተሰበከው ቅድሚያ ጌታችን የኢየሱስ በኢትዮጵያ



በኢትዮጵያ መጥቶ በማስተማሩ ነው። ለምሳሌ ሌሎችን የክርስቲያን ሊቅ ነን ባዮችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከ12 ዓመቱ 18 ዓመቱ የት እንደነበረ ብትጠይቋቸው መልስ የላቸውም። ኢትዮጵያውያን ግን መልሳቸው በኢትዮጵያ እየተዘዋወር እያስተማረ ነበር ይላሉ። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሰ በኋላ በጆርንድ ጃንደረባው ባኮስ ግንቦት 8 ቀን 34 ዓም በዓለም ከተሰበሰቡት ሕዝቦች መካከል በጴጥሮስ የተሰበከውን ትምህርት ተቀብሎ በሠረገላ ሲሄድ ሳለ መንፈስ ቅዱስ በፍሊጶስ አድሮ ጃንደረባውን እንዲያነጋግረው ከላከው በኋላ ተጠምቆ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ ጀምሮ ክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ማስተማር ጀመረ።

1ኛ መጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 26-33
2ኛ ዘመድኩን በቀለ ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ ገጽ 4

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መጽሐፍት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ብዛት ያላቸው መጽሐፍት መጥቀስ ይቻላል። ከዚያም በኋላ ጃንደረባው ባስተማረው ትምህርት ሕዝቡ ገብቶት በ330 ዓም ወዲህ የመንግሥት ሃይማኖት ሁኖ ታወጀ። በሃይማኖት በኩል እንዲህ ሲል በአስተዳደር በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰችበት ወቅት ነበር። የዛሬው ትውልድ በዓይን የሚታይ ቅርስ ሰላማና ነበር የሚባለው ታሪክ ልብ ወለድ መስሎ ስለሚታየው እንጂ ኢትዮጵያ በ335 ዓም የሮማው ገዥ አቻ መንግሥት ኢትዮጵያ መሆንዋን አምኖና አክብሮ በአስተዳደር ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት እንኳ አብረን እንተባበር ብሎ ለአጤ አብርሃ ወአጽብሃ የላከው ደብዳቤ ታሪክ መዝግቦት ይገኛል። ክርስቲያኖች ባንድ ባህሪና በሁለት ባህር ትርጉም ጭቅጭቅ በገጠሙበት ወቅት የአይሁድ እማኝ ንጉሥ ፈንሃስ በየመን ይኖሩ የነበሩትን ክርስቲያኖች በማጥፋቱ አጤ ካሌብ መርከባቸውን ጭነው ወደ የመን ዘምተዋል።

ንጉሡ ነገሥት አጤ ካሌብ በየመን የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ከታደጉ በኋላ የፈረሱ ቤተ ክርስቲያኖችን አድሰዋል። ከዚያም ደጃዝማች አብርሃ ንጉሡ የመን ብለው ሹመው አጤ ካሌብ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መንግሥታቸውን ለልጃቸው ሰጥተው ገዳም ገብተዋል። የመን የነበሩት ንጉሥ አብርሃ በ570 ዓም ወደ መካ ዘመቻ ማድረግ ጀመሩ። በዚህ ዘመን ነቢዩ ሙሐመድ የተወለዱ ተብሎም ተጽፏል። ንጉሥ አብርሃ መካ ደርሰው በጣዖት የሚያመልከውን ሕዝብ ክርስትና ሳያስተምሩ ሙተው ቀርተዋል። ወታደራቸው ከሞት የተረፈው ሳውዲ ዓረቢያ ገብቶ መኖር ጀመረ። ለምሳሌ የእስልምና ሃይማኖት መስራቹን ጡት አጥብተው ያሳደጉት እሙሃይመን አል አበሽ ወይም ደግሞ በረከቱል አል ሐበሺንና ሌሎችን መጥቀስ ይቻላል። እስልምና ሃይማኖት ሲመሰረት የመጀመሪያውን አላህ አክብር ያሉት በላይ ገብረ እግዚአብሔር ቢላል ሌሎችም የአረብ ሰደተኞችን እየመሩ ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን ዛሬ ድረስ በአረብ አገር ቅይጥ ሁነው የቀሩትን ጥቁር ኢትዮጵያውያን በዚያን ወቅት ከሞት የተረፉት ናቸው።

# ምዕራፍ 3

## ከእስልምና ምስረታ እስከ ንግሥት ዩዲት!

<u>ቅዱስ ቁርአን</u> መቅድሙ ገጽ 7 "ኢትዮጵያ ልጆቿን በመካከላቸው ልዩነት ሳታደርግ አፍቅራና አስተባብራ ከመኖሯ በላይ እንግዶችንም ቢኾን በአክብሮት ተቀብላ የምታስተናግድ አገር መኾኗ የታወቀ ነው:: ነቢዩ ሙሐመድ በ610 ዓ.ል በተነሱ ጊዜ ነገዶቻቸው ተከታዮቹን ስለአሠቃዩዋቸው ሐበሻ (ኢትዮጵያ)የእውነት አገር ናት በውስጧም ሰውን የማይበድል እርሱም ዘንድ አንድም የማይበድል ንጉሥ አለና ወደዚያ ብትኼዱ መልካም ነው:: "በማለታቸው በመጀመሪያ በ615 ዓ.ል.የነቢዩ ሴት ልጅና ኸሊፋው ዑስማን የአጎታቸው ልጅ ጃዕፈር የሚገኙበት 16 ስደተኞች ዳግመኛም ከመቶ በላይ የሚኾኑ የሃይማኖት ጥገኞች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው 15 ዓመት በመልካም ጥገኝነት ተቀምጠዋል::

ጠላቶቻቸውም ስደተኞች ተይዘው እጃቸው እንዲመለስላቸው ቢጠይቁ ንጉሡ ገንዘብ ያላጠፋ፤ነብስ ያልገደሉ መኾናቸውን አጣርቶ አሳልፎ አልሰጥም በማለቱ ጥገኝን አሳልፎ ያለመስጠት ሕግ ከኢትዮጵያ ንጉሥ ተጀመረ፤ እንደሚባል ነቢዩ ሙሐመድም ለተከታዮቻቸው ሐበሾችን ኢትዮጵያውያኖችን ካልወኰዋችሁ አትውጓቸው ማለታቸው ይነገራል:: ንጉሡም ድርብ ምንዳ ያለው ጻድቅ ንጉሥ መኾኑ በቁርኣን በ3ም 199 አንቀጽ 28 .52-54 አንቀጽ ተገልጿል" ይላል::

ሐጂ ሙሐመድ ሣኒ ሐቢብ <u>እስልምና እና የታላቁ ነቢይ የሙሐመድ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 47 "ቁረይሾች ያመኑትን ሰዎች መጨቆንና ማሰቃየታቸው እየቀጠለ ስለ ሄደ በተለይ ጠንካራ ወገን በሌላቸው ሰዎች ከፍ ያለ ችግር ደረሰባቸው:: በዚህ ጊዜ ነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያ የእውነት ሀገር ናት ንጉሥዋም መልካም ሰው ነው፤ በሱ ዘንድ ማንም ሰው አይበደልምና የአላህ ፈቃድ ሆኖ መከላከያ ኃይል እስከናገኝ ድረስ ወደ እዚህ ሄዳችሁ ጊዜ ብታሳልፉ መልካም ነው:: ስላሏቸው ከነቢይነት ዘመን 5ኛው ዓመት በሽሽግ ወደ ሐበሻ መሰደድ ጀመሩ" ሲሉ ጽፈዋል::

የእስላም ስደተኞች በኢትዮጵያ መጥተው በሰላም መቀመጣቸው በመካ ላሉ ቁረሽዎች ዜናው ደረሳቸው:: በዚህ ወቅት ቁረሽዎች ለንጉሥ አርማህ ብዙ ገጸ በረከት እስይዘው ወደ ኢትዮጵያ ላኩ:: የአጋሜ አውራጃ ንጉሥ ስደተኞችን በባልደረባነት የሚያስተናግዱ ናቸው:: ከመካ ወርቃቸውን ይዘው የመጡት ቁረሽዎች በገንዘብ ገዝተው ለመውሰድ ነበር አሳባቸው ንጉሥ አርማህ ግን ምክንያቱ ምን እንደሆነ ከሳሽና ተከሳሾችን ከአከራከሩ በኋላ "ስደተኞችን አሳልፌ አልሰጥም" በማለት አሳፍረው መለሱአቸው::



ሒራ አሳታሚና አከፋፋይ የግል ማህበር <u>የሐበሻው ሂጅራና ሙሃጂሮች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 36 "ሙሃጂሮቹን ለመውሰድ የመጣው ልዑክ (ቡድን)የቅሌት ማቁን ተከናንቦና ይዞት የመጣውን ገፀ በረከት ተሸክሞ በመጣበት እግሩ ተመልሶ ሔደ:: ከአንድ የተከበረ ወገን ወደ ሌላ የተከበረ ወገን የተላከ ገፀ በረከት መመለስና ተቀባይነት ማጣት በጣም አሳፋሪና ቅስም የሚሰብር ሊሆን ይችላል:: የሐበሻው ሂጅራ ኢስላምንና አዲሱን አመለካከት የተከታዮቹ አገር ከሆነ አካባቢ ውጭ ለማስፋፋትና ለማስተዋወቅ ይልቁንም ለገዥዎችና ለሹማምንቱ ለማስረዳትና ለማሳመን ችሉአል" ሲሉ ጽፈዋል::

ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ <u>የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 199 "ቁረይሾች ማምባር የዘመቱ የሀበሻ ወታደሮችን ቁጥር በሚመለከት በኡሁዱ ጦርነት 3000 በኸንደቁ ጦርነት ደግሞ 10000 ነበር" ይሉና "ሀበሾችና የመካ ወታደራዊ ድርጅት በሂጅራ ዘመን በሚል ርዕስ በ1916 ባዘጋጀው ጹሑፍ የመካ አዋማዊ ቁረይሾቾችን ወደ ሽንፈትና ውድቀት ያደረሱት አሀበሾች የተባሉ ኢትዮጵያዊ ወታደሮች ናቸው በማለት ጽፎአል" ሲሉ ጽፈዋል::

የኢትዮጵያ ልጆች የዕስላም ሃይማኖት መስራቾች ሲደበደቡ ትክክል አይደለም በማለት በመንግሥት ታዘው ሳይሆን በፈቃዳቸው ዘምተዋል:: የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ለእስልምና ሃይማኖት እድገት ያደረጉት ጥረት ተክዶ እንሆ ዛሬ ወንድሞቻችን እኛን ክርስቲያኖችን እየገደሉን ነው:: እስልምና ሃይማኖት ትክክል ትርጉሙ የተረዳው ምዕመን ከሆነ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ ጦርነት ማንሳት ፈጽሞ አይችልም:: ምክንያቱም የነቢያቸው ትዕዛዝ "ኢትዮጵያውያንን ካልወጓችሁ አትውጓቸው" በማለት አስተምረዋል:: ለምሳሌ ይህ ወንድሙን ማጥፋት ተግባር መቅረት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ራሳቸው ሙስሊም ወንድሞቻችን ማስተማር ይገባቸዋል::

አህመድ ሙነወር ሰይድ ኢብራሂም <u>የእስልምና ድንጋጌ የአመጣጥ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 102 "አላህ ሙስሊሞቹን ፀሎታዊ ስግደቶችን እንዲያከናውኑ፤ ዘካትን (አስራትን) እንዲያበረክቱ፤ ሐጂን እንዲያደርጉ፤ ውሉችን እንዲያከብሩና እንዲፈጽሟቸው ሰውን ያለአግባብ እንዳይገድሉ ጥቃትን እንዲከላከሉ እነኚህንና የመሳሰሉትን ደንግጓል" ሲሉ ጽፈዋል::

አንባቢያን ብተለይም እስላም ወንድሞቼ "ሰውን ያለአግባብ እንዳይገድሉ ጥቃትን እንዲከላከሉ" የሚለው ሕግ ምንን ያመለክታል? ቅዱስ ቁርዓንን ደግሜ ደጋግሜ አነበብኩት ነገር ግን "ሰው ግደል ትጸድቃለህ" የሚል ተጽሉ አላነበብኩም:: በሀገራችን በአንዳንድ አካባቢ ወንዶች አንበሳ ካልገደሉ ወንዶች የማይባሉ ይመስላቸዋል:: ገዳማቱ ቤተ ክርስቲያኑ እየተቃጠለ ነው:: ባንድ ሳምንት 4 ታላላቅ ገዳማት ተቃጥለዋል:: ይህ ሁሉ ድፍረት ግን መልካም አይደለም::

ዲ/ን ናትናኤል ታምራት እግዚአብሔር ለምን ዝም አለ? በተባለው መጣጥፋቸው ከገጽ 12-19 የጻፉትን አቤቱታ ሳነብ ከልብ አዘንኩ:: ይህን የእርሳቸውን ጹሑፍ ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመልከቱ:: ሌላው በጎርጎርዮስ አቆጣጠር ጥር 12 ቀን 2008 የተቀረፀ ዲቪዲ ተመለከትኩ:: የሰው ልጅ እንደ በግ በአንገቱ መታረድ ይገባዋል ወይ? እነዚህ ክርስቲያን ወገኖቻችሁ መሆናቸውን እንዴት ረሳችሁ? ኧረ መልካም ጅምር አይደለም? በኢትዮጵያ ታሪክ ክርስቲያንና እስላም አብሮ በሰላም የኖረበት መሆኑን ነው ተጽፎ ያነበብነው? አክራሪዎች ለክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን ለእስላም አማኞችም የሚተኙ አይደሉም:: የፓኪስታን ሆነ የሌሎችን የእስላም አገሮች እልቂት በአክራሪውና ሰላም ፈላጊው ሕዝብ መካከል እያለቀ ያለውን ማስተዋል ይጠይቃል::

ዘማሪት ፀዳለ ጎበዜ አቤቱ የሆነብንን አስብ በተባለው የመዝሙር ዲቪዲ ያቀረቡት ክር ላይ የሚያሳዩት ሥእሉ ክርስቲያኖች በእስላሞች የተገደሉ መሆናቸውን ሲሆን የክርስቲያኖች ቤታቸው ሆነ ቤተ ክርስቲያኑ የተቃጠለውን እያሳዩ ለእግዚአብሔር ይዘምራሉ:: ክርስቲያኑ የእምነታችን አንዱ መፈተኛ በመሆኑ ወደ እግዚአብሔር አንጋጦ በማልቀስ ላይ በመሆኑ ደስ ሊላችሁ አይገባም:: ይህ በጣም ድፍረት መልካም አይደለም:: የሚገርመኝ አንድ ነገር አለ:: ያም ሰው ካልገደላችሁ አትጠድቁም" የሚል ሃይማኖት መኖሩን አላውቅም:: ከቅዱስ ቁርዓን ላይ አልተጻፈም::

ታዲያ የት አመጣችሁት? ሰው መግደልን ደስ የሚለው ሠይጣን እንጂ እግዚአብሔርን አምናለሁ የሚል ሰው አለ ብዬ አላምንም:: የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (አርቶዶክስ) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በአክራሪ እስላሞች እየተደበደቡ ነው:: በእርግጥ የኢትዮጵያ እስላሞች ሁሉም ይህን እኩይ ድርጊት ይደግፋሉ ማለት አይደለም:: ከዚህ የሚከተለውን ሰነድ ስጽፍ አለፍ አለፍ እያልኩ የጥቅስ ምልክቱን እያስገባሁ ባንድ ሰብስብ አድርጌ አገለብጠዋለሁ::

ኢትኦጵ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 057 ሚያዝያ 1996 ዓም ገጽ 36 "አበሻ የእውነት ምድር ነች" ነቢዩ መሐመድ" ይላል እርስቱ ደግሞ ኒውስ እርስቱ "ኢትዮጵያዊያን እስላሞች እንጂ በኢትዮጵያ የምንገኝ እስላሞች አይደለነም" ይላል:: ልክ ናቸው ወያኔዎችና አንዳንድና አክራሪዎች ጠብ ለማፍለቅ ስለፈለጉ "በኢትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች" እያሉ ያወሩ ስለነበር እነዚህ መርዞች ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ኢትዮጵያውያን እስላሞች" በሚለው አስተካክለው ጽፈዋል:: "በአክሱም ጽዮን አካባቢ መስጊድ ካልሰራችሁ ብሉ ያካባቢውን እስልምና ተከታይ ዜጎችን ወጥሮ ቢይዛቸውም ካልጠፋ መሬትና ቦታ ምነው እዚህ ላይ ስሩ እንባላለን ለጥላቻና ለቅራኔ እንጋበዛለን በማለት እንቢታውን ገልጿል" ይሉና::

"በሀገር ቤት በዲሞክራሲና በነፃ መንቀሳቀስን አሳቦ የጊዜው አገራዊ እንገብጋቢ የፖለቲካ ጥያቄ የአዳዲስ ሃይማኖቶችና እምነቶች ማነስ ይመስል



በሃይማኖት ስም ለሚንቀሳቀሱና ፍቃድ ለጠየቁ የውጭ ድርጅቶች አሳንዳች ገደብ በሩን በርግዶ ከፍቷል:: እነዚህም ድርጅቶች አሳንዳች ጠያቂ እንደልብ በመላው የሀገሪቷ ግዛቶች ይንቀሳቀሳሉ:: ያሻቸውን ራዕይና እምነት ይሰብካሉ፣ ያስፋፋሉ:: ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው ሕዝቡ ለመጤዎቹ ያለውን ንቀት ባሳየና እንቢታውን ገልጦ ጆሮ አልሰጥ ባለ ቁጥር በመንግሥት ባለሥልጣናት የሚደርስበት መዋከብ ቀላል አይደለም:: ይባስ ብለውም ሰባኪዎቹ የመንግሥትን ባለስልጣናት በሙስና በማጥመድ በሚጠሩት ስብሰባ በግድ እንዲገኙ ያስገድዱታል" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ጥቅስ የተወሰደበትን የጻፉት ሰብሰብ ብለው መሆናቸው የስማቸው ብዛት ይገልጻል::

ሙዳይ መጽሔት ሰኔ 1985 ዓም ከጅቡቲ ሁነው የኢትዮጵያ እስላሞች ለኢትዮጵያ የክርስቲያን አባቶች መለያየትን በተመለከተ የጻፉትን ጹሑፍ በጥሞና ሳስተዋለው የዛሬዎችን ከይሲዮች ዘመር ብለን እንዳናይ ያደርገናል:: ይህን በሰኔ 1985 ዓም የጻፉትን ጹሁፍ ቀንጭቤ ከማቀርበው ይልቅ ሙሉውን ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመልከቱ:: ይህን አንብበው የዛሬዎን ደግሞ አጢኑ::

በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ እስላሞች ከኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ጋር ችግር እንዲፈጠር ያደረገ የወያኔ መንግሥት መሆኑን ከላይ የተነበበው ጥቅስ ያስረዳል:: ለዚህም ነው ነባሩ የኢትዮጵያ እስላሞች ይህን እኩይ ድርጊት አይደግፉም ያልኩት:: ከዚህ በፊት በምጽፋቸው መጽሐፍት እስልምና ሃይማኖት ከመስራቹ እስከ አማኙ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ደግፎት ከዚህ የደረሰ መሆኑን በታሪክ ሠነድ አስደግፌ ስጽፍ እባካችሁ በክርስቲያኖች ላይ ክፉት አታስቡ የሚለውን አልተውኩም:: ዛሬም ቢሆን እባካችሁ ማለቴን አልተውም:: ነገም ከነገ ወዲያም ጌታችን መዳኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቂምን መያዝ እንደሌለብን አስተምሮናል ይህን እርሱ ያስተማረውን ትምህርት በመያዝ ስንደበደብ አልቅሰን ዝብ ብለናል::

ትንቢተ ሚክያስ 7+2 "ደግ ሰው ከምድር ጠፍቶአል:: በሰውም መካከል ቅን የለም፤ሁሉ ደምን ለማፍሰስ ያደባሉ፤ሰውም ሁሉ ወንድሙን በመረብ ለመያዝ ይከታተላል እጆቻቸውን ለክፋት ያነሳሉ" ሲል ጽፏል:: በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ መንግሥትና የክርስቲያኖች ጠባቂ ነን ባዮች የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ዝም ማለቱ ነው::

"ክርስቲያን መሳይ አባቱን ገዳይ ይድረስ ለጳጳሳት"ትገርማላችሁ የምትጠብቁት ምዕመን ሲደበደብ ለፀሎት ምዕመናኑን ጠርታችሁ እግዚአብሔር ይማራችሁ ሳትሉ መቅረታችሁ በእናንተም ላይ አንድ ቀን ፍርድ መምጣቱ አይቀርም! በእርግጥ እኛ በዓይናችን ልናይ አንችል ይሆናል ነገር ግን እናንተ ከፉ ረኞች በታሪክና በእግዚአብሔር ፍርድ ማግኘታችሁ አይቀርም:: ለሩቅ ምስራቅ ሕዝብ እልቂት የኢትዮጵያን ምዕመናንን ለፀሎት የጠራችሁ ስትሆኑ እንጠብቀዋለን የምትሉትን መንጋ ሲታረድ ግን ድምጻችሁ ጠፍቷል::

ዲያቆን በጋሻው ደሳለኝ የመስቀሉ ስር ቁማርተኞች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 61" ከዓመት በፊት ጃፓኖች ሱናሚ በሚሉት የኀርፍ መጥለቅለቅ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዓላማችን 260.000 ዜጎቿን ስታጣ በእርስዎ ትዕዛዝ ለሞቱት ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ጸሎት እንደተደረገላቸው የምናስታውሰው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው:: ዛሬ ግን ለገዛ ወገንዎ የጸሎትን ቸርነት መከልከልዎ መላውን ኢትዮጵያዊ ከልብ መጉዳቱ ብቻ ሳይሆን የሚሰሩት ስራ ሁሉ ለጽድቅና ለበረከት ሳይሆን ለታይታ መሆኑን ያመለክተ ነጸብራቅ ነው:: ግድያውን ባይቃወሙ እንኳን ስቆቃና ሀዘን የከበደውን ኢትዮጵያዊ እህት ወንድም እናት አባት የሞተበትን መከረኛ ሕዝብ ለማፅናናት መቼ ብቅ አሉ? መስቀልን እኮ ማክበር የሚቻለው እንደ ክርስቶስ ለሕዝብ እየሞቱ እንጅ በሽቶ የሰከረ ነጫጭ ቀሚስ እያጠለቁ አይደለም" ሲሉ ጽፈዋል::

በ2001 ዓም ላይ እስላም ወንድማችን አዲስ አበባ ላይ አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ሲሰግድ ተይዟል:: እንዲሁም የካ ሚካኤል ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ አላህ አክብር ብሎ ሲሰግድ ተይዟል:: ጎንደርም እንዲሁ ጥምቀተ ባህሩ ላይ ችግር መነሳቱና በሀረርም እንዲሁ ብጥብጥ ተነስቶ ነበር:: ይህ በውነቱ መጥፎ ጅምር አይደለም:: እስላም ወንድሞቻችን ከዚህ በፊት በአንድነት ተፋቅረን አብረን መኖራችን ታሪክ የዘገበው ሲሆን ዛሬ ግን በአንዳንድ አክራሪ ምክንያት ሰላም እየጠፋ ነው:: ስለዚህ አስቡበት የወያኔ መንግሥት ለራሱ ሥልጣን መሰንበቻ ሲል የማይፈነቅለው ድንጊያ የለም:: ይህ የእርሱ ሴራ ከሆነ ራሳችሁን ነፃ አድርጉ እንጂ አትውቀሱ:: ወያኔ ከዚህ በፊት ይዞት የተነሳው ካርድ ሁሉ ተቃጥሎበታል የቀረችው ይች በሃይማኖት ጉዳይ ሕዝቡን ማጋጨት መሆኑ ግልጽ ሲሆን ይህን ተጠቅመው አንዳንድ አክራሪዎች ሕዝብ መፍጀታቸውን እንዲያቆሙ ጥረት ማድረጉ የግራ ቀኙ የሃይማኖት መሪዎች ጉዳይ ይሆናል::

ይህ ከሆነ በኋላ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ወጣቶች ሰብስበው ግራና ቀኙን የሃይማኖት አጥባቂዮች ነቅፈዋል:: በክርስቲያኑ በኩል የተናገሩት ቃል አግባብ አይደለም "አንዳንድ ደብተሮች የክርስትና ደሴት ናት የሚሉት" ሲሉ ታሪክም አትናገሩ ማለታቸው ነው:: ኢትዮጵያ የእምነት ደሴት ናት ያሉት አንዳንድ ደብተሮች ከማንም ፀሎት ቤት ገብተው ሰው አልገደሉም:: ሰው እንደበግ አላረዱም:: ይህ እግዚአብሔር ለምን ዝም አለን? የተባለው መጣጥፍ ሆነ ድቪዲዩ የሚያሳየው ክርስቲያኖች በገጀራ መታረዳቸውን ነው:: ይህ ደግሞ ወንጀል ነው:: ከዚህ ዝቅ ብሎ የሚነበበው ታሪክ የሚያሳየው ሥዕላቸው የታረዱ ሰዎች ሲሆን ከዚህ መጽሐፍ ላይ ሲወጣ በደንብ ሁኖ አይታይም:: ይህን ካልኩ በኋላ ደግሞ ከዚሁ ቀጥሎ ያለው እስላም ወንድሞቻችን በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ላይ እርስ በርዕስ የደረሰውን ችግር በመቃወም ጅቡቲ ሁነው የጻፉትን ያሳያል:: ስለዚህም ነው ሁሉን እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መቀየም የሌብንም የምለው::



## ክፍል ሦስት

## አዲሱ በእስልምና ስም የሚንቀሳቀሰው ኃይል በቤተክርስቲያናችን ላይ ያደረሰው ጥቃት

### 1.አዲስ አበባ

እስላማዊው ኃይል በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ላይ ላደረጓቸው እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ነጥቦች ማሳያ ናቸው::

- በ1996 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አራት ኪሎ እና ስድስት ኪሎ ተጀምሮ የቆመው የመስጊድ ግንባታ
- በሐምሌ 1998 ዓ.ም አራት ኪሎ በሚገኘው ንቡረዕድ አድማሱ ለአዲስ ዓለም ማርያም ያወረሱትን ቦታ ለመውሰድ የተደረገው ጥረት ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተካሔዱ ሰልፎችና ግርግሮች
- በጥምቀተ ባሕር ቦታዎች ላይ የሚቀርበው የመስጊድ ግንባታ ጥያቄ፣
- የአየር ጤና ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን በጥምቀት ባህ ሯ መውጫ ላይ መስጊድ እንዳይሰራ የታገለችው ትግል በዚሁም ሳቢያ የተነሳው ንጭት ፣
- በአዳዲስ ሰፈሮች ላይ የሚካሔደው የመስጊድ ግንባታ ፣
- ከ 139 በላይ መስጊዶች በቅርብ የተሠሩትን ሳይጨምር ከ79 በላይ በዚህ 14 ዓመት የተሠሩ ናቸው::
- በነሐሴ 7 ቀን 1999 ዓ.ም 7 በማህደረ ስብሐት ልደታ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያደረሱት ብጥብጥ

### 2. ሐረርጌ /ባለምለ/

- መጋቢት 12 ቀን 1998ዓ.ም ማክሰኞ ቀን በገበያ ዕለት ክርስቲያኑን በሙሉ በስድስት ሰዓት ለማጥቃት ተወስነ ተማሪዎቹ በዐራት ሰዓት ጀመሩት ከፌዴራል የሚሰጥ ኃይል ቶሎ እንዳይደርስ መንገዱን በትላልቅ ዛፍ እና ድንጋይ ዘግተው ሕዝበ ክርስቲያኑን፣ ንብረቱን ማቃጠል እና መደብደብ ሲጀምሩ በረዶ የቀላቀለ ዝናብ [illegible]



- በዚሁ ወቅት ህዝበ ክርስቲያኑን ስመባረክ መጥተው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ኢዎስጣቴዎስ የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ሲመለሱ በተፈጠረው ችግር ምክንያት በቁኒ ወረዳ እና በቦኬ ወረዳ በሚገኘው በጣራ ቁራ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የነበረው ፕሮግራማቸው መስተጓጎሉ::

### 3. አርሲ ሲጋ /ቆራ እንሻ/

- ጥቅምት 24 ቀን ከኢድ አል ፈጥር በዓል መልስ "ክርስቲያኖች ጠላታችን ናችሁ አንገታችሁን እንቆርጣለን" እያሉ በአይሱዙ ተጭነው መፈክር ሲያሰሙ ዋሉ::
- በዚሁ ዕለት ክርስቲያኖችን ደብድበው ቤታቸውን አፍርሰው ጥቂቶቹን በጩቤ ወግተው ጉዳት ቢያደርሱም መስተዳድሩ ለቀረበለት ጥያቄ በሽማግሌ ፍቱት ከሚል የዘለለ መልስ አልሰጠም::
- ኅዳር 7 እና 8/1998 ዓ.ም / አሏህ ወአክበር" በሚል የእንሻ ቅድስት ማርያምን ቤተክርስቲያን አቃጠሉ፣ የ72 አባወራ ክርስቲያኖች ቤቶችን አቃጠሉ፣ ከዚያም ብዙዎችን ገደሉ፣ አፈናቀሉ"

### 4. ባሌ

- በወሰሉ፣ ቡልቻ ሰርዳ፣ ቀበሌዎች 60 መስጊዶች የተሠራባቸው አካባቢዎች አሉ:: በዚህ ሀገር ላይ የኦርቶዶክሣዊት ቤተክርስቲያን ግንባታ ጠይቃ ተከልክላለች::
- በአንድ ቀን 18 የኦርቶዶስ እማኝ የገበሬ ክምሮች ተቃጥለዋል::
- ከገጠር ክርስቲያኖች ይፈናቀላሉ ፣ አብያተ ክርስቲያናት ይቃጠ

## . ወሎ

- ወሎ መካነ ሰላም በሚባው ወረዳ እጅግ ብዛት ያላቸው መስጊዶች በአንድ ባለሀብት ልገሰና ተሰርተዋል::
- በከሚሴና ባቲ በ1998 ዓ.ም በተምቀት በዓል ላይ ግጭት ፈጥረዋል።
- ብዙ መድረሳዎች (የቁርአን) ት/ቤቶች ተሠርተዋል።
- ከሚሴ ሀገረ ስብከቱ ፊት ለፊት መስጊድ ለመገንባት ክርክር ላይ ናቸው:: እስካሁንም ይህ ነገር አዘል ጥያቄዎቻቸው መፍትሄ አላገኘ ም::
- በ1998 ዓ.ም ደሴ ቁራናችን ሸንትቤት ተገኘብን በሚል ሰበብ በደሴ ሲኒማ አዳራሽ ውስጥ ህዝብን ሰብስበው መንግስት መፍትሔ ካልሰጠን ሀገርን ከሚረብሹ አሸባሪዎች ጎን እንሰለፋለን እያሉ ንፁሁን የእስልምና ማህበረሰብ ሲያነሳሱ ነበር።

## . ጎንደር

የአበራ ጊዮርጊስንና የበዓታ ለማርያም የጸበል ቦታዎችን የደገበኛል ያቄ በማትረብ ክፉዩ በኋላ አንድ አልሞት ባይ ተጋዳይ ግለሰብ በፈጸመው ኔታ ተነሣሥተው በ4/10/98/

1. የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የእስላም ወረዳ ይባል፣
2. በክርስቲያን መዝታችን ይብቃ፣
3. ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ለምን ትባላለች?
4. ግራኝ መሐመድ ያረፈበት ቦታ ላይ ሐውልታችን ሲሰበር መንግስት ድጋፍ አላደረገልንም
5. ለምን በክርስቲያን ስም እንጠራለን የሚሉ ነጥቦችን ለዞኑ መስተዳድር አቅርበዋል።

ሌቀ ... አሁን እንድርያስ በተገኙበት እና የዞን መስተዳድር ላይ



- ከምስት ያላነሱ «የወታደር» ማሠልጠኛዎች ተገኝተዋል።
- በ18/10/98 የጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ለማቃጠል ሲንቀሳቀሱ ፖሊስ ቀሃ ወንዝ ላይ መልሰአቸዋል።
- በ20/10/98 ዓ.ም ኑር ዓሊ በሚባል ሹፌር በከባድ መኪና ከነተሳቢው የተመረዘ ሰይፍ ሲገባ ተጠቆሞ ሳይያዝ ቢቀርም በ23 ሸረሩ ቀጥጥር ሥር ውሎአል:: ከሥርጭት የተረፈው 63 ሰይፍ መስጊድ ውስጥ ሲገኝ ከ 24-26 በተደረገ ፍተሻ 111 ሰይፍ ተገኝቷል።
- በ27/10/98 መኪታር ሳህል ጅብሪል የተባለ እስላም የሚያጠቃበትን ካርታ አነስተኛ ካሜራና የእጅ ሰምብ ይዞ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገዳማ በሲቀ ሲታውንት ዕገራ ላይ ጥቃት ለመፈጸም ሲል ከመንበረ መንግሥት መድኃኒዓለም ግቢ በፖሊስ ተይዟል።
- የጥንቶቹ ሽማግሌ እስላሞች በሁኔታው ተደናግጠው ከዚህ ውጭ ነን በማለት ጥቆማ አኪሒደው የጦር ማሠልጠኛቻቸውን ጠቁመዋል።

## በማሠልጠኛው ከተገኙት ነገሮች መካከል

- ፋክስ፣ኢንተርኔት፣
- የአራቱ ጉባኤያት መምህራንና የደቀ መዛሙርቶቹ ስም ዝርዝር ለተለያዩ እስላማዊ መንግሥታት ፋክስ የተደረገበት ቀና ቀናዎቹ ናቸው።
- የቁልጋው አጥማቂ መነኩሴና የአባ ጊዮርጊስ ዲያቆን ተደብድበዋል።

ፅጉሜ ላይ የታሰሩት ይፈቱ በሚል ሰላማዊ ሰልፍ ሊያካሄዱ ሲሞክሩ ከመንግስት ጋር ተጋጭተዋል ። ለአዲስ አበባው የመስጊድ ግንባታ ጥያቄ በአንድ ቀን ለግደት 29,000 ብር ድጋፍ ተዋጥቷል፡ በሞባይልም ማበረታቻም ይሰጥ ነበር።

## 7. ኢሊባቡር ጅማ

*በ1998 ዓ.ም*

- ክርስቲያን ሴቶች ውሃ መቅዳት አይችሉም ይደፈራሉ።
- ጉልላታቸው ተነሥቶ ጨረቃና ኮከብ የተሰቀለባቸውና ወደ መስጊድነት የተሰወጡ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ቅኔ ማህሌት ውስጥ ሜት ተቀሟል።
- ዲያቆናት ተገደው ሰልመው ቁራን ይማራሉ።

ኤን ሸበ መመም ወም አይችልም::



*1998 ዓ.ም*

ነሐሴ 10 ጀምሮ እስገድዶ የማስለም መርሀ ግብር አውጥተው ነበር።
ከመስከረም 16 1997 ዓ.ም ጀምረው ተገደው ከ 488 በላይ ክርስቲያኖች ሰልመዋል።
ከ 2000 በላይ ተፈናቅለዋል።
ከ350 ቤቶች በላይ ተቃጥለዋል ንብረታቸው ተዘርፈዋል።
ሶስት አብያተ ክርስትያናት ተቃጥለዋል ተዘርፈዋል። ለዚህም ማስረጃ እምነቱ ኢንተርናሽናል ያወጣው መግለጫ ለመጥቀስ ቢያስፈልግም መቀ፣ ጎሬ፣ ያንፋ ማርያምን መጥቀስ ይቻላል።

## . አዋሳ

ሆነ ተብሎ በተቀነባበረ ዘዴ በአንድ የቁራን ብጣሽ ስም ብጥብጥ በማንሳት ምህርት እንዲስተጓጎልና ምንም የማያውቁ ሰዎች እንዲንገላቱ አድርገዋል።

## . ወሊጋ

ምዕራብ ወለጋ ቆንን የምትባል ቦታ ቢያንስ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል። ክርስቲያኖችም በከፍተኛ ፍጥነት በመሰደድ ላይ ናቸው። ይህም የጥፋት ልዑክ የሆኑ የሙስሊም አባላት በሁሉም ቦታ በፍጥነት እየተስፋፉ መሆኑን ያመለክታል።

## . ጅማ /አጋሮ/

ጥቅምት 5 ቀን 1999 ዓ.ም የጻድቁን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ክበረ ዓል ላይ ሊሊት ቤተ ክርስትያኑን በመውረር 8 ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ/ ገጀራና በእሳት ተቃጥለው/ ተገድለዋል። 38 ሰዎች ቆስለዋል ቤተ ርስቲያኑን አቃጥለዋል። ክርስቲያኖችም ሌሊቱን ሙሉ በአካባቢው ወደ ... መሮጥና መሞታቸው የማይታወቅ በእርካታ



**እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን የህይወትን አክሊል**
**እሰጥሀለው ራይ 2:10**



*ጥቅምት 4 ቀን 1999 ዓ.ም. በአጋሮ ወረዳ በበሻሻ ቃት የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዓልን ለማክበር ሄደው የተሰዉ ሰማዕት ወ/ሮ ዓለምነሽ ደበሉ*

« . . . . . . . . . » እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው
ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነፁ
ራይ 7:14



መምሬ ከፍያለው ይግለጡ
ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም. በአጋሮ ወረዳ በበሸሻ ቃት የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዓልን ለማክበር ሄደው የተሰዉ ሰማዕት



**ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ስላንተ ቀኑን ሙሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን**

**ሮሜ/8፤35-36**

## *በሁሉም በታዎች ላይ ያላቸው የጋራ ጥያቄዎቻቸው*

1. ኢትዮጵያ ለምን የክርስቲያን ደሴት ትባላለች? እኛስ ለምን በክርስቲያን ስም እንጠራለን?
2. ኢትዮጵያ የዐረብ ሊግ አባል ለምን አትሆንም ?
3. በታፊር /በክርስቲያን/ ለምን እንገዛለን ?
4. የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛውን እስላም ነው፡፡
5. ከሐረርጌ ፤ ከአርሲ ፤ ከባሌ ፤ ከጅማና ፤ከኢሉባቦር ክርስቲያኖች ከአካባቢያችን ይውጡ፡፡ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ዓ.ም የሚለው ይቅርና እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ይባልልን ዓ.ም. የሚለው የአንድን ሃይማኖት ሀሳብን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በማለት ለጠ/ሚር መለስ ዜናዊ ግልፅ ደብዳቤዎች ጽፈዋል፡፡ ለዚህም ማሳያ ሰለፊያ ጋዜጣ ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም. ያወጣው ጽሁፍ ይመልከቱ፡፡

## *ከስልቶቻቸው መካካል*

- በአለባበሳቸው በዝቶ ለመታየት መጣር
- መተንኮስና አጋጣሚውን መጠቀም
- የመስጊድና የመድረሳዎችን ግንባታ ማስፋፋት
- በዓለም ማህበረሰብ ዘንድ ጭቆና ያለባቸው እስኪመስል ድረስ መጮህ
- ሰሞኑን በዌብ ሳይቶቻቸውና በጋዜጦቻቸው የሚጮሁት ጩኸት እጅግ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ነው፡፡ ሰለፊያ አልቅዱስ ጥቅምት፣ ህዳር 1999 ዓ.ም. የወጡት ጋዜጦች

ከ፲ንቢላ እስከ ሁመራ ለሱዳን መሬት ከተሰጠ ይመጣል መከራ ገጽ

# ከጅቡቲ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች

ይድረስ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያ ን መሪዎች! እኛ የኢትዮጵያን [illegible]

*የተከበራችሁ የቤተክርስቲያን መሪ ዎች!* እርግጥ ነው ስለክርስትና እምነ ት ታሪክ ከናንተ ይበልጥ አናውቅ ም፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያውያን እንደመ ሆናችን የእስልምና እምነት በአገራችን ስለተስፋፋበትና ከክርስቲያን ወንድሞ ቻችን ጋር በመፈቃቀርና በመከባበር፣ በስምምነት በወዳጅነት ስለምንኖርበት ምስጢር የምናውቀው ቁምነገር አለ፡፡ ስለዚህም አንዳንድ ነጥቦችን ልንገልፅ ላችሁ ተገደናል - ከታሪክ እንደምና ውቀው፡፡

የእስልምና ሀይማኖት በመነሻው ወቅት ከባድ ችግርና ፈተና እንዳጋጠ መው ይታወቃል፡፡ ዋናውን ችግር ለመጥቀስ ያህል በተለይም የመላው እስላም ኮሚውኒቲ ከተቋቋመ በኋላ ኡመተል መሀመድ (የመሀመድ ተከታ





## ምዕራፍ 4

## ከንግሥት ዩዲት እስከ ዘመነ መሳፍንት

በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል በሕገ ኦሪት "አንድ አምላክ አለ" ብለው ያመልኩ ነበር:: ኋላ በቀዳማዊ አጤ ምኒልክና በወንድማቸው በዛጉዌ ምኒልክ፤ አማካኝነት አሪት ሃይማኖት በኢትዮጵያ ተሰብኮ ነበር:: ክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ሲሰበክ ግማሾቹ አሪትን አንለቅ ብለው የቀሩ ነበሩ:: እነዚህ የአሪት እማኞች ራሳቸውን አደራጅተው ንጉሥ እስከመሆን ደርሰው ነበር:: በዚህ ወቅት ቤተ መንግሥቱን ወገራ አድርገው ክርስቲያኖችንና አሪት አማኙን በሰላም ወልቃይትን አልፈው ፖርት ሱዳን መደኔ ድረስ የሚያስተዳድር ንጉሥ ጌዲዮን ነበሩ:: እነህ ንጉስ የአሪት አማኝ ነበሩ:: የአክሱም ነገሥታት በራሳቸው ድክመት መውደቅ ስያሳዩ ክላይ የተጠቀሰው የንጉሥ ጌዲዮን ሴት ልጃቸው ክርስቲያኑን መንግሥት ደምስው የአሪትን እምነት ለማስፋፋት ጥረት አደረጉ:: እነህ ንግሥት በተለይ የደመሰሷቸው ከውጭ አገር በስደት መጥተው ገዳም በስማቸው የተሰራውን በተለይ የ9ኙ ቅዱሳን ገዳም ደምስሰዋል:: ሌሎችን ገዳማትም መደምሰሳቸው ታሪክ ነው::

ከ840 ዓም እስከ 882 ዓም ለ42 ዓመታት በውድም በግድም ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል:: በዚህ ወቅት ብዙት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ቅርሳቅርስ ተቃጥለዋል:: ነባሩ መንግሥት ከአክሱም ወደ ሸዋ መንዝ በስደት ሔዱ:: ንግሥት ዮዲት ሲሞቱ መንዝ ተደብቆ የነበረው መንግሥት ተመልሶ አክሱም በመግባት እንደ አባቶቹ አስተዳደር ይዞ ሊቆይ አልቻለም:: በዚህ ወቅት የአጤ ድል ነዓድ ልጅ ሞሰብ ወርቅን በንግርት ያገቡት መራ ተክለ ሃይማኖት መንግሥቱ ነጠቁና ከትግራይ አክሱም ላኮ መልዛ የዛሬው ወሎ ክፍለ ሀገር ሮኃ አዛወሩት:: ከ912 ዓም ጀምሮ ቤተ መንግሥቱን ከትግራይ አክሱም ወሎ ላስታ ከትሞ አገር በማስተዳደር ላይ የነበረው የዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን ሥራ የሰራ ቀላል አይደለም:: ቤተ ክርሥቲያን ከግብጾች ፈልቅቆ ለማውጣት ጥረት ያደረገ መሆኑ የቅዱስ ሐርቤ ታሪክ ሕያው ምስክር ነው::

በቅዱስ ላሊበላ ደብር ሰበካ ጉባኤ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ የተባለው መጽሐፍ "በመጀመሪያ የሠራቸውን ቤተ ማርያም ብሎ ሰየማት በስተኋላዋ የሠራችውን ቤተ መድኃኒዓለም ብሎ ሰየማት:: በስተፊቷ የሠሩትን ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አንዲቷን ደብረ ሲና ብሎ ሰየማት ሁለተኛይቱን ቤተ ጎለጎታ ብሎ ሰየማት:: በስተቀኝ የተሠራችውን ቤተ መስቀል ብሎ ሰየማት፤ በስተግራም የተሰራችውን ቤተ ደናግል ብሎ ሰየማት:: እንደዚህም አድርጎ ሁሉቱን የአማሩ ቤተ ክርስቲያኖችን ስራ ሥራቸውም ልዩ ነው:: የተቃረቡም ናቸው:: ነገር ግን በመካከላቸው ያለ ቅጽር ይለያቸዋል እንጂ ከሊህም ከሁለቱ

፦) በአሰብት አካባቢ አኩዋን ሙስ ሊም (ወንድም እስላሞች) በመባል የ ሀይማኖታችንን ትምህርት በሚገባ እየ ሰፁ የመስገጃ (የመፀለያ) ቦታዎችን የቀረቀሩ የመሀመድን ትልቅ ነቢይ ትና የእስልምናን ሀይማኖት ዕኑነት ማስተማር ዋጅባቸውን (ድርሻቸውን) ሀቃቸውን) እየተወጡ ናቸው። ይሁን ንጂ እነዚህ አኩዋን ሙስሊሞች ስለ ሀይማኖት በሚያስተምሩበት ጊዜ የሰ ውን ሀይማኖት በማንቋሸሽና ምዕመና ውን (ተከታዮቻቸውን) በመናቅ አል በረም። አይደሉምም። ምክንያቱም እ ዲህ ዓይነቱ ድርጊት ሆጥያት (ሀራ ም) መሆኑን ቀድመው ያውቁታልና ምንም ተራ የሀይማኖት ሰባኪ ቢሆ ም።

በሕሰም የእስልምና ታሪክ ውስጥ ዚያ ሥልጣኔ በሌለበት ዘመን ያለግ ታ በሙዴታ ሃይማኖቱን ተቀብሎ ክብርና በኢማኖ የኖረ የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕዝብ መሆኑ በጣም የሚ ስደንቅና ኢትዮጵያውያን ሙስሊም ና ክርስቲያኖች የምንኮራበት ጉዳይ ው። በዚህ ወቅት የነቢ መሀመድ አሊ ወሰላት ወሰላም) ዘመዶችና ሮች ምንም እንኳን የእስልምናን ይማኖት በግድ በሰይፍ ቢቀበሉም ኢትዮጵያ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ግን ሀይማኖቱ ትክክለኛነትና በነብያችን ሙሀባ (ፍቅር) ነበር የተቀበለው ሀይ ማኖቱን። ስለዚህ ከእስም ከሁሉም ላይ ግን ነብያችን ከመጀመሪያው መረቁን እኛን ኢትዮጵያውያኖችን ው። (ባረክ አላሁ ሀበሽ) የሀበሽ ዝብ ይባረክ ብለዋልና ይህ ንግግራ ው ሀይማኖታችን ኢትዮጵያ ውስጥ መስፋፋቱ በፊት ነበር። ለዚህ አባባ ትንና እምነታችን አንድ ከእስላም ፅሐፍ የተገኘ የኢትዮጵያ ታሪክ በ ትሹ በማስረጃነት እንጠቅሳለን። በዚ ቁረሾች የነቢ ተከታዮችን በሚያጠ ብት ዘመን ከእልቂት የተረፉት ሙስሊም ወንድሞቻችንና የነቢ ቤተሰ ች ለነቢ እንዲህ አሉዋቸው ቁረሾች ሲያጠፉን ነው ተከታትለው ልና ወዴት እንግባ» ብለው ጭንቀት ሲጠይቋቸው ነቢም እንዲህ ሰ ሀበሽ ወአርዙን ወይቡን ጋረቡን ... (ሐ.ዱ ሀበሽ ሀገር ... እዚያ መሬት ይ ሆናችሁ ፈጣሪን ብትለምኑ ሰማችኋል) ብለው አሉዋቸው። ሰላም ወንድሞቻችን ወደ ኢትዮጵያ ዘች መጡ (ፀሀ የሆኑ)። በዚያን ጊዜ ነበረው የኢትዮጵያ ንጉስ ነገሥት ክርስቲያን መንግሥት ቢሆንም

በደስታና በክብር ተቀበላቸው። እነሱ ም የመጡበትን ሁኔታና የእስላም ተከታይ መሆናቸውን ገለፁለት። ይኽ ን የሰሙት ቁርሾችም እስከ ኢት ዮጵያ ተከታትለው መጡና «እነኚህ የእስላም ተከታዮች ሀይማኖትህን እንዳይበክሉብህ ስጠንና እናጥፋቸው» በማለት ንጉሡን ለመኑት። ብዙም ገፀ በረከት አቀረቡለት። ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ ንጉስም «ጋራ ሙሉ ወር ቅ ብትሰጡኝ እነኚህን እስላሞች አሳ ልፌ አልሰጣችሁም» አላቸው። ከዚያ ም እስላም ወንድሞቻችን በግዛቱ ሀይ ማኖታቸውን እንዲያስፋፉ ፈቀደላ ቸው።

መሠረቱ ይህ ሆኖ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ወላጆቻችን ምንም እንኳን በሀይማኖት ቢለያዩም እስከ አሁን የቆየ በሀገራችን የሀይ ማኖቶቻችን ባህል በህዝቦች መካከል የአንድነትና የፍቅርን የመከባበርን በጋን ገንብቶአል። እኛ የተለያዩ ሃይ ማኖት የምንከተል የኢትዮጵያ ሕዝ ቦች የአንድ ሃይማኖት ተከታይ ወገን በዓል በሚያከብሩበት ጊዜና ወቅት የሁሉም ሀይማኖት ተከታይ በጋራ በደስታና በፍቅር እያከበርን የምንኖር ከሌላው ዓለም ህዝብ የተለየን ነን። ይህም አንድ ወንድም አንድ ዝርያ በመሆናችንም ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ ክርስቲያን ወንድ ሞቻችን ምዕመናን ላይ የተፈፀመው ቃለ እግዚአብሔር አስነዋሪ በደል ስን ሰማና ስናይ ከልብ የምናዝነውም በዚ ህ የተነሣ ነው። ክርስቲያን ወንድሞ ቻችን የሚሰሙበትና ፈጣሪያቸውን ከሀጢያት ለመንፃት በሀብረት የሚለ ምኑበት ቤተክርስቲያናቸው እየተዘ ጋባቸው ሀይማኖት የሌሽ (ባሆት አምላኪ) ይመረጡ በየመኪና መንገዱና በየሜዳው በመንግሊታታቸው ከልብ እ ስገናኛለን።

እንደ እውነቱ ከሆነ የሀይማኖት መሪ ውና መንግስት በዚህ አስከፊ ዘመን የክርስቲያንነት መብት ከመግፈፍና ምዕ መናንን ከማንከራተት ይልቅ የሀይማኖት መሪው በተሰሙት የሀይማኖት ትምህርት ና መንግሥት ደግሞ ፈጣሪ በሰጠው ስልጣን ተጋግዘው ነባሩን የክርስቲያን ሀይማኖት ማክበር ይገባቸው ነበር። የሀይማኖት መሪው ጳጳስና መንግሥት የክርስቲያን ሀይማኖት ሰባኪ ባህታዊ ከማሰር ይልቅ ማክበርና ማበረታታት ሲገባቸው ይህ አይነት ድርጊት በመደረጉ በጣም ትልቅ ውርደት ነው። ይልቅ ባገኛችሁት የፈጣሪ ስልጣን ተደኪታችሁ ለፈጣሪ ትልቅነት በማስተማር በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን ምዕመናን ጥሩውንና

በጉውን ነገር ከመምከር ይልቅ ህዝቡ ወደመረጠው ጥሩ የፈጣሪ ቤት መንገድ በሚያመራበት ወቅት የፈጣሪን (የአላህን) ቤት መዝጋታችሁና ማዘጋታችሁ አስግቶ ናል፤ አሳዝኖናል። ኃጢአትም ነው። እግ ዚአብሔር የማይወደው። በዚያን ሰዓት ህዝቡ ቤተክርስቲያን ስትዘጉበት አላህ ተብረዱን አውርደው እንጂ ሰው ለሀይማኖቱ ሲል ይሰዋል ይህ ሁሉ ህዝብ አንድ አይነት እንቅስቃሴ ቢጀምር በህዝቡና በታጣቂው መካከል ግጭትና እልቂት ቢፈጠር ማነው ተጠያቂው? ይህ ተግባር እኛን ሙስሊሞችን ከልብ አሳዝ ኖናል። ለላሉ ከላይ እንደገለፅነው የእግዚአብሔርን ቃልና ትምህርት ለክ ርስቲያኑ ህዝብ ከማስረዳትና ከማስተ ማር ይልቅ ለምድራዊ ክብርና ስልጣን ሲሉ የክርስቲያን ሀይማኖት ተከታይ ምዕመናንን ማንገላታት ኃጢአትና ትልቅ ውርደት መሆኑን ቢገነዘቡት እንወዳለን።

እኛ ኢትዮጵያውያን እስላሞች ክርስ ቲያን ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ስን ገላቱብን እንወድም መጥፎም ነገር እንዲደርስባቸው አንፈልግም። ምክንያቱም 1ኛ/ ወንድሞቻችን ደሞቻችን ናቸው። 2ኛ/ ከላይ እንደገለፅነው ለኑመታል መሀመ ድና ለእስልም መስፋፋት ያሳዩት መንፈ ስና በፈፀሙት ክቡር ተግባር ባለው ለታችን ናቸው። የሀይማኖት መሪዎች ግን ለምድራዊ ስልጣንና ክብር ብላችሁ የእግዚአብሔርን ቃል አትጋፉ ይሄ ድር ጊት ደግሞ ሀይማኖትን ማፍረስ ማለት ነው። ሀይማኖት ካለምክንያት አይፈር ስም። ታዲያ ህዝቡ ሀይማኖቱን እየወደደ የሀይማኖት መሪዎች ሀይማኖቱን የሚበ ትኑና የፀሎት ቤቱን የሚዘጉ ከሆነ ተልዕኮ አላቸው አያስኝምን? እናንተ ቢመክሳችሁም የኢትዮጵያ ህዝብ ሀይማ ኖቱን በግድ ስለአፈረሱበትና በቡር ስለአስገደዱት ሌላ ሃይማኖት አይከተ ልም። ከፍላጉት ውጭ በሃይል የማሆን ነገር የለምና። የግድ ነገር ለትንሽ ጊዜ ነው ይላሉ አባቶች ሲተርቱ። በተከበ ረችው አገራችን ጅሰሳም አከራሪዎች ተልዕኮ ያለው ማንኛውም ግለ ሰብ ሆነ ድርጅት ካለ እኛ የኢትዮጵያ እስላሞች እንቃወመዋለን። ቁረአናችንም የሰውን ሀይማኖት እያንቋሸሻችሁና እያፈራረሳችሁ በግድ እስላም አድርጉ አይልምና። ይል ቁንስ ቁርአናችን የሚለው «ለኩም ዲንኩም ወላ የዲን» ነው። ከዚህ ውጭ ግን ሀራም ነው። ስለዚህም የኢትዮጵያ ክርስቲያን ወንድሞቻችን የአገራችን መሪዎችና የአረብ አክራሪዎች በፈጠሩት ሁካታና ቀማታ ምክንያት ሀይማኖታ ችሁን ማናጋት የለባችሁም። ሶብርና ኢማን አላህ ይስጣችሁ። አላህ ከናንተ ጋርም ይሁን አሜን !!

==== ==== ==== ====





## ምዕራፍ 4

## ከንግሥት ዩዲት እስከ ዘመነ መሳፍንት

በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል በሕገ አበው "አንድ አምላክ አለ" ብለው ያመልኩ ነበር። ኋላ በቀዳማዊ አጤ ምኒልክና በወንድማቸው በባጉዌ ምኒልክ፣ አማካኝነት ኦሪት ሃይማኖት በኢትዮጵያ ተሰብኮ ነበር። ክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ሲሰበክ ግማሾቹ ኦሪትን አንለቅ ብለው የቀሩ ነበሩ። እነዚህ የኦሪት እማኞች ራሳቸውን አደራጅተው ንጉሥ እስከመሆን ደርሰው ነበር። በዚህ ወቅት ቤተ መንግሥቱን ወገራ አድርገው ክርስቲያኑንና ኦሪት አማኙን በሰላም ወልቃይትን አልፈው ፖርት ሱዳን መደኔ ድረስ የሚያስተዳድር ንጉሥ ጌዲዮን ነበሩ። እኒህ ንጉስ የኦሪት አማኝ ነበሩ። የአክሱም ነገሥታት በራሳቸው ድክመት መውደቅ ሰያሳዩ ከላይ የተጠቀሰው የንጉሥ ጌዲዮን ሴት ልጃቸው ክርስቲያኑን መንግሥት ደምስው የኦሪትን እምነት ለማስፋፋት ጥረት አደረጉ። እኒህ ንግሥት በተለይ የደመሰሷቸው ከውጭ አገር በስደት መጥተው ገዳም በስማቸው የተሰራውን በተለይ የ9ኙ ቅዱሳን ገዳም ደምስሰዋል። ሌሎችን ገዳማትም መደምሰሳቸው ታሪክ ነው።

በ840 ዓም እስከ 882 ዓም ለ42 ዓመታት በውድም በግድም ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል። በዚህ ወቅት ብዛት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ቅርሳቅርስ ተቃጥለዋል። ነባሩ መንግሥት ከአክሱም ወደ ሸዋ መንዝ በስደት ሔዱ። ንግሥት ዮዲት ሲሞቱ መንዝ ተደብቆ የነበረው መንግሥት ተመልሶ አክሱም በመግባት እንደ አባቶቹ አስተዳደር ይዞ ሊቆይ አልቻለም። በዚህ ወቅት የአጤ ድል ነዓድ ልጅ ሞሰብ ወርቅን በንግርት ያገቡት መራ ተክለ ሃይማኖት መንግሥቱ ነጠቁና ከትግራይ አክሱም ላኮ መልዛ የባሬው ወሎ ክፍለ ሀገር ሮኃ አዛወሩት። ከ912 ዓም ጀምሮ ቤተ መንግሥቱን ከትግራይ አክሱም ወሎ ላስታ ከትሞ አገር በማስተዳደር ላይ የነበረው የባጉዌ ሥርዎ መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን ሥራ የሰራ ቀላል አይደለም። ቤተ ክርሥቲያን ከግብጾች ፈልቅቆ ለማውጣት ጥረት ያደረገ መሆኑ የቅዱስ ሐርቤ ታሪክ ሕያው ምስክር ነው።

በቅዱስ ላሊበላ ደብር ሰበካ ጉባኤ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ የተባለው መጽሐፍ "በመጀመሪያ የሠራችውን ቤተ ማርያም ብሎ ሰየማት በስተኋላዋ የሠራችውን ቤተ መድኃኒዓለም ብሎ ሰየማት። በስተፊቷ የሠሩትን ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አንዷቱን ደብረ ሲና ብሎ ሰየማት ሁለተኛይቱን ቤተ ጎለጎታ ብሎ ሰየማት። በስተቀኝ የተሠራችውን ቤተ መስቀል ብሎ ሰየማት፣ በስተግራም የተሰራችውን ቤተ ድናግል ብሎ ሰየማት። እንደዚህም አድርጎ ሁሉቱን የአማኑ ቤተ ክርስቲያኖችን ሰራ ሥራቸውም ልዩ ነው። የተቃረቡም ናቸው። ነገር ግን በመካከላቸው ያለ ቅጽር ይለያቸዋል እንጂ ከሊህም ከሁለቱ

አንዷቱን ቤተ ገብርኤል ብሎ ሰየማት:: ሁለተኛይቱንም ቤተ አባ ሊባኖስ ብሎ ሰየማት:: እንደዚህ አድርጎ ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አያያዘ:: በቅጽር አንድ አደረጋቸው ሁለተኛም በቅጽር ለያያቸው:: ሁለተኛም ቀጥሎ የሚአስደንቁ ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ሠራ:: ሥራቸው ግን የሁለቱም እየቅል ነው:: ከሊህም አንዷቱን ቤተ ክርስቲያን ቤተ መርቆሬዎስ ብሎ ሰየማት:: እንደዚህ አድርጎ ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት እያያዘ:: ለብቻዋም አንዷቱን ቤተ ክርስቲያን ሠራ:: ሥራዋም ልዩ ነው:: መላእክት እንዳመለከቱት ምድሩን እየለኩለት እንዳሳዩት በትእምርተ መስቀል አስጊጦ ሠራት:: እርሷንም ቤተ ጊዮርጊስ ብሎ ሰየማት:: እንደዚህም አድርጎ አስሩን አብያተ ክርስቲያናት ሰርቶ ፈጸማቸው:: ስራቸውም እየራሱ ነው መልካቸውም እየራሱ ነው" ሲል የቅዱስ ላሊበላ ገድል ከግእዝ ወደ አማርኛ የተተረጎመው ታሪኩን ጽፎታል::

ዶ/ር እያሌው ሲሳይ <u>የአገው ሕዝቦችና የዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 184 "የእነዚህ አብያተ ክርስቲያን የአሠራር ስልትም ሆነ የእያንዳንዳቸው ዝርዝር ሁኔታ ፍጹም የሆነ የኢትዮጵያዊነት ባሕርይ የተላበሰ ለዘመናት ተደጋግመው በተሰሩት የጥንት አክሱም ሥነ ሕንፃ ንድፎች ላይ ምስክርነታቸውን የሚገልጽና የሚታይ ነው:: የላሉበላ 11 አብያተ ክርስቲያን ለዚህ ቀደምት የሥነ ሕንፃ ጥበብ መቀጠልና ሕያው መሆን ግንባር ቀደም ምሳሌዎች ይሁን እንጂ ሌሎችም ተመሳሳይ የሆኑና በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሕንፃዎች በምድረ ኢትዮጵያ ይገኛሉ:: ሌሎች አገሮች እነዚህን የመሰሉ የድንጋዮች ፍልፍል ሕንፃዎች የተነደፉበት የሥነ ሕንፃ ጥበብ ፈጽሞ የላቸውም:: ኢትዮጵያ የድንጋይ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያን ሥራ በግብፅ ውስጥ ካሉት ጥንታዊያን ሕንፃዎች ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና ወይም ግንኙነት ፈጽሞ የላቸውም:: ሁለቱም ሕንፃዎች በአይነትና በአሰራር የተለያዩ ናቸው:: ልዩነታቸውም በአሰራራቸው ስልትና በባሕርያቸው ብቻ ሳይሆን እነዚህኞቹ ከተፈለፈሉበት ቋጥኝ ተለይተው እንደ ቤት ራሳቸውን ችለው በመቆማቸው ከዋሻዎች ውስጥ እና ውጭም በመፈልፈላቸው ጭምር ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

ወደኋላ ልመለስና የአክሱም ነገሥታት በ921 ዓም አጤ ድል ነአድ በመራ ተክለ ሃይማኖት አጤ ድል ነአድ ሲጠቁ ወደ ሸዋ መንዝ ተሰደዱ:: የሚሉ ሲኖር አንዳንዶች ደግሞ አጤው ወደ ሸዋ አልተሰደዱም የተሰደዱት ሌሎች ልጆቻቸውና የቤተ መንግሥቱ ባለመዋል ናቸው ይላሉ:: ይህ የነገሥታት ትውልድ ሸዋ ከገባ ጀምሮ ከአማራውና ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ተጋብቶና ተዋሕዶ የኖረው ተማሪ ተሥፋ ልደት የኋላው አጤ የኩኖ አምላክ የሐይቅ ገዳም ተማሪ ነበሩ:: በዚህ ገዳም የቤተ ክህነትና የታሪክ ተማሪም በመሆን ቆይተዋል:: በዚህ ወቅት ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር ግንኙነት መስርተዋል:: አብዛኛው ደግሞ ለዛጉዌ ነገሥታት ለአጤ ይትባረክ ወታደር በመሆን አገልግሏል ተብሏል:: በደሮም ተመካኘ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስልጣኑን በ1261 ዓም ከሮኃ ወደ ሸዋ አዛውረዋል:: የሸዋ መንግሥት በ1261 ዓም እስከ 1519 ዓም በሰላም ኑሯል:: በነገራችን ላይ የአጤ አምደ ጽዮንንና የአጤ



ዘራዕይ ይቆብን ጀግንነት ሳይጠቀስ የማያልፍ ታሪክ አለ:: እነዚህ ገናና ነገሥታት ለአገር አንድነት ያደረጉት ትግል ሊሰመርበት ይገባል::

አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ <u>ድብቁ መለኮታዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 111 "አጤ አምደ ጽዮን ክርስቲያን ንጉስ እንደ መሆኑ መጠን ክልሉን በተለይም ከአማራ ሀገር ቀጥሎ ወደ ታች እስከ ሕንድ ውቃያኖስ ያለው ሀገር በእስላሞች ተይዞ ስለነበር ያንን ለማስለቀቅ ብዙ ጦርነቶችን እንዳካሄዱ የንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሐፊ በአንክሮ ገልጾታል" ሲሉ ጽፈዋል:: በ1519 ዓም ላይ ግን የቱርክ ረዳት ተጨምሮበት አጤ ግራኝ አህመድ ተነስተው መንግሥቱን አናጉት:: ይህን ያህል ዘመን የቆየው የሸዋው መንግሥት አንድም የታሪክ አሻራ ቤተ መንግሥተይ አልተወልነም የለም:: ገዳማት መመስረታቸው እንዳለ ሁኖ ሌሎች ለቤተ መንግሥት መገልገያ ከተማ ፍርስራሹ አልተገኘም::

ግራኝ ተብሎ ተጽፎ ያገኘነው በእኔ አጻጻፍ አጤ አሕመድ (ግራኝ) ትውልድና ዘር በኩል የትግራይ አፋር ተወላጅ የሐረር ባላባት ከሆኑ የተወለዱ ሲሆኑ ቱርኮችና አረቦች ባስታጠቁአቸው የጦር መሳሪያ የአጤ ልብነ ደንግልን ጦር እይመቱ ምት መተው መላ ኢትዮጵያን በግድም በውድም ለ15 ዓመታት አስተዳድረዋል:: የአጤ ልብነ ደንግል መንግሥት ከሸዋ ወደ ጎንደር መግባት መንስኤው እርሳቸው በአጤ ግራኝ አህመድ ድል መሆናቸው ነው:: ልጃቸው አጤ ገላውዲዮስ አጤ ግራኝ አህመድን ድል ካደረገ በኋላ ደንቀዝን መሰርተዋ:: ሊቦ አውራጃ ውስጥ እንዲሁ በዘመኑ ለስንት ዓመት የተሰራበት መሆኑ ግልጽ ባይሆንም ቤተ መንግሥት አለ:: ሌላው በዚሁ አካባቢ አንድ አስደናቂ ታሪካዊ ገበታም ይገኛል:: የቤተ ክርስቲያኑን ስም መጥቀሱ ምናልባት ለሌቦች መጠቆም እንዳይሆን እንጂ ታሪካዊ ገበታው የተጻፈበት በእብራይስጥና በአርብኛ ሲሆን ትርጉሙም አብርሃም ይስሃቅን ለአምላኩ ሊሰዋለት በተዘጋጀ ግዜ ደሙን ሊያቀትበት ይዞት የነበረው ገበታ መሆኑን ጹሁፉ ይገልጻል:: ይህን ታሪክ ሲናገሩ የሰማኋቸው

<u>አንድ አባት ሐምሌ 27 ቀን 1999</u> ዓም ነው:: ከዚያም ጎርጎራ በአጤ ፋሲል ተመስርቷል:: ኋላም ጎንደር በ1632 ዓም ተመስርቷል:: ጎንደር ቤተ መንግሥትያ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከሆነ ጀምሮ ዳር ደንበር ለማስጠበቅ ጥረት ተደርጓል:: አንዳንድ ግለሰቦች አሮሞዎች ከሩቅ አገር የመጡ አስመስለው ይናገራሉ:: ይህ ከእውነት የራቀ ሲሆን ትክክለኛ ታሪክ ግን ከቦረና ወደ ደጋው ኢትዮጵያ የተስፋፉ ናቸው:: እነዚህ አሮሞዎች ንዋሪዎን ሕዝብ እየገደሉና የነሱ ባሪያ እያደረጉ እስከ ትግራይ ተስፋፍተዋል:: መልካቸው አቋማቸው ከሌላው ኢትዮጵያዊ የማይለዩ መሆናቸውን እንኳን የማይገነዘብ አንዳንድ ደነዝ ግለሰብ አፉ እንዳመጣለት ከውጭ መጡ ይላል:: ሕዝቡን ገድለው መሬቱን ስሙን ቀይረው እነሱ ሰፍረውበታል ከተባለ ትክክል ነው:: በጎንደር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ አብረው የሥልጣን ተቋዳሽ ኑረዋል:: የሁሉም ነገሥታት የትውልድ ሀረግ ሲመዘዝ ዘሩን ይጠቅሳል:: ለምሳሌ

በጎንደር የሚነገር አማርኛን በጥሞና ብናመሳክረው ኦረሞኛ ቋንቋ ቅልቅል ይታይበታል።

ጉርባ፣ሙጫ፣ሉባ እነዚህ በ3 ቃላት ለምን የአማርኛ መጠቀሚያ ሆኑ። ጉርባ ማለት ወጣት ልጅ እንደማለት እንጠቀምበታለን። ሉባ ማለት ደግሞ ብልህ ልጅ እንደማለት ነው። ሙጫ የሚለውን ደግሞ ትንሽ ልጅ ወይም ደግሞ ለማንኛውም ትንሽ ለማለት ሙጫ እንላለን። የአባ ባሕሪን ድርሰት ሳነብ ኦሮሞዎች በጌምድር ላይ ጦርነት ሲያደርጉ የተዋጉበት ቦታ የጠቀሰው እኔ ተወልጄ ካደኩበት አካባቢ በተለይ አያቴ እማሆይ የሹሜ ወርቁ የተወለዱበት መንደር መሆኑን አነበብኩ። ቱርኮች በምጽዋ ብቅ ብለው ባህረ ነጋሽ ይስሀቅን ወደነሱ በማስገባታቸው ምክንያት አጤ ሠርፀ ድንግል በ1573 ዓም ጦርነት ገጠሙት። በዚህ ጦርነት ወቅት ከሀዲው ባሀረ ነጋሽ ይስሀቅ በደቡብ ኢትዮጵያ ተዋጊ ተመቶ ሞተ። የዛሬው ከተማ ጎንደር ከ1632 ዓም ጀምሮ እስከ 1761 ዓም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ስትሆን ከ1761 ዓም እስከ 1845 ዓም ድረስ ያለው ዘመን መሳፍንት ተብሎ የሚጠራው አጥፊ ዘመን ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ጠቅልሉ ከጎንደር የለቀቀው ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ከሞቱ ወዲህ ነው። በጎንደር ዘመነ መንግሥት ብዙ ልማቶች እንደነበሩ ቢጠቀስም። ዛሬ ድረስ ሕያው ምስክር ሁኖ የምናየው የፋሲል ግንብ የተገነባ ቢሆንም ቅሉ የጦር መሳሪያ ስላላመረቱ አጤ ቴዎድሮስ ይበሽቁ ነበር።

## ምዕራፍ 5

## ከዘመነ መሳፍንት እስከ አጤ ምኒልክ!

በንጉሠ ነገሥት 2ኛው አጤ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመን በ1747 ዓም ትግራይን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ደጃዝማች ስሑል ሚካኤል ይባሉ ነበር። እርሳቸው በባሕረ ነጋሽ አርኪኮ ብቅ እያሉ ከሚሄዱ ቱርኮች ጋር ተወዳጅተው የጦር መሳሪያ እያጠራቀሙ ራሳቸውን ማደራጀት ጀመሩ ኋላም ሸፈቱ። በቀድሞው ባህልና ወግ መሰረት የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ አባቶች በሽምግልና መክረው እንዲያስገቧቸው ተብሎ ካሉበት አካባቢ ሰዎች ቢላኩም ደጃዝማች ከአቅዋማቸው ፍንክች የማይሉ ሆኑ። አጤ ኢያሱ ምታ ነጋሪት ክተት ሰራዊት ብለው ጦርነት ሲገጥሙ ደጃዝማች ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቁ ቢሆንም የአጤውን ሰራዊት ሊቋቋሙ አልቻሉም። ቀድሞ እምቢ ብለው የነበረውን ሽምገግልና እሽ አሉ። ደጃዝማች እጃቸውን ሰጥተው ጎንደር በግዞት እንዲቀመጡ ተወሰነ። ከተወሰነ ዓመታት በኋላ ምሕረት ተደርጎላቸው የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ወይዘሮ እስቴር ኢያሱን እንዲያገቡ ተደርጎ ከደጃዝማችነት የራስነት ማዕረግ ተቀብለው የቀድሞ ግዛታቸው ትግራይ ተመልሰላቸው ሄዱ።



ንጉሠ ነገሥት አጤ ኢያሱ ሙተው ልጃቸው አጤ ኢዮአስ በኢትዮጵያ ሲነግሡ ለራስ ስሑል ሚካኤል ደስ አላቸው። ምክንያቱም አጤ ኢዮአስ ልጅ ናቸው። እንኳን ደስ አልዎ"ለማለት የሚመጡ መስለው 26 ሺህ የጦር መሳሪያ ከቱርክ ተቀብለው ከትግሬ ጎንደር ገቡ። ከዚያም ግንቦት 8 ቀን 1761 ዓም አጤ ኢዮአስ ኢያሱን በሻሽ አንቀው ገደሉአቸው። አንዳንድ ጸሐፊ "ራስ ስሑል ከትግሬ ጎንደር እንደዝቡ ከአጤ ኢዮአስ ጋር በሰላም ብዙ ወራት ተቀምጠዋል" የሚሉ ቢኖሩ አብዛኛው ሠነድ ግን የሚለው ራስ ከፍተኛ የሆነ የሥልጣን ፍላጎት ስለነበራቸው የየጁ ኦሮሞዎችና የቋራ አማሮችን ጠብ በከፍተኛ ልዩነት እንዲያድግ ካደረጉ በኋላ አጤ ኢዮአስን ገድለው ሌሎችን የነገሥታት ዘሮች ከወይን አምባ አምጥተው እህታቸውን ለ70 ዓመቱ አዛውንት ድረው እርሳቸው አድራጊ ፈጣሪ ሁነው ሳለ የቋራ አማሮች የእትጌ ምንትዋብ ቤተሰቦች በከፍተኛ ቁጭት ሲነሱ የየጁ ኦሮሞዎችንና አማሮችን እንዲደባበዱ አድርገዋል" ይላሉ።

ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሉ</u>ች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 295 "ራስ ስሑል ሚካኤል የተባለው ሰው ተነስቶ ነገሥታቱን በየምክንያቱ አንዱን እየገደለ አንዱን እያነገሠ ኢትዮጵያ ለሥርዓት አልበኝነት አመራር ዳረጋት። ከጥንት ጀምሮ ለኢትዮጵያ አንድነት ምልክት የነበሩት ነገሥታት ከተዳፈሩ በኋላ በሌብነት፣በቀማኝነትና በሰንፍና ወድቆ የነበረው ሁሉ አሁን በያለበት እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በመባባል በያለበት ብጥብጥና ጦርነት ያካሄድ ጀመረ። ትምህርትና ብስለት በሌላቸው ደደብ አለቆች መሪነት የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞት ፍርድ የተፈረደበት ለከፍተኛ የመጨረሻ ውድቀት የተጋለጠ አሳዛኝ ሕዝብ ሆነ። ዘመነ መሳፍንት በሚባል ዘመን የሌቦች አለቆች ወሮበላ እንዲከተላቸው ዋና መጠቀሚያ ያደረጉት የነበረው መሣሪያ ዘር እየቆጠሩ የጨዋ ልጅ ነኝ በማለት ነበር። እኔ በጣም የሚገርመኝ ወረበላዎቹ እርስ በራሳቸው ፊታውራሪ፣ደጃዝማች፣ ራስ ተባብለው ሕዝቡን እርስ በርስ እያፋጁ ኢትዮጵያን ያጠፋአት መሆናቸው ሲታወቅ መሳፍንትና መኳንንት መባላቸው ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

በላይ ግደይ <u>የኢትዮጵያ ሥልጣኔ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 171 "ራስ ስሑል ሚካኤል በ1761 ዓም አጤ ኢዮአስን በሻሽ አሳንቆ አስገደለው። በንጉሥ ሺሚና ሻረንቱ የሚታወቀው ኃይሉ ራስ ስሑል ሚካኤል ባለሙሉ ሥልጣን በመሆን ለእርሱ አገዛዝ የሚመቹትን ነገሥታት ብቻ እየመረጠ በየጊዜው አንግሶአቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል። ራስ ስሑል ሚካኤል ኢትዮጵያን በፈላጭ ቆራጭነት በስልጣን ላይ ሲኖሩ አገሪቱን እንዲያስተዳድሩ የፈቀዱላቸው ከቤተ ክርስቲያኑ እስከ ቤተ መንግሥቱ ለትግራይ ተወላጆች ነበር። ዛሬ በወያኔ እንደአለው ሥርዓት ማለት ነው። ሌሎች ነገዶች መሳሪያ ታጥቀው የገንዛ ወገኑን እንዲወጋ አዘዙት እንጂ አገር ለማስተዳደር አልሰጡም።

ዶ/ር ላጲሶ ጌ ድሌቦ <u>የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ</u> በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ 106 " በ1769 ራስ ሚካኤል ስሑል በጎንደር አጤ

ኢዮአስን ጨምሮ የኦሮሞና የአማራ የሥልጣን ባላንጣዎቹን ለመቅጣት 26 000 ወታደሮቹን ይዞ ወደ ጎንደር ከተማ በገባ ጊዜ "ካሉ በኋላ በገጽ 107 "ራስ ሚካኤል ስሑል በአመጽ እርምጃ በጎንደር አጤ ኢዮአስንና ዕጨጌ ሰላማን በማስገደልና ሁለት ሌላ አሻንጉሊት ነገሥታትን ሹም ሽር በማድረግ በአካባቢው ዘመን መሳፍንት ተብሎ የሚታወቀውንና እስከ ዳ/ዊ ቴዎድሮስ ድረስ የሚቆየውን የጦርነት ዘመንና ሥርዓት ከመሰረተው በኋላ በኦሮሞና በአማራ የጦር አበጋዞች ሕብረት በጦር ሜዳ ተሸንፎ በሰኔ 1772 ወደ ትግራ ክልሉ በሽንፈት ተመለሰ" ብለዋል።

በራስ ስሑል የአገዛዝ ዘመን ኑቢያ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሱዳን ተብላ ትጠራ ጀመር። ደቡብ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያኑ መስጊድ እንዲሰራበት በጎሳ የተሳለቀው ስልጣን አፍቃሪ ራስ ስሑል ሚካኤል የኢትዮጵያን መንግሥት በማፍረሳቸው ነው። ይህ ስርዓት የለሽ ዘመነ መሳፍንት የኢትዮጵያ አንድነት ማፍረሱ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በጎሳ ተከፋፍሎ እንዲደባደብ የተደረገበት ሲሆን የኢትዮጵያ ጠላቶች ሰላዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡበት ወቅት ነበር። ሌላው ቀርቶ ጀምስ ብሩስ የአባይን ወንዝ ተከትሎ ኢትዮጵያ የገባበትና የኢትዮጵያ ቅርሳቅስ የዘረፈበት ዘመን ነበር። በዚህ ወቅት አንድ ታምር ተፈጠረ! ያም ባልታሰበና ባልተጠበቀ ቦታ መይሳው ካሳ የኋላው አጤ ቴዎድሮስ ተነሱና ቅድሚያ ቅኝ ግዥውን ቱርክን ሰናር ድረስ እየዘመቱ ያስቃዩት ጀመር። ይህ በዚህ እንዳለ የእርሳቸው ዝና ይበልጥ በቋራና በደንቢያ አልፎም ጎጃም አገው ምድር ይሰማ ጀመር። ደጃዝማች ገለሞ ከጭልጋ ቅማንት፥ፊታውራሪ ገብርዬ ከጋይንት፥ ራስ እንግዳ ከጎጃም ተራ በተራ ወደ ልጅ ካሣ ሠፈር መጡ።

የልጅ ካሣ ጀግንነትና ቆራጥነት ከሕብረተሰቡ አልፎ ጎንደር ግንብ ጠባቂው 3ኛው አጤ ዮሐንስ ባለቤት ለእትጌ መነንና ለልጃቸው ለራስ አሊ ሰላም ይነሳቸው ጀመር። መሳፍንቶች እንደካሣ ያለ ወንድ ብቅ ሲል ወደ መንደራቸው እንዲመጣ ሺህ መልዕክተኛ ይልኩና ያስመጡታል። ውለው አድረው ሞራሉን አድቅቀው ይለቁታል። ይህን በማድረግ የተካኑት መሳፍንቶች ካሣን "ከማራቅ ማቅረቡ ሳይሻል አይቀርም በማለት የልጅ ልጃችን ትዋበች አሊን እንስጠዋለንና ይምጣ"የሚል ውሳኔ ይደርሳሉ። ልጅ ካሣ ጥሪውን ተቀብለው ጎንደር ሕደው ትዋበችን አግብተው ወደ ቋራ ተመለሱ። ሳይውሉ ሳያድሩ ወደ ገዳሪፍ ዘመቱና ቱርክ በዘመናዊ የጦር መሳሪያ የደነደነውና በወታደራዊ ስልት የሰለጠነ መሸጎ የተቀመጠውን የካሣ ሰራዊት ይነድፈው ጀመር በዚህ ወቅት ልጅ ካሣ ቆሰሉ።

አንዳንድ የታሪክ መጽሐፍት በዚህ ወቅት ባለቤታቸው ወይዘሮ ተዋበች አሊ አብረው ሕደው ስለነበር በቱርክ ተማርከውባቸው ነበር። ነገር ግን ልጅ ካሣ ከታሰሩበት ገብተው አስለቅቀው ይዘዋቸው ወደ ሠራዊታቸው ተቀላቀሉ የሚሉ አሉ። ልጅ ካሣ በዚህ ጦርነት መቁሰላቸው የሁሉም የታሪክ ደራሲያን ቃል አንድ ነው። እርሳቸው ቢቆስሉም ብዙ ንብረት ማርከው መመለሳቸው ታውቋል። ከሱዳን ወደ ቋራ እንደተመለሱ ብዙም ሳይቆዩ ባለቤታቸውን



በመያዝ ከማረኩት ንብረት ይዘው ጎንደር ሄዱ። እንደደረሱ ብዙም ሳይቆዩ ኩሶ ታይቷቸው መድኃኒት ቀምሰው ዋሉ። በዚህ ወቅት እትጌ መነን "ለቆለኛ ወርቅ አያንሰውም" ብለው አንድ ወርች ስጋ ስለላኩላቸው ልጅ ካሣ ተቆጡ ወዲያው ባለቤታቸውን ይዘው ወደ ቋራ ገሰገሱ።

ልጅ ካሣ እትጌ መነን ሆነ ግንብ ጠባዊቂው 3ኛው አጤ ዮሐንስን ሆነ ሌሎችን መኳንንቶች ሳይሰናበቱ ጉዞአቸውን ወደ ቋራ አደረጉ። የባልና ሚስቱ መጥፋት በቤተ መንግሥቱ ሲሰማ እቴጌ መነን "ይህ የፍየል እረኛ ልጅ ምንኛ ቢንቀን ነው? ሳይሰናበተን ልጃችን ይዞ ሄደ" በማለት ይጮሁ ጀመር። በዚው ወቅት ልጅ ካሣን አንቆ ይዞ የሚያመጣ ጦር ወደ ቋራ ተላከ። ልጅ ካሣም የመጣውን ጦር ደምስሰው ማረኩ። ከጎንደር ወደ ቋራ የሄደው ሰራዊት መደምሰሱ ወሬው ጎንደር ሲሰማ እንዴት ቢደፍረን ነው ይህን ያደረገው ይባልና ይሳቅም ጀመር። እትጌ መነን ግን ተበሳጩ ደጃዝማች ወንድ ይራድ በዚህ ቀን "ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ አንገቱን አንቄ አመጣዋለሁ በማለት በብርሌ ጠጃቸውን እንደያዙ ፎከሩ። ደጃዝማች ወንድ ይራድ የአራት ደጃዝማቾች ጦር መሪ በመሆን ወደ ልጅ ካሣ ሰፈር ገሰገሱ። በሌሎች የታሪክ አጻጻፍ የደጃዝማች ወንድ ይራድ እንጅ ቀኛዝማች ወንድ ይራድ አይባሉም ደብተራ ዘነብ ግን ቀኛዝማች ይሏቸዋል። ስለዚህ ጦርነት ጉዳይ ደብተራ እንዲህ ይላሉ።

ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ ሲትማን ያሳተመው ገጽ 10 "መኳንንት ብዙ ነው 1000 ነፍጥ ተማረከ። ልጅ ካሣም አራት መቶ ጋሻና 22 ነፍጠኛ ይዘው ነው የገጠሙት። ተወይዘሮ መነንም አንድ መኮንን ቀኝ አዝማች ወንድ ይራድ እንዲህ ብሎ ፎከረ። ለወይዘሮ መነን ይህን የኮሶ ሺያጭ ልጅ አሁን እንደ ሙጭልጭላ አንገቱን አንቄ አመጣልሻለሁ አይዞሽ ብሎ ወይዘሮ መነን እንደ ደነገጡ አይቷልና ልጅ ካሣ ሽፈተ ባልዋቸው ጊዜ ጫቆ ተተያዙት መኳንንት አንዱ ቀኛዝማች ወንድ ይራድ ነው። የኮሶ ሺያጭ ልጅ ብሎ ልጅ ካሣን የሰደበ። ልጅ ካሣም እሱን እንደ ተያዘ ባዩ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ወታደርንም ሁላ እንዲህ አሉት። ወታደር ዛሬ ለምኘሀለሁ ኮሶ የሚመገብ እንግዳ መጥቶብኛልና ብለው ብዙ ኮሶ በተሰበሰበ ጊዜ አስቀድተው በታላቅ ጥዋ ሙሉ አድርገው ለቀኛዝማች ወንድ ይራድ እንዲህ ብለው ሰጡዎው። እናቴ ከገበያው ኮሶ ሳይሸጥላት ቀረ። እህል ታጣና ይህንን ኮሶውን ተመገቡ ባሉ ጊዜ እኩሌታው አስተፋው ልጅ ካሣ ጦራቸውን ከጭናቸው አኑረው ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ልጅ ካሳ ሲባሉ ሳለ ደጃዝማቹን ማረኩ። በኢትዮጵያ ባሕል መሰረት ደጃዝማች የማረከ ደጃዝማች ይባላልና ከዚህ ወዲህ ደጃዝማች ካሳ ተብለው ይጠሩ ጀመር። ደጃዝማች ካሣ እርሳቸውን ሊወጋ የመጣውን ሁላ አንድ ባንድ ድል ካደረጉ በኋላ ሌሎችን መኳንንቶችን ተራ በተራ ደብድበው በኢትዮጵያ ላይ አጤ ቴዎድሮስ ተብለው የካቲት 5 ቀን 1845 ዓም ነገሡ። ከዚህ ወዲህ የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ምኞት አደረባቸው።

ጠመብንጃ አውሮፓ ተሰርቶ ከሚመጣ

ከሀገሬ ኢትዮጵያ ከአፈሩ ተነጥሮ ይውጣ!
የሃይማኖት አስተማሪ ከአውሮፓ ከሚመጣ
ከሀገሬ ቤት ክርስቲያን ከገዳም ይውጣ
ኢትዮጵያ ዳር ደንበሯ ይጠበቅ
ድንቁርና ጠፍቶ እውቀት ይራቀቅ
ኢትዮጵያ በሁሉም ነገር ትላቅ

ብለው ሲነሱ ምድረ መኳንንት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የእርሳቸውን ዓላማ የማይደግፍ ሁላ ተገድሏል:: ሰው ቤት ውስጥ ገብቶ በላት ተቃጥሏል:: ነገር ግን እርሳቸው የማይሆንላቸው በሀገራቸው ምክንያት መሆኑን የዓይን ምስክር እስረኛው እንግሊዛዊ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል::

ዶ/ር ሕንሪ ብላንክ ዳኛው ወልደ ሥላሴ እንደተረጎመው <u>የእሥራት ዘመን በአበሻ አገር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 184 “ቴዎድሮስ በራሳቸው ጉዳይ መታገሥ ይችላሉ! በአገር ጉዳይ ግን ፈጽሞ ትዕግሥት አልነበራቸውም” ሲሉ ጽፈዋል:: አጼ ቴዎድሮስ ያደጉት ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ሊሰጠው ካለው ቦታ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም በመሆናቸው የኢትዮጵያን ታሪክና ወታደራዊ ኃይሏን ጠንቅቀው ስማቸው ባልታወቀ ፈላሲ መነኩሴ ተምረዋል:: እርሣቸውን እቅድ ያልተከተለውን ገድለዋል:: ታዲያ አንዳንዴ በገና ሲደረድሩ እየበሸቃቸው እንዲህ ይሉ ነበር::

“ይሉኛል ይሉኛል ይሉኛል ጨካኝ
ሐሳቤን ሳያውቁ ምክሬን ሳይሰሙኝ”

በማለት ያዜሙ ነበር:: ጋፋት የብረታብረት እንዱስትሪ መስርተው ከሀገራቸው ውስጥ መድፍ ተሰርቶ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ተጠብቆ ኢትዮጵያውያን በትምህርት ልቀው ተራቀው ማየት ነበር የእርሳቸው ዓላማ:: የዛሬው ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው በ1965 ዓም ጋፋት የአጤ ቴዎድሮስ የብረታብረት ፋብሪካ በተባለው መጣጥፋቸው የእውቀት ጥማት የገደላቸው መስሉ ስለታያቸው::

አበባው ይግዛው <u>የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ</u> ጥር 25 ቀን 1965 ዓም “አጤ ቴዎድሮስን የገደላቸው የጥበብ ጉጉታቸው ነው” ሲሉ ጽፈዋል:: ስለዚህ የአጤ ቴዎድሮስን ሕልም የተረዳላቸው መኳንንት አልነበረም:: የውጭ አገር ሰዎች በሃይማኖት ስም ሰላዮቻቸውን ልከው ከእርሳቸው ጋር ግጭት ፈጥረው ሲታሰሩ የገንዛ ወገናቸው የውጭ አጎብዳጅ ሀገሩን ካጅ ምድረ መኳንንት አሲሮ አሲሮ የእንግሊዝን ጦር መርቶ አምጥቶ አገሪቱን አስደፈረ:: እርሳቸውም በራሳቸው ሽጉጥ ጠጥተው ሞቱ:: ወይዘሮ ምንትዋብ ጎጃሜ አጤ ቴዎድሮስ አባታቸውንና ወንድሞቻቸውን ስለገደሉባቸው አጤውን እየሰደቡአቸው ለ14 ዓመታት አብረው ይኖሩ ነበር:: ወይዘሮ ምንትዋብ አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ አሉ::



አባቴን ወንድሜን ቢገድሉ ነበር መናደዴ
በራሱ ቆረጡ ይቅር አለ ሆዴ

እያሉ ሲያለቅሱ ሌሎች የአጤ ቴዎድሮስን ሬሳ ሲመቱና ሲጎትቱ እርሳቸው ሬሳውን ሌሎች እንዳይመቱ ይከላከሉ ነበር:: የአጤ ቴዎድሮስን ሬሳ ከሚመቱት መካከል ካህናቱ ይበዙ ነበርና ወይዘሮ ምንትዋብ ወንድ መሳይ አለሁ አለሁ ባይ፤ፈሪ ሬሳ ገዳይ፤ ብለው በጎደም ራሱን ሲሉት ቅንባ የሚያከለው ሻሹን አስጣሉት:: እኒያ የቤት ጀግና ግን አንዳንዴም እየፈከሩና እያለቀሱ እያዘኑ የዚያን ጀግና ሬሳ ልብስ እያለበሱ ሲታገሉ ባለ ሌላ ታምር መታየት ጀመረ:: የእንግሊዝ ወታደር የአጤ ቴዎድሮስን ዘውድ ከራሳቸው ላይ ሲያወጣ ግል የማነን ዘውድ ማን ይወስዳል ብለው ፈረንጁን ጉርቦውን አንቀው ባለ እንግሊዛዊው አብሮ ሁለቱን መግደሉን

ቀሲስ ከፍ ያለው መራሂ <u>ሰስቱ ምንትዋቦች</u> በተባለው መጣጥፋቸው ታሪካቸውን ጽፈውታል:: እርሳቸው ታሪኩን ያገኙት እንፍራዝ ቤተ ክርስቲያን የአጤ ቴዎድሮስ ልጅ ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ ጽፈው የተዉት መሆኑን ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ በልጅነታቸው ጀምሮ ዳር ደንበር ማስከበር ነበር ሕልማቸው:: የትግሬው ደጃዝማች ንጉሤ ለፈረንሳይ መሬት በባህር ደንበር ላይ መበስጡቱ አይገቡ ገብተው እርሱን ድል አደረጉ ፈረንሳዮች ቴዎድሮስ እንዳይመታቸው ሩጠው ጠፍተዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ሲሞቱ በወቅቱ ጉልበታም መኳንንት የነበሩት የስቆጣው ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድህን 2ኛው አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው በኢትዮጵያ ላይ ግንቦት 10 ቀን 1860 ዓም ነግሰው የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማ አንስተው ጎንደር ደጃዝማች ጥርሶ ጎበዜን ለመውጋት ሲሮጡ እርሳቸውንም ድል ሲያደርጉ ጎጃም በመሸፈቱ ወደ ጎጃም ዘምተው አንዱን ድል አድርገው ሲያባርሩ ባላምባራስ አዳልን ራስ ብለው ሲመለሱ ትግሬ የባለቤታቸው ትንሽ ወንድም ልማደኛው ደጃዝማች ካሳ አሁንም በድጋሜ እርሳቸውን ወግተው የኢትዮጵያን መንግሥት አፈረሱ::

ደጃዝማች ካሣ ቅድሚያ አጤ ቴዎድሮስን ለማስገደል እንግሊዞችን መርተው የመጡ ናቸው ይችን ታሪክ የወያኔ ሰዎች ሊሰሙ አይፈልጉም:: ደጃዝማች ካሳ 4ኛ አጤ ዮሀንስ ተብለው ሐምሌ 7 ቀን 1863 ዓም ሲነግሱና የዘውድ ባላቸውን ባመቱ ቢያከብሩም ወዲያው በተለያየ ቦታ ግብጽ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለመያዝ ስትመጣ አጤ ዮሐንስ ድባቅ መተው መለሱ:: በዚህ ጦርነት ከፍተኛ የሆነ ጀግንነት ሰርተዋል:: በዚህ ድል እኛ ኢትዮጵያውያን ከልብ እናከብራቸዋለን::የሚገርመው ነገር ደግሞ አጤ ዮሐንስ ጀብድ የሰሩበት መሬት ልጆቻቸው ወያኔዎች ለኤርትራ ሰጡት:: በዚህ ጦርነት በተለይ የትግራይ ልጆች በብዛት ደማቸው የፈሰሰበት ጉዳጉዲትኔን ጉራዕ ሌሎችም ወረዳዎች ዛሬ የአጤ ዮሐንስ ወታደር ደሙ የፈሰሰበትን መሬት በታሪክ “ነበር” እያልን ማውሳት ብቻ ሆነ:: የአጤ ዮሀንስ ጀግንነት ይህ ብቻም አይደለም:: በ12ኛው ክፍለ ዘመን በቅዱስ ሀርቤ ተጀምሮ የነበረው

ኢትዮጵያውያን ልጆች ጳጳሳት ይሾሙ የሚለውን በማንሳታቸው ግብጾች 4 ጳጳሳት ልከውላቸዋል። በዚህም ክርስቲያኖች ልንኮራባቸው እንችላለን። ነገር ግን በወሎ እስላሞች ላይ ሳያስተምሩ ለፈፀሙት ጭካኔ እንደግፍም።

የአጤ ዮሀንስን ሌላው ስህተታቸው ጣልያንን በተመለከተ ሰሐጢ ዘምተው ሳይወጉ ተመለሱ። እንዲሁም ጎንደርን ድርቡሽ እንዲወረው የሆነው 1ኛ ጎንደሬዎችን ተሰሪ በተባለ ሠራውይታቸው በመፍጀታቸው 2ኛ በአካባቢው ጦር ትተው ባለመሄዳቸው ሲሆን 3ኛ ከሰሐጢ መተማ መዝመት ሲገባቸው እርሳቸው ግን ድርቡሽን ቅድሚያ ሳይወጉ ወደ ጎጃም ዘመቱ። አጤ ዮሐንስ ልብ የሚነካ አዋጅ ነበር ወደ ሰሐጢ ሲዘምቱ ያወጁት።

አዋጅ!

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ልብ አድርገህ ተመልከት ኢትዮጵያ የተባለችው 1ኛ እናትህ ናት! 2ኛ ዘውድህ ናት! 3ኛ ሚስትህ ናት! 4ኛ ልጅህ ናት! 5ኛ መቃብርህ ናት! እንግዲህ የእናትን ፍቅር የዘውድ ክብር የሚሸትን ደግነት የልጅን ደስታ የመቃብርን ክባቲነት አውቀኸው ተነሳ ይህንንም አዋጅ ከሰማህ በኋላ ከመጋቢት 25 ቀን 1880 ዓም ጀምረህ ወደ ሰሐጢ ተጓዝ" የሚል አዋጅ አውጀው ወደ ሰሐጢ ተጓዙ።

እርሳቸው ወደ ሰሐጢ ሲዘምቱ ጎንደር በድርቡሽ ሲወረር እርሳቸው ጣልያንን ጦርነት አልገጠሙም ነበር። የሕዝቡ መልዕክት ሲደርሳቸው የጣልያን መነኩሴ ከክርስቲያኑ ጣልያን ጋር ጦርነት ከሚገጥሙ ክርስቲያኑን ያጠፋውን ድርቡሽን ቢገጥሙ መልካም ነው እያሉ ለእኛ የበስማም ቄሶች ሲነግሩአቸው እነሱም ይህን ለአጤው ሲያስረዱአቸው ከሰሐጢ መቀሌ ከመቀሌ ደብረ ታቦር ከዚያም አመድ በር ላይ ደርሱ። ከአመድ በር ላይ ውይይ ተደረገ። መኳንንቱ ቅድሚያ መተማ መዝመት አለብን አሉ። እርሳቸው እና አንዳንድ የእርሳቸው ደጋፊዎች ደግሞ ቅድሚያ ጎጃም እንዝመት አሉ።

ገሪማ ታፈረ የመከራ ድምል ከምጽዋ እስከ መተማ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 127 "አልሰማም እኔ ጃንሆይ በእውነቱ እንውረድ መተማ እንዝመት በሚሉት በየክፍሉ ትተን ከቤታችን ጠላት አጋጣሚ ሆኖ ድል ብንሆን ድንገት ልጆቻችን እኮ አያገኙም ግዛት አምጠው እያዩን ሸዋና ጎጃም ከመለዲ ጋራ ወርደን ብንገጥም ያየስ መቸም አይድን የሰማ አይሰቅም! የመተማው መውረድ ጥቂት ይቆየን አስቀድመን ሸዋ መዝመት አለብን ሺዋን ጋልበንበት አርጌሳ ድረስ ግርማችን አሳይተን ለደቡብ ንጉሥ ጎጃምን ነብኘተን እስከ ርእስ ርእስ ይህን ፈጽመን ነው በደም መለወስ ጦርነት የሚገጥም ሁለት ልብ ሆኖ ወገን አስጠቅቶ ጠላት አደንድኖ እንደ ትቢሓ ጢስ ያልቃል በኖ በኖ ወደ መተማ ስንዘምት አይታየኝም" ሲሉ ተናግረዋል።

ስለዚህ አብዛኛው መኳንንት ቅድሚያ መተማ እንዝመት ሲሉ እርሳቸውና ጥቂት መኳንንቶች ግን ጎጃም ዘምቼ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ደፍቼ ሸዋ



ተሻግሬ ንጉሥ ምኒልክን ፈንክቼ መተማ እዘምታለሁ ብለው ጎጃም ዘመቱ ድል አድርገው ወደ ሸዋ መንገድ ሲጀምሩ ከንጉሥ ምኒልክ የተላከ ባሕታዊ "ዮሐንስ የሥላሴ ባርያ ሸዋ ብትዘምት ምኒልክን ድል ታደርጋለህ! 40 ዓመት ትነግሳለህ! ነገር ግን በነብስህ ትኮነናለህ! መተማ የዘመትክ እንደሆን ትሞታለህ ነገር ግን ትጸድቃለህ" ሲላቸው ቄስ አጤ ሊጸድቁ መተማ ዘመቱና ድል አድርገው ከበቅሎ ላይ ቆጭ ብለው ምርኮ ሲቀበሉ ሳለ በተባባሪ ጥይት ተመቱና ሞቱ። አጤ ዮሀንስ መተማ የዘመቱት ሊጸድቁ እንጅ ለጎንደር ሕዝብ ብለው አይደለም። ለምሳሌ ለያንዳንዳቸው የታሪክ ነጥብ አንዳንድ የታሪክ ሰነድ ዋቢ መጥቀስ አስፈላጊ በመሆኑ ከብዙ በጥቂቱ እነዚህን የታሪክ መጽሐፍት ለዋቢነት ልጥቀስ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ አንድነት እና አጤ ዮሐንስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 504 "ያፄ ዮሐንስ ወታደር በጉዛምንና በማቻክል የተገኘውን የቤተ ክርስቲያን ሳንቃ እየነቀለ እያወጣ በጭምት አፋፍ የጥይት ማብረጃ ለማድረግ ተራውን (ተርታውን) አቁሞ ማገሩን እየፈለጠ ማንደድ ታቦቱም ከመንበሩ እያወጣ በየሜዳው በጣለው ጊዜ በንዴት ጳጳሱ አንተ ድርቡሽን አጠፋለሁ ብዬ መጣሁ ያልከው ለጎጃምአንተ ድርቡሽ ሆንክ ብለው አጤ ዮሀንስ መቆጣታቸውን ወደ አምባው ሌሊት እንዲገቡ በጨረቃ የተላኩ ያፄ ዮሀንስ ወታደሮች እንደፈጁ ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ተናደው ከላይ ብዙ ጭፍራ ሰደው ጎጃምን ክፉኛ ማስፈጀታቸው" ይሉና ገጽ 536 "አጤ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ለመምጣት ሲነሱ በምስጢር ከንጉሥ ምኒልክ የተላኩ መነኮሳት መጥተው (ሔደው) ወደ ሸዋ የሄድህ እንደሆነ ንጉሥ ምኒልክን ድል ታደርጋለህ በነፍስህ ግን ትጎዳለህ! ወደ መተማ የሄድህ እንደሆነ ግን በሰማዕትነት ትሞታለህ። በነፍስህ ትጠቀማለህ ቢሏቸው በሥጋዬ ተጠቅሜ በነፍሴ ከምጎዳ ሞት ይሻለኛል ብለው ወደ መተማ ሄዱ" ሲሉ ጽፈዋል። መዝበት አለብኝ ያሉበትን አስመልክቶ ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገልአል።

አጤ ዮሐንስ ሞት የአጤ ምኒልክ እጅ ያለበት መሆኑን አፍወርቅ ገብረ እየሱስ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 56 "ያጤ ዮሐንስ ሞት ግን ባጤ ምኒልክ ብርታት ነው እንጂ በዚያ ደካማ ድርቡሽ ብርታት እንዳልሆነ ሁላችን እናውቃለን" ሲሉ ጽፈዋል።

## ምዕራፍ 6

## አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ ደንበር መደናበር ጀመራ!

ንጉሥ ምኒልክ 4ኛው አጤ ዮሀንስ ሞት ከሰሙ በኋላ ሚያዝያ ሚያዝያ 22 ቀን 1881 ዓም ወሎ ውጫሌ ሁነው "ገኘሁህ እኔ ነኝ ባለሀበት እርጋ"ብለው ሲያውጁ ሱዳን ድርቡሽ ገዳሪፍን አልፈው መደኔ ደርሰው ነበር። የአጤ ምኒልክ ኃይል የማይከተላቸው መሆኑን ካረጋገጡ ጀምሮ ከመደኔ ወደ ገዳሪፍ

ቀስ እያሉ መራመድ ጀመሩ፡፡ ይህ በሱዳንና በኢትዮጵያ በኩል ያለው በዚህ ላይ እንዳለ ቅኝ ገዥዎች ማንጃበብ ጀመሩ፡፡ ከዚህ ላይ ወደ ኋላ ልመለስና የኢትዮጵያን ስፋትና የሕዝቧን ጀግንነት አስመልክቶ ትንሽ ልበል፡፡ ሕዝቧም የጠነከረ ሲሆን በተለይ ጀግንነትን በተመለከተ እንቱ የተባሉ ነበሩ አባቶቻችን፡፡ እስኪ የሌላውን የታሪክ መጽሐፍ ልተውና ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን አንድ ታሪክ ልጥቀስ፡፡

ብርሃኑ ደሴ ጣሰው <u>የፍቅር መቅረዝ</u> በተባለው መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ 79 ግዜ እንደሆነ ምዕራፉንና ቁጥሩን ጨምሮ ጽፈዋል፡፡ እኔ ደግሞ እርሳቸውም ያለፉት አለ እላለሁ፡፡ እርግጥ ከሌሎች ደራሲያን በጣም ልቀው ሔደዋል፡፡ ኢትዮጵያ የምትባል ጥንታዊት ትልቅ አገር ነበረች፤ቁመቷ አጠረ ወርዷ ጠበበ እንጂ ስሟና ሕዝቧ ዛሬ ድረስ አለ፡፡ የዚች አገር ታላቅነትና የሕዝቧ ጀግንነት በተመለከተ ከሌላው የታሪክ መጽሐፍ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው መዝግቦት ይገኛል፡፡

አንዳንዶ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡ ሰዎች 41 ግዜ ስሟ ተጽፏል ይላሉ፡፡ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 14- 9 "ኢትዮጵያዊውም ዝሪ አንድ ሚሊዮን ሰዎችና ሦስት መቶ ሰረገሎች ይዞ ወጣባቸው፤ወደ መሪሳም መጣ፡፡ አሳም ሊጋጠማው ወጣ፤በመሳሪም አጠገብ ባለው በጽፍታ ሸለቆ ውስጥ ተሰለፉ፡፡ አሳም አቤቱ በብዙም ሆነ በጥቂቱ ማዳን አይሳንህም አቤቱ አምላካችን ሆይ በአንተ ታምነናልና፤ በስምህም በዚህ ታላቅ ወገን ላይ መጥተናልና እርዳን አቤቱ አምላካችን አንተ ነህ ሰውም አያሸንፍህ ብሎ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ" ሲል ጽፎአል፡፡ ይህንና ሌሎችን የመሳሰሉ ጥቅሶች መሰብሰብ ይቻላል፡፡ እንግዲህ አንባቢያን ከዚህ በላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ካነበብን በኋላ ዛሬ ለምን ኢትዮጵያ ልትደክም ቻለች? የመጣው ሁሉ ለምን ይጠላታል? የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን አልፈን የመካከለኛዋ ኢትዮጵያን ታሪክ በመጠኑ ቃኝቼ ወደ ተነሳሁበት ልመለስ፡፡

ነጋ ወልደ ሥላሴ <u>ባለታሪክ ኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 7 "ሆኖም ኢትዮጵያ የሚለው ስም በግል መጠሪያነት በተለይ የተሰጣት አንድ አገር ነበረች፤እሷም ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ናት፡፡ አዋሳኞቿም በስተሰሜን ግብጽ ሆኖ እስከ አስንተኛው የዓባይ ወንዝ ፏፏቴ ድረስ የሚዘረጋ ከዚያም እስከ ኤለፍንቲን ደሴት የሚደርስ በስተምዕራብ እስከ ሊቢያ መሐል በምሥራቅ ቀይ ባሕር በስተደቡብ ያልታወቁ የአፍሪካ አገሮች ናቸው፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ በስምሥራቅ የአፍሪካ ጠረፍ ላሉት አገሮች የነፃነት ምሰሶ ሆና ቆይታለች፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት እስከ ቅድመ ልደት ክርስቶስ 1000 ድረስ ኀልውናው ነበረው፡፡ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከ1896 ዓም ጀምሮ በኃያላን የአውሮፓ መንግሥታት ዘንድ የሐበሻ መንግሥት በሚል ስያሜ ታወቀ" ሲሉ ጽፈዋል፡፡



ዘውዴ ገብረ ሕይወት <u>የሕይወት ውጣ ውረድ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 193 "በኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚታወቀው ሶማሊያ ከቅኝ ገዥዎች እጅ ውስጥ ከመግባቷ በፊት ከቀደሙት የኢትዮጵያ ነገሥታት አንዱ አጤ ዘርዓ ያዕቆብ (1426-1460 በኢትዮጵያ (አቆጣጠር) የመንግሥታቸው አስተዳደር በምሥራቅ ክፍል እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ተዘርግቶ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የዋቢ ሸበሌን ጅረት በመከተል ሠፍረው የሚገኙ ሶማሌዎች አዶና የሚሉዋቸው ከሶማሊያ የተለዩ ዘሮች ከአጤ ዘርዓ ያዕቆብ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ተቆርጠው የቀሩ ወይም በአገሩ ላይ የሠፈሩ ለመሆኑ ዋና ማስረጃ ሆነው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡"

ይሉና ገጽ 194 "በሶማሊያ የኢትዮጵያ ወሰን ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምሮ ፥ ቀብሪ ደሐር፥ እየተባለ የሚጠራ አንድ የአውራጃ ግዛት አለ፡፡ ስሙንም ያለጥርጥር ያገኘው ከትግርኛ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም በጦርነቱ ወደፊት እንግፋ ለሞቱት ቀብር በኋላ ይሆናል ማለት ነው፡፡ አጤ ምኒልክ የተጠቀሰውን ሰርኩላር ካሰራጩና የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በዓለም ካሳወቁ በኋላ ጥቂት ቆይት ብሎ ነው ወደ አድዋ የዘመቱት" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

ከአክሱም ምስረታ በፊት የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሜረዊ የሚባለው በዛሬው ቋራ አካባቢ ነበር፡፡ ከ880 ዓመተ ዓለም ወዲህ ቤተ መንግሥቱ ጠቅልሎ ከሜሮይ ወደ አክሱም ሲዛወር ሜሮይ መረዊ ሴሳም ሴላ ተብሎ የሚጠራው ከተማ የንግሥት ወይም የንጉሥ መቀመጫ ሆነ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ አክሱም ሲቀመጥ ንጉሶች ወይም ንግሥቶች በተለይም ከ1 እስከ 12 ሕንደኬም ቤተ መንግሥታቸው በዛሬው ቋራ አካባቢ ሜርዊ እንደ ነበር ነው፡፡

ብላቴ ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል <u>ዝክረ ነገር</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 819 ገልጸዋል፡፡ ግንቦት 8 ቀን 34 ዓም ክርስትና የተጠመቀው (ባኮስ) ጃንደረባው የንግሥት ሕንደኬ ግምጃ ቤት ሹም ነበር፡፡ ሐዋርያው ማቴዎስ ኢትዮጵያ ለማስተማር በመጣ ወቅት ቅድሚያ ከተጠመቁት ታላላቅ ሰዎች መካከል ንግሥት ሕንደኬ አንዷ ናቸው፡፡ ይህ ከተማ እንዳልነበረ የሆነው ከ842 ዓም ወዲህ ነው፡፡ ታዲያ ሜሮይ የሚቀመጠው ንግሥት ሆነች ንጉሥ እስከ ሳይላዕ ግብጽ ይገዙ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ሆና የግዛት ወሰን እየደከመ የመጣው ከ7ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ወዲህ ነው፡፡ ቤተ መንግሥቱ ከአክሱም ሮሃ ላሊበላ ሲዞወር አረቦች ሮማውያንን ከግብጽ አስለቅቀው ሕዝቡን ፈጅተው አገሩን በሰይፍ አስልመው ሲይዙት ለምልክት የተረፈው የአልክሳንደሪያ ክፍለ ሀገር ሲሆን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የነበሩት ቀስ በቀስ የዛሬው ታንዛንያና ኬንያ ሱማሌ ሱዳን ጀቡት ጅቡቲ ሁሉም የኢትዮጵያ ግዛቦት ሁነው ይኖሩ ነበር፡፡

የግብጹ ከሊፋ የክርስቲያኖችን አባት ሊቃነ ጳጳሱን ሲያስር ንጉሠ ነገሥት አጤ ዳዊት በ1375 ዓም ካርቱም መጥተው ካልፈታህ አባይን ሊገድቡ የሚችሉ መሆናቸውን ሲልኩበት የታሰሩትን ፓትርያርክ ፈታ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ሲገኝ ግማሹ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተሰጥቶ

ነበር:: የግብጽ ሊቀ ጳጳስ በሀገራቸው ውስጥ ባለው ችግር ምክንያት ይህ ክብር ያለው መስቀል ለአጤ ዳዊት ላኩላቸው:: ይህ ሁሉ ሲሆን የኢትዮጵያ ግዛት ከግብጽ ጋር ያዋስን ነበር። እንግዲህ ውድቀት የታየው ለመጀመሪያ ግዜ በ1744 ዓም አጤ ኢያሱ ሰናር አስገብረው ሲመለሱ በ1745 ዓም አልገብርም ብሉ ሲሸፍት ያንን ለማስገበር ሲዘምቱ ተደበደቡ። ለዚህም ዘመነ መሳፍንቱ ተመሰርቶ መንግሥት ጠፋ:: እርስ በእርስ ሲዋጋ ከግማሽ በላይ ኢትዮጵያ በቱርክ ቁጥጥር ውስጥ ወደቀች።

ሱማሌም ተረሳች፣ኬንያም ተዘነጋች፣ቱርኮች በጎጃምና በጎንደር ከ1780 ዓም እስከ 1840 ዓም ድረስ 42 ግዜ ጦርነት አድርገዋል:: ይህን ጦርነት የመሩት የአካባቢ የጎበዝ አለቆች እንጂ በመንግሥት ደረጃ አልነበረም:: ከ42 ጦርነቶች መካከል 3ቱን የኋላው አጤ ቴዎድሮስ የመሩት ሲሆን እርሳቸው ከትልቅ ወንድማቸው ከደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ጋር በመሆን በልጅነታቸው ተዋግተዋል:: አጤ ቴዎድሮስ የተዋጉት ገዳሪፍን አልፈው እንደነበር አይዘነጋም:: ይህ ሁሉ ሲሆን ሱዳን የኢትዮጵያ ግዛት ነበር ማለት ነው::

የቀድሞው ኑቢያ የዛሬው ሱዳን በ18ኛው ክፍለ ዘመን አዲስ ስም ካገኘች በኋላ በዓለም ላይ የቱርክ የበላይነት እየቀነሰ ሲመጣ ለእንግሊዝ ግዛታቸውን እያስረከቡ ወጡ:: ግብጾች በተራቸው ሱዳንን ሊመቱ በመነሳታቸው በዚህ ወቅት የሱዳን መሐዲስቶች ተጠናክረው ደብድበው ሲያባርሩአቸው 4ኛው አጤ ዮሐንስ ከሱዳን የሚባረሩትን ወታደሮች መንገድ ከፍተው በከሰላ ወደ ምጽዋ እንዲሄዱ አደረጉ:: በዚህም ድርቡሾች ቂም ያዙ! በወሉ እስላሞች መጎዳትም ተጨማሪ ሆነላቸው:: ከዚህ በኋላ ማሕዲስቶች ያላቸውን ጦር አደራጅተው ኢትዮጵያን ሊወጉ ከገዳሪፍ አልፈው ገላባት ሲደርሱ ቀም የሚላቸው ጠፋ:: በዚህ ምክንያት ማሕዲስቶች ከ1878 ዓም ጀምረው ከገላባት መተማ አልፎ ጭልጋ ሲገባ የሚከላከል የለም:: ምክንያቱም የጎንደር ሕዝብ በአጤ ዮሐንስ ተሰሪ ተደብድቦ አልቋል:: ከሞት ያመለጠው አገር ጥሎ ሐረር ገብቷል:: የቀሩት ቢበዛ ከባላንባራስ ያለፈ ሥልጣን ያለው ጎንደሬ በአጤ ዮኀንስ ዘመን አልነበረም:: የተወሰኑት ሸዋ ገብተው ደጃዝማች የተባሉ ሲኖሩ ጎንደር ሲደበደብ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከጎጃም ደንቢያ ሳር ውሃ ላይ ጦርነት ገጥመው ድርቡሽን አይመቱ ምት መተው ቅስሙን ሰበሩት ነገር ግን ድል የድርቡሽ ሆነ:: በዚህ ወቅት የጎንደር ሕዝብ ተማርኮ ወደ ካርቱም ሲወሰድ እንዲይ ይል ነበር::

“ወገራ አሳላፊ ደንቢያ እንጀራ ጣይ
ተበላይ ጎንደሬ አትነሳም ወይ
ትመጫለሽ ብዬ ዙሬ ዙሬ ሳይ
ወይ ጥጋብ ወይ ኩራት ጎንደር ቀረሽ ወይ” አለ::

የጎንደር ሕዝብ በድርቡሽ ማለቅ የሰሙት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ወይዘሮ ምንትዋብ ከአባታቸው ጋር ዘምተው ያዋጉ ነበሩ:: በእርግጥ ስለ እርሳቸው ቀሲስ ከፍ ያለው መራሂ ሰስቱን ምንትዋቦች በተባለው



መጣጥፋቸው ታሪካቸውን ጽፈዋል:: ጀግና ሴት ሲሆኑ ድርቡሽን በለው እያሉ በማዋጋት ላይ ሳሉ ተማረኩ:: ታዲያ ካርቱም ሲደርሱ “ስለሙ ሲባሉ አልሰልምም በማለታቸው ምክንያት ተገደሉ” ለሃይማኖታቸው ሲሉ የሞቱ ቆራጥ ሃይማኖተኛ ሲሆኑ የሰለሙት ኢትዮጵያውያን ጎንደር መጥተው ተናግረዋል:: የወይዘሮ ምንትዋብ ተክለ ሃይማኖት ግጥም::

“አገር የምትገቡ የምትሻገሩ
ድመት በልታ ሞተች ብላችሁ ንገሩ”

ሲሉ ገጥመው ተገድለዋል:: የጎንደር ሕዝብ በድርቡሽ ሲደበደብ ያለ የሌለ ኃይላቸውን በመያዝ የመጡና ደም መላሽ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሲሆኑ ለእርሳቸው ደንቢያ ሳር ውሃ ላይ መታሰቢያ ሐውልት ሊቆምላቸው ይገባል:: በእርግጥ በስማቸው ስንክሳር የተጻፈ መሆኑን በሰው ሲወራ ሰምቻለሁ:: እንግዲያ ንጉሥ ምኒልክማ ከእንጦጦ አዘዞ ለመድረስ 6 ወር ፈጀባቸው:: አዘዞ ደርሰው ብዙም ሳይቆዩ በጎጃም አድርገው ሸዋ ተሻገሩ:: አጤ ዮሐንስ ጎጃምን ድል አድርገው ወደ መተማ ዘምተው ድርቡሽን ድል አድርገዋል:: ነገር ግን በተባራሪ ጥይት መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓም ተመተው ቆሰሉና በበነጋታው ሞቱ:: ድርቡሽ ሸሽቶ ከሄደ በኋላ አጤውን የገደሉ ለድርቡሽ በርረው ተናገሩ:: በዚህ ወቅት ድል ሁኖ የተባረረው ድርቡሽ ተጠናክሮ እንዲመለስ አደረጉ:: ለአጤው ሞት በታሪክ ተጠያቂው አጤ ምኒልክ ናቸው::

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 56 “ያጤ ዮሐንስ ሞት ግን ባጤ ምኒልክ ብርታት ነው እንጂ በዚያ ደካማ ድርቡሽ ብርታት እንዳልሆነ ሁላችን እናውቃለን” ሲሉ ጽፈዋል:: ሊቀ ጠበብት አፍወርቅ ገብረ ኢየሱስ የአጤ ምኒልክን መጽሐፍ የጻፉት በ1901 ዓም ሲሆን አጤ ምኒልክ በሥልጣን ላይ ሳሉ ነው::

የሕይወት ውጣ ውረድ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 193 “ጥንታዊት ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ አገር የወሰን ክልሏም አሁን ከሚታወቀው የሚያልፍ ነበር:: ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በ1883 ዓም ለዓለም መንግሥታት ባስተላለፉት (ሰርኩላር) በምሥራቅ ያለውን የአገራችን ወሰን ሲገልጹ የኢትዮጵያ ግዛት ወሰን ከሶማሊያም የሚያልፍ መሆኑን አመልክተዋል:: ይህም ቢሆን በአገሩ በርሃማ መሆን ለጊዜው ሳይቀናና የአስተዳደር ሥሪትም ሳይመሰረትበት የቆየ ነበር:: ከዚህ የተነሣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ቅኝ ግዛት ለመያዝ ይጣደፉ ከነበሩት ሦስቱ ኃያላን መንግሥታት ፈረንሳይ፣እንግሊዝ፣ ጣልያን ይህን የአገር ክፍል ተከፋፍለው ሊይዙት ችለዋል” ቢሉ ጽፈዋል::

አውሮፓውያን አፍሪካን ለመከፋፈል 4 ሁነው ካሴሩ በኋላ ሶስቱ በኢትዮጵያ ዙሪያ መክበብ ጀመሩ:: ጣልያን ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓም የውጫሌን ውል ከተዋዋሉ በኋላ አስመራን የአጤ ዮሀንስ አጎት ልጅ ደጃዝማች ደበብ በርያው ይዘው አስረከቧቸው:: ከዚያም ግማሽ ሶማሌን ያዙ:: ፈረንሳይ በደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል ያጣውን እድል በቀይ ባህር መሬት አጤ

ምኒልክ የዛሬውን ጅቡቲን የቀድሞውን ጀቦት በውል ሲሰጡአቸው እንግሊዝ ሱዳንንና ኬንያን፣ ግማሽ ሱማሌን በቅኝ ግዛት ሲይዝ ደንበር ለመደናበር ከአጤ ምኒልክ ጋር መነጋገር ተጀመረ። በዚህ ወቅት አጤ ምኒልክ በደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ሆነ ወደ ጎንደር የተለያዩ መልዕክተኞች ሲልኩ ወደ ጎንደር የተላኩት ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ፣ ጭልጋ ሲደርሱ በወባ ታመሙ። ከሕመማቸው ተሽሎአቸው ወደ ገዳሪፍ ሲሄዱ ሱዳንን የያዘው የእንግሊዝ መንግሥት ተደናባሪ ሻለቃ ግዊን ከዚህ ቀም የሚለው ሰው ባለማግኘቱ የሚበቃውን ያክል ከልሎ ወደ መጣበት ሲመለስ የአጤ ምኒልክ ወኪል ደጃዝማች መሸሻ ሲደርሱ ምልክት እንጂ ሰው ባለማግኘታቸው የሆነውን ለአጤ ምኒልክ ተናገሩ። በዚህ ወቅት አጤ ምኒልክ ይህን ደንበር እንደማይቀበሉት ሚያዝያ 14 ቀን 1883 ዓም ለእንግሊዝ ንግሥት ቢክቶርያ የጻፉት ደብዳቤ እንዳልተቀበሉት ሲሆን ይህን ደብዳቤ በሰነድ አምድ ቁጥር 3 ይመልከቱ።

አስናቀ እንግዳ <u>አረባዊ አጼነትና የአፍሪካ ቀንድ ፍዳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 148" እንግሊዝ ሱዳንን በቅኝ ገዥነት በምታስተዳድርበት ግዜያት በኢትዮጵያ በኩል ከላይ ባለሥልጣን ሳይኖር እንግሊዝ የራሱን ሰው ሻለቃ (ሜጀር)ግዊን አስማርታ በመሰለው አዘጋጅቶ የነበረውን ንድፍ (ልኬት)ስ?ስእል ዛሬ የሱዳን መንግሥት ያንኑ የሻለቃ ግዊን ንድፍ በዓለም አቀፍ ተዋቂነት ያለው ህጋዊ የአገር ክልል አስመስሎ አቅርቦታል። እንዲያውም በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በጎንደር ክፍለ ሀገር ለሱዳኖች ቅኝ ገዥዎች ካስረከቧቸው ክልል አልፈው በመግባት ብዙ መሬት ይዘዋል።"

"ሱዳንና ኢትዮጵያ በደንበር ያልተወሰኑ አንድ አገር ሁነው ለብዙ ዘመናት አብረው የኖሩ ሲሆን በተለይ ምስራቁ የፍንጂ ክፍል ግዛት ቅኝ ገዥዎች አካባቢውን ወርረው እስከተቆጣጠሩት እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ የግዛት አካል እንደነበር ይታወቃል። ቅኝ ገዥዎች ሕዝቡን የሚለያይ ደንበር ከማብጀታቸው በፊት በመሬቱ ላይ የነበሩ ነዋሪዎች መብታቸው ተጠብቆ ወደየት መወገን እንደሚፈልጉ ተጠይቀው ሳይረጋገጥ ነው። መሬቱ ሲከለል በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ለመከለል ብቃት ያላቸው ባለስልጣኖች ሳይኖሩ በአንድ የእንግሊዝ ሻለቃ ብቸኛ ተካላይ የተሰራው ሁኔታዎችን ያላሟላ ፈጽሞ የማይጸና ዋጋ ቢስ ያደርገዋል። ትናንትና መይሳው ካሳ አጤ ቴዎድሮስ ሰናር፣ወድ መድሀኔ ከካርቱም 180 ኪሎሜትር ምስራቅ በኢትዮጵያ ግዛትነቱ ከቱርክ ተስፋፊዎች ጋር የተዋደቁበት ታዲያ ሻለቃ ግዊን የከለለውን የገዳሪፍንና የደማዚንን አውራጃዎች በሙሉ ወደ ሱዳን ከልሎ ሲያቀርቡላቸው አጤ ምኒልክ አልተስማሙም" ሲሉ ጽፈዋል።

ዛሬ ላለውና ለሚመጣው ትውልድ ማለት የምፈልገው ነገር ቢኖር አጤ ምኒልክ የጌዊንን የድንብር ውል ፈጽሞ አልተቀበሉም። አጤ ምኒልክ ይህን በ1883 ዓም ከጻፉ በኋላ የአድዋ ጦርነት መነሳትና ድል ማድረግ ኋላም እርሳቸው መታመም ሁኔታውን የለዋወጠው ቢሆንም የጊዊንን ካርታ አለመቀበላቸውን ግን የተረጋገጠ ነው። በእጇ ያልገባ ሉንደን የሚገኝ የእኛ



ሰዎች የያዙት ሰነድ እንዳለ ሰምቻለሁ። ምናልባት በቅርቡ የኢትዮጵያ የድንበር ጉዳይ ኮሚሽኑ ያወጣዋል ከተባለው መጽሐፍ ላይ እንደሚወጣ ተነግሮኛል። በዚህ ሰነድም ላይ መሐተሙ ያረፈበት ቢሆንም የፈረመበት ኢትዮጵያዊ አለመኖሩን ተነግሮኛል። ማህተሙም ከሴላ ቦታ የነበረ ማህተም ቢድንች ተነስቶ የተቀመጠ ነው ተብሎም ተነግሮኛል። ይህን የተነገረኝን እንደባለው ይዘን እርሳቸው በጻፉት ላይ ግን ከዚህ መጽሐፍ ከወጣው ሠነድ ላይ ደንበራቸው የት እንደሆነ ዘርዝረው ጽፈዋል። ለዚህም ነው አልተቀበሉም የምለው። እርሳቸው ሲታመሙ የልጅ ልጃቸውን አልጋ ወራሽ ብለው ግንቦት 10 ቀን 1901 ዓም ለሕዝብ ከተናገሩ በኋላ ሲያርፉ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ይህን አውሮፓውያንን ከአፍሪካ ደብድበው ለማውጣት የነበራቸው ምኞት አይዘነጋም። እስኪ ትንሽ ስለኒህ ወጣት ፀረ ቅኝ ገዥ የሆኑትን አገር ወዳድ ታሪክ ስለ እርሳቸው ምን ይላል።

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ <u>የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 115 "ዳግማዊ ምኒልክ በ1906 ዓም በታኅሳስ ወር ከሞቱ በኋላ አቤቶ ኢያሱ ወዲያው በጥር ወር የመልክተኞች መሪ አድርገው ወደ ነምሳ ላኩኝ ይላል ደጃዝማች በላይ አሊ ታሪኩን በመቀጠል እንዲህ አሉ አብረውኝ የሄዱት መልክተኞች ደጃዝማች ተሰማ ገዝሙ፥ልጅ አበበ ወልደ፡ና ልጅ ተፈሪ ቸርነት ናቸው። የነምሳ ሰው ሙሴ ሺሜር መንገድ እንዲመሩንና በሚቸግረን ሁሉ እንዲረዱን አደራ ተብለው ከእኛው ጋር ወደ ነምሳ ሄዱ" ይሉና ገጽ 117 "ያቀረብነው ጉዳይ የጦር መሣሪያ ስለ መግዛት ነበረ። ከአቤቶ ኢያሱ የታዘዝነው አንድ ሙቶ መድፍ ሰባ ሺህ ሚኒሽርና መውዜር ጠበንጃ ጥይትም ለአንድ ጠበንጃ 500 እየታሰበ እንድንገዛ ነው።"

"ደጃዝማች ተሰማ ገዝሙ ጉዳያችንን ለማስረዳት ብዙ ጊዜ ሲናገሩ ሙሴ ሺሜር ንግግሩን እየተረጎሙ ይረዱን ነበር። ከብዙ ንግግር በኋላ መሣሪያውን እንድንገዛ ተፈቀደልን። የመሳሪያውንም ዓይነት አሳዩን። መድፍ ወይም ጠመንጃው አዲስ ዓይነት ነበረ። ከዚህ በኋላ ግን በአገሩ ላይ አንድ አዲስ ነገር ደርሶ ጉዳያችን ለዋወጠው። እኛ እዚያው ቪየና ላይ እንዳለን የነምሳ አልጋ ወራሽና ባለቤቱ ለጉብኝት ወደ ሰርቢያ ሂደው ሳሉ በሰኔ ወር መጨረሻ አደጋ ተጥሎባቸው ሁለቱም ተገደሉ። በዚህም ምክንያት በአገሩ ላይ ጦርነት ሆነ። አሳይተውን የነበረውን አዲሱን ዓይነት መሣሪያ ለነሱ ለራሳቸው የሚፈልጉት ሆነ። ስለዚህም እኛ መግዛት የምንችለው አሮጌውን ዓይነት መድፍና ጠመንጃ መሆኑን አስታውቁን እርሱንም እንኳ ከብዛቱ ቀነሱብን። የሸጡልን ምን ያህል እንደ ነበረ አሁን ዘንግቸዋለሁ። ሆኖም ሠላሳ ሺህ ጠመንጃና አንድ የተራራ መድፍ ይመስለኛል። ጥይትም እንዲሁ በመጠኑ ሸጠውልናል።"

"በቪየና የተቀመጥነው ሰባት ወር ያህል ነው። እዚያው እንዳለን ትልቁ የአውሮፓ ጦርነት የሚጀምር ስለ ሆነ ወደ አገራችን በቶሎ መመለስ አስፈለገን። በጦርነቱ ምክንያት የባሕሩ መንገድ ይዘጋብናል የሚል ስጋት ነበረብን። ሙሴ ሺሜር ቀደም ብለው መሣሪያውን በነጋዴ መርከብ አስጭነው ወደ ጅቡቲ አስተላለፉት። እኛም በሐምሌ ወር መጀመሪያ ትሬስቲ ላይ

በነጋዴ መርከብ ተሣፍረን ወደ ጅቡቲ መጣን፡፡ አዲስ አበባ ስንደርስም የመልክታችንን ሁኔታ ለማስረዳት ከአቤቶ ኢያሱ ፊት ቀረብን፡፡ እሳቸውም ከቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስና ከአቶ ተሰማ እሸቴ ጋራ ሆነው ተቀብለው አነጋገሩን፡፡ ጉዳዩን የሚከታተሉት እነዚህ ሁለቱ ባለሥልጣኖች ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስና አቶ ተሰማ እሸቴ ነበሩ" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ከዳግማዊ አጤ ምኒልክ ወደ ልጅ ኢያሱ ሲሸጋገር እንዳልተለፋለት በማስመሰል አንዳንድ የቤተ መንግሥት ደራሲያን የዛሬውን ትውልድ ለማሳመን ጥረት ቢያደርጉም ቅሉ ወጣቱ (አጤ) ልጅ እያሱ ግን "ይንገሡ" ሲባሉ መልሳቸው "ፈረሴ ምጽዋ ውሃ ሳይጠጣ አልነግስም" አሉ ይህን ያሉትን ጀግና ዛሬ አንዳንድ ሰዎች የሰሩ አስመስለው አያዩአቸውም፡፡ እኒህ ወጣት በ12 ዓመታቸው አልጋ ወራሽ ሲሆኑ ሞግዚት ነበራቸው፡፡ ሞግዚታቸው ሲሞቱባቸው በ14 ዓመታቸው አገር መምራት ሲጀምሩ ቅኝ ገዥዎችን ከኢትዮጵያ ዳር ደንበር መንጥረው ለማውጣት ጥረት ማድረጋቸው ዛሬ ያለውን ደንበር ወሰን ሊቀበሉት ቀርቶ ሕልም እንኳን አላለሙበትም፡፡ ወጣቱ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ቅኝ ገዥዎችን ከምስራቅ አፍሪካ ጠራርገው ለማስወጣት የነበራቸው ምኞት በአውሮፓውያንና ሥልጣን በፈለጉ መኳንንቶች በተለይም በደጃዝማች ተፈሪ ሴረኝነት ሊከሽፍ ቻለ፡፡ በወቅቱ የነበሩት ምኒስተሮች ይንገሡ ሲሏቸው ቅድሚያ የእርሳቸው ዓላማ ምን እንደነበር አሳሰቡአቸው፡፡

ኅበዜ ጣፈጠ <u>አባ ጤና ኢያሱ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 57 "ሚኒስተሮችና መኳንንቶች በቆይታ ተመካክረው ለአቤቶ ኢያሱ የምክር ቃል አቀረቡ፡፡ የምክሩ ቃል ጃንሆይ አጤ ምኒልክ በሕይወታቸው ሳሉ አልገወራሺ ኢያሱ ነው ብለው አስታወቁን፡፡ አሁን እርሳቸው ዐረፉ፡፡ እንግዲህ ምን እስኪሆን እንጠብቃለን የዘውድ በዓልዎ የሚደረግበትን ቀን እንወስንና ዘውድ ደፍተው በአባትዎ መንበረ ዳዊት ይቀመጡልን የሚል ነው፡፡ አቤቶ ኢያሱም ምክራችሁ መልካም ነው፤እኔም ሳላስብበት አልቀረሁም፡፡ ነገር ግን አባቴን ራስ ሚካኤልን በፊት ንጉሥ አሰኝቼ በኋላ ንጉሠ ነገሥት መሆን ይገባኛል ብለው መለሱላቸው፡፡ ከዚያም አያይዘው ፈረሴ ከምጽዋ ውኃ ሳይጠጣ ዘውድ ጭኜ ንጉሠ ነገሥት አልባልም እያሉ መቆየታቸውን የሚታወስ ነው" ሲሉ ጽፈዋል፡፡ እኔ በቅንፍ (አጤ)እያልኩ ነው የምጽፍ፡፡ ይህን ግልጽና ትክክለኛ ታሪክ አቶ ዘውዴ ረታ ውድቅ ሲያደርጉት ይታያሉ፡፡

ዘውዴ ረታ <u>ተፈሪ መኮንን ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 280" ኢትዮጵያ በኮሎኒሊስቶች የተወሰደባት ግዛቶቿ ተመልሰውላት ፈረሴ የምፅዋን ባሕር ውሃ ሳይጠጣ ዘውድ አልጭንም ብለዋል የሚለው ሰበብ መነገር ጀመረ፡፡ በውነቱ እንደዚህ አስበውም ከሆነ ይህን የተለሙትን ግብ ለመምታት ንጉሠ ነገሥት መሆን እንቅፋት ሊሆንባቸው እንደማይችል ማወቅ ነበረባቸው" ሲሉ ጽፈዋል፡፡



(አጤ)ልጅ ኢያሱ አባታቸው ራስ ሚካኤልን ንጉሥ ካሰኙ በኋላ አውሮፓ የጦር መሳሪያ ለማስመጣት መልክተኞች ልከዋል፡፡ የ(አጤ)ልጅ ኢያሱ ዓላማ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር እንዲከበር ከፍተኛ የሆነ ጥረትና ሕልም ነበራቸው ይህን አስመልክቶ አባ ጤና ኢያሱ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 78 "ልጅ ኢያሱ የአባታቸውን የአጤ ምኒልክ የፖለቲካ መስመር ከመከተል አልፈው ዓይነተኛ መመሪያ አድርገውት ነበር፡፡ በዓለም አቀፍ ግንባር ደግሞ በብልሃት በተቀነባበረ የዲፕሎማሲ ትግል አማካይነት የኢትዮጵያን ጠረፎች ከባዕዳን እጅ እንደሚያስለቅቁ ተስፋ ማድረጋቸው አልቀረም" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

የሱማሌን ፀረ ቅኝ ግዥ የሆኑትን ሰብስበው ማደራጀታቸው ወሰናቸውን ለማስከበር ስላሰቡ ነው፡፡ በአሰብ አስተዳደር በአፋር ግዛት ብቻ ከ40 ሺህ በላይ ወታደር ማሰባሰባቸው ከአፋሯ ቆንጆ የወለዱአቸውን ልጅ ምኒልክ ማለታቸው ሕዝቡን ከሕዝብ ለማቀራረብና በሃይማኖት መለያየትን ለማስቀረት ያደረጉት ዓላማ የእርሳቸው ተግባር ሕዝቡ አንዴ ተነስቶ ቅኝ ገዥዎችን እንዲመታ ለማድረግ ስላሰቡ መፈክራቸው "ሃይማኖት የግል ነው አገር የጋራ ነው" የሚለውን ዓላማ ዛሬ አጤ ኃይለ ሥላሴ እንዳሉት ተደርጎ ይሰበካል፡፡ ይህ የአጤ ልጅ ኢያሱ ዓላማ የተረዱት ቅኝ ገዥዎች ልጅ ኢያሱ "ሰልመዋል" ብለው የእርሳቸውንና የእስላሞች ሥዕል+ ፎቶአቸውን ካርቱም ወስደው በነሱ ካሜራ አብረው የተነሱ አስመስለው ለመኳንንቶች አምጥተው ሰጡአቸው፡፡ መኳንንቶችን አጉል እማኝ ነን ባዮች በመነሳታቸው የተጀመረው የደንበር ማስከበሩ ጉዳይ ተረስቶ በርሳቸው ላይ ተዘመተባቸው፡፡

መስከረም 17 ቀን 1909 ዓም ጀምረው አገር ያስተዳደሩት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ናቸው፡፡ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን ኢትዮጵያ ያሰራችው ገጸ ምድር ካርታ አለ፡፡ የሀገር ካርታ አልባ ኢትዮጵያ የመንግሥቱ ማኅበር ዓባል አገር ልትሆን አትችልም፡፡ ካርታ እንደነበራት ኢትዮጵያ በወቅቱ ለመንግሥቱ ሙ'ነበር ጀኔቭ ከጻፈችው ደብዳቤ ላይ ሐምሌ 26 ቀን 1915 ዓም የተጻፈው ደብዳቤ "የአገሪቱ ካርታ" የሚለው ቃል የአገር አንድነት ለመጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ጥረት ተደርጓል፡፡

ኢትዮጵያ ማሟላት የሚገባትን ሕጋዊ ሰነዶች ካቀረበች በኋላ መስከረም 16 ቀን 1916 ተፈቅዶላት የመንግሥቱ ማህበር ዓባል ሆነች፡፡ ምንም እንኳን ይህ ማህበር በ1928 ዓም በመርዝ ስትገደል ባይደርስላትም ሀገሪቱ ከአጤ ምኒልክ ወደ አጤ ልጅ ኢያሱ ከዚያም ወደ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ደርሶ ለማስፋፋት ጥረት ባያደርጉም የተረከቧትን አገር ለማስጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ትግል አድርገዋል፡፡ በእርሳቸው ዘመን የተሰራው ካርታ ዛሬ በዋሽንግተን ዲሲ ታላቁ መጽሐፍት ቤት ይገኛል፡፡ ራስ ተፈሪ መኳንንቶችን ተራ በተራ እያሰሩ አገሪቱን በቻቸውን ለመያዝ ሲያስቡ ብዙዎችን አጠቁ፡፡ ንጉሥ መሆን አለብኝ ብለው በአጫፋሪዎቻቸው በኩል ለንግሥት ተነግሮላቸው የጎንደር ንጉሥ ሁነው ነገሡ በዚያን ግዜ ከቀሩት መኳንንቶች መካከል የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ባለቤት ራስ ጉግሳ ወሌ፤ በመሆናቸው ጠብ ፈልገው ነው፡፡ ንጉሥ

ተፈሪም በጎንደር ላይ ሲነግሱ መተማ ቀረጥ በራሳቸው ቁጥጥር ስር ለማድረግ ወሰኑ። ለዚህም ራስ ጉግሣ ወሌ የማይቀበሉት መሆኑን ገለጹ።

ቀኛዝማች ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም ገጽ 3 "በራስ ተፈሪና በራስ ጉግሣ መካከል ብዙ ችግሮች ተከሰቱ። ያም የዘረፋ ሁኔታም ጭምር ነው። ምክንያቱም የመተማው ግምሩክ ራስ ተፈሪ በራሳቸው ቁጥጥር ስር ለማድረግ ይጥሩ ጀመር። ራስ ጉግሣ በእኔ በገዥው እንጅ በራስ ተፈሪ ቁጥጥር አይሆንም። ማንኛውንም የጎንደር ንብረት እኛ ተረክበን እንደማንኛውም መኳንንቶች ግብር ለመንግሥት እንከፍላለን እንጂ በቀጥታ የራስ ተፈሪ ወኪል መተማ አይቀመጥም አሉ። በዚህ ምክንያት ከራስ ተፈሪ ጋር ተጣሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ በፈረንጅ ሹፌር (አብራሪ) በአየር ተደበደቡ ሞቱ" ሲሉ ጽፈዋል።

ተፈሪ መኮንን ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 296 "ንግሥተ ነገሥታት ሆነው የአባታቸውን ዘውድ የሚወርሱት ወይዘሮ ዘውዲቱ ምኒልክ ከእንግዲህ ወዲህ ሕይወታቸውን ለኢትዮጵያ አገራቸውና ለሕዝባቸው ደህንነት ሠውተው ከምድራዊ ዓለም በመራቅ በጾም በጸሎትና በንጽህና መኖር ስለአሰባቸው ከባለቤታቸው እንዲለያዩ በታላላቆቹና በሃይማኖት አባቶች ተወስኖባቸዋል። ስለዚህ የንግሥቲቱ ባል በመሆኔ በንጉሥ ደረጃ የወርቅ ወንበር ተዘጋጅቶልኝ ተከብሬና ታፍሬ በሰፊው እንደላቀቃለሁ ብለው ሲያልሙ የነበሩት ትልቁ ጎንደሬ እንኳንስ የሥልጣኑና የወጉ ተካፋይ ለመሆን ቀርቶ ከሚስታቸው ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ ለመኖር እንኳ እንዳልተፈቀደላቸው በተነገራቸው ጊዜ ምን ያህል ብስጭት ምን ያህል ሐዘን እንደ ተሰማቸው መገመት ይቻላል"።

ይሉና ገጽ 298" የሸዋ ብልሃት የረቀቀ ስለሆነ ለሕዝቡ የተነገረው ንግሥት ራሳቸው ማንም ሳያሳስባቸው ከእንግዲህ ወዲህ ሕይወቴ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነት ስለሆነ ከዚህ የተለየ ዓለም የለኝም በማለት በጾምና በጸሎት ተወስነው ለመኖር ቆርጠዋል ተብሎ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ንጉሥ ተፈሪ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ዶ/ር አነር በተባለው ሐኪም ገድለው ስልጣናቸው ቁጭ እንዳሉ ብዙ ሳይቆይ የጣልያን ወረራ ብቅ አለ። በዚህ ወቅት አጤው ማይጨው ዘምተው ድል ሆኑ። ጣልያን ለጊዜው ድል ሊያደርግ የቻለው በአየር መርዝ ጢስ ሲሆን እርሳቸው ቤተሰቦቻቸውንና ባለሟሎቻቸውን አስከትለው ለንደን ገቡ። የሆገሬ የፋርጣ አልቃሽ እንዲህ አለች።

በትግሬ በወሎ በጎንደር በጎጃም ቢመጣ መቸ ይገባት ነበር
በሸዋ ወለጋ ኢሉባቦር በከፋ ቢመጣ መቸ ይገባት ነበር
በጋሞ አሩሲ ሲዳሞ በባሌ በሐረር ቢመጣ መቸ ይገባት ነበር
በሰማይ መጣብን በማናውቀው ሐገር" ነበር ያለችው።

በዚህ ወቅት ጣልያን ለአገዛዙ ያልተመቹት 1ኛው የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅድሚያ አሻፈረኝ ብለው ከአገር ልጆች ጋር አብረው



ቆመው ጠላትን ወራሪውን እንኳን ሕዝቡ መሬቷ እንዳትገዛው ብለው ለምዕመናን ልጆቻቸው አስተምረው መስዕዋት ሆኑ። 2ኛው ኢጣልያን ጠላት አድርጋ የተነሳችበት በአማራው ሕዝብ ላይ ሲሆን የአማራ ክፍለ ሀገር ናቸው ከሚባሉት ቀርቶ በሌሎች ክፍለ ሀገር ውስጥ አርበኛ በመሆን ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር ወራሪውን ጠላት ጠዘጠዙት። እንግሊዞች የጌዊን ወሰን እንደያዙ ናቸው። ጅቡቲ ከፈረንሳይ ጋር የነበረውን ወሰን ሲቀበሉ ከሱዳን ጋር በሚዋሰነውን በመያዝ ከውጭ ጋር የሚያገናኘውን እንዳለ አድርገው ሱማሌንና ኤርትራን ከሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች ጋር ደብልቀው በወረቀት ላይ ነድፈው ለማስተዳደር ጥረት ሲያደርጉ ሲጀምሩ ቁርጠኛ የኢትዮጵያ ልጆች በያሉበት ይነድፏቸው ጀመር። በዚህ ወቅት ጣልያን ከጀርመን ጋር ስትሆን እንግሊዞች ቀደም ይጠሉአቸው የነበሩ የኢትዮጵያውን ከአጤው ጀምሮ ወደ ሱዳን ማስገባት ያዙ። አርበኞችንም ማድነቅ ጀመሩ።

የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሰራረት 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 79 "ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛቷ ካርታ ውስጥ ብታስገባትም የአርበኞች ትግል እየጠነከረ በመሄድ ላይ ስለነበረ ጦሯ ከሰፈረበት አካባቢና ከታላላቅ ከተማዎች በስተቀር የኢትዮጵያን ለመቆጣጠር አልተቻለም" ይሉና ገጽ 82 "ሰኔ 10 ቀን 1940 ዓም የኢጣሊያ የጦር አዋጅ አናግራ ከጀርመን ጋር መሰለፏን ለዓለም ይፋ በማድረጓ የኢጣሊያን አዋጅ እንደሰሙ ጀ/ፕላት ለኢትዮጵያ አርበኞች የሚከተለውን መልዕክት አስተላለፉ። ወረቀቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በአውሮፕላን ተበተነ። መልዕክቱም ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ከዛሬ ጀምሮ በእንግሊዝና በኢጣሊያ መካከል ጦርነት ተጀምሯል። የጋራ ጠላታችንን ተባብረን ለመደምሰስ ጠመንጃ ጥይት መድኃኒት ካስፈለጋችሁም ልብስና ምግብ የሚያስፈልጋችሁን ያህል ለማንሳት መልዕክተኞቻችሁ ወደፊት በሚነገራችሁ ቦታና ጊዜ እንዲያገኙ የሚል ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ከበደ ተሰማ የታሪክ ማስታወሻ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 206 "በማግሥቱ ዱካን ለቀን ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ጉዞዋችንን ቀጠልንና ሐምሌ 25 ቀን 1932 ዓም የሱዳንን ወሰን አልፈን በኢትዮጵያ መሬት ገባን" ሲሉ ጽፈዋል። በወቅቱ ሱዳንን ይገዙ የነበሩ እንግሊዞች ቀደም ሲል ብቻቸውን ወስነው ደንበራችን ካሉት ላይ ቁመዋል። ኢጣሊያን በወረቀት ላይ ይሳል እንጂ ወደ ደንበር ብቅ አላለም። እንግሊዞችም አገሯ ደከማለች ብለው አዲስ መስመር ለመስራት አላቀዱም። በዚህ ወቅት ነው ደካዝማች ከበደ ተሰማ ከኢየሩሳሌም ካርቱም ከዚያም ገዳሪፍ ብሎም ዱካ ወደ ኢትዮጵያ ሊገቡ የመጡት።

ሕይወት ጎዳና ያቺ ቀን ተረሣች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 400 "እንግሊዞች ሸፍቶች እያሉ ይጠሩን የነበረውን አሁን ቃላቸውን ለውጠው የኢትዮጵያ አርበኞች በሁሉም በኩል ኢጣሊያንን አጣደፋት እያሉ በሬዲዮን ሳይቀር ይናገሩ ጀመር" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ ላይ ሲጤን የሚገባው ጉዳይ አለ።

# ክፍል ሶስት

## ምዕራፍ 1

## የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን

ንጉሥ ተፈሪ አጤ ኃይለ ሥላሴ ተብለው ከስልጣን ከወጡ ጀምሮ ከላይ የተዘረዘረው እንዳለ ሁኖ እንደገና አንድ አድርገው ለማስተዳደር ጥረት ሲደረግ የወሰን ጉዳይ አንዱ ዋና መሆኑን ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ገልጸዋል። ከዚህ ላይ አጤ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ከበደሉት ይልቅ የሰሩት ይበልጣል። መቸም እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሌም መጥፎውን አጉልቶ ማሳየት በሀገራችን የተለመደ መሆኑ ባይካድም ከዚህ በታች የሚተነተነው የክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ለድንበር ማስከበር መሳካት አጤው መልካም ፈቀዱ ሳይኖር በስልጣናቸው ሊሰሩት እንደማይችሉ ግልጽ ነው። በእርግጥ የወጣቱ የሕግ ምሁሩ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ብስለት መኖር እንዳለ ሁኖ የአጤ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ ሳይጨመርበት ግቡን ሊመታ አይችልም። የክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ፣ ጹሑፍ እንደሚያመለክተው አጤ ምኒልክ ከተለያዩ የቅኝ ገዥዎች መንግሥታት ጋር የተዋዋሉትን ውል እርሳቸው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት የሰሩትን ጽፈዋል። አጤ ምኒልክ ጋንቤላን በውል የሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል። ያም እንግሊዞች ከሱዳን ሲለቁ ጋንቤላን ለኢትዮጵያ ሊያስረክቡ የተስማሙ መሆኑን ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ለደርግ መርማሪ ኮሚሽን የአስረከቡት በ57 ገጽ ሰነድ ዋቢ ነው። ከዚህ ከክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተ ወልድ ጹሑፍ ደንበርን በተመለከተ እርሳቸው የጻፉትን ብቻ ሰብስቤ ጠቅለል አድርጌ ከዚህ መጽሐፍ ላይ አቅርቤዋለሁ። ከዚህ በታች የጻፉትን ሰነድ ከመጻፌ በፊት አንዳንዱ ቃል ግልጽ ያልሆነውን ( )በቅንፍ እጽፋለሁ። ምክንያቱም ለወደፊቱ ዋናው ተገኝቶ ለማመሳከር ይቻል ይሆናል በማለት ሲሆን አንዳንድ ቃላት ፈረንሳይኛና እንግሊዘኛ ቋንቋ አለበት።

### "በኢትዮጵያና በፈረንሳይ ሱማሌ ጠረፍ"

ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ <u>መስከረም 10 ቀን 1967 ዓም ለመርማሪ ኮሚስዮን ያቀረቡት ጹሑፍ</u> በተባለው መጣጥፍ ገጽ 46-50 "አፋምቦ አመላለስ በምን አኳኋን እንዳስመለስኩ፤ አፋምቦ በኢትዮጵያና በፈረንሳይ ሱማሌ ጠረፍ አጠገብ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ስትራቴጂክ የሆነ ሥፍራ ነው። አውሳንና የፈረንሳይን ሱማሌ ተራራማ በመሆን ኮንትሮል የሚያደርግ ውሃም ያለበት በጣም ጠቃሚ ስፍራ ነው። ፈረንሳይም ሁል ጊዜ የጅቡቲ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ወደ አውሳና (ድሬዳዋ) ነበር አይናቸውን



የሚያዘነብሉት በ1906 የፈረንሳይና እንግሊዝ ጣልያን ኢትዮጵያን በዞን ለመከፋፈል ያደረጉት ውል ማየት በ1944 ውል በኋላ እንግሊዞች ኢትዮጵያን ለቀው ሲሄዱ ፈረንሳይዎች አፍምቦን መያዛቸውን ተእንግሊዞች ሰሜን የፈረንሳይን አምባሳደር ጠርቼ ፕሮቴስታሲዎን አድርጌ በተሉ እንዲለቁ ብጠይቅ አገሩ የፈረንሳይ ስለሆነ አንለቅም አሉ። ተጃንሆይ ጋርም ተመንግሥት ጋር ተመካከርኩ። በኋይል ለመውሰድ ያን ጊዜ ራስ አበበ የጦር ሚኒስትር ነበሩ። ኃይል በዚያን ጊዜ ጅቡቴ ታሉት ፈረንሳዮች ጋር ለመዋጋት የሚበቃ እንደሌለ አስረዱኝ። ሃሳቤ ጅቡቴንም ለመያዝ ነበረ። ምንም በኃይል አለመቻሉን ሲታወቅ በዲፕሎማስ ብቻ የተቻለውን እንዳደርግ ታዘዝኩ"።

"የፈረንሳይን አምባሳደር ጠርቼ እናንተም የኛ ነው ስትሉ እኛም የኛ ነው ስንል የሚለየን በእኛ በኢትዮጵያ መካከል የተደረገው የጠረፍ ውል ነው። ተውሉ ጋር የተያያዘ ካርታ የስዕል ካርታ የሚባል አለ። ስለዚህ አሁኑኑ አንድ ስምምነት ፕሮቶኮል ፈርመን የሚለየን ለማድረግ እንስማማ ይህንንም ስናደርግ አፍምቦ በውነት የማን እንደሆነ ይታያል አልኩት! እሱም በመንግሥት ስም አሁን ጦርነት ላይ ነው ያለነው ይህንን ለማድረግ ጊዜም የለ አፍምቦንም አንለቅም አለ። እኔም አገራችን ይዘን አንለቅም አገሩ የማን እንደሆነ ለመነጋገር ስምምነት ለማድረግ አንድ በስምምነት እናድርግ ብንል እምቢ ታላችሁ የፈረንሳይን አምባሳደርነትህን ፕረቭልጅ ሁሉ እንሰቻለሁ ይህንንም የምናደርገው በመጨረሻ (በቪቪረሽም) ጊዜ እናንተ የኢትዮጵያን ነፃነት እናውቅም ብላችሁ የጣልያንን ይዞታ አውቃችሁ ነበር። እናንተም በጀርመን (ልፋት)" ኃይል ይሆን እንደሆን የእኔ ነው " ስለተያዛችሁ የፈረንሳይን ነፃነት አናውቅም። ያቀረ ብትሉን የውል ሀሳብ መንግሥትህ ተቀብሎ ለመፈረም ፈቃደኛ የሆነ ጊዜ ስምምነቱን ስንፈርም አንድ መግለጫ እናወጣለን ይኸውም ኢትዮጵያንና ፈረንሳይ በአፊሲኤል እንደ ፀና አገርና መንግሥት የሚተዋወቁበት እስከዚያ ድረስ ግን እንደ ፕራይቬት ሰው ነው የምንመለከትህ ብዬ ማናቸውንም ፕሮቪልጅ አነሳሁ። ባንዴራ ማድረግ D.C አቶሞቢሉ ላይ ማድረግ እንዲከለከል ለፖሊስ ነገርኩ። ይህም የዲፕሎማቲክ ዶሜኒቲ መነሳት ለመንግሥቱ አስታወቀ መልሱን ሲጠባበቅ ቆየ"።

"ተትንሽ ቀን በኋላም ፈረንሳይ መንግሥት ደጉል በሀሳባችን ተስማምቶ ውሉን እንዲፈርም አዘዘው አምባሳደሩም ሙሴ ደ.ብሊስ ይባል ነበር። በዚህ አኳኋን ፕሮተኮሉንም ሁለት (--) የሚተዋወቅበትን አብሮ ተፈረመ። ያጤ ምኒልክን ውል መሠረት በማድረግ የውሉ ዓመት በፈረንሳይ በሱማሊና ለማድረግ በሁለቱም በኩል ኮሚሲዎን ተቋቋመ። በኛ በኩል እነኮሎኔል እርገቱ አቶ አበበ ገ/ጻድቅ ነበሩ። ኮሎኔል ክፍሌ አሁን ደጃዝማች ያን ጊዜ የጸጥታ ኃላፊ ነበር። በሥራው ጊዜ የገጠመን ችግር! በካርታ ሥራ ምንም ፕሬዚዎን-የሴላው በጣም ሽግ የሆነ አገሩን ሳያየው እቤቱ ቁጭ ብሎ ወሰኑ በዚህ በዚህ ሥፍራ እንዲህ ያለው ስም ባለው ተራራ ያልፋል እያለ ነው ያሰመረው። እቦታው ላይ ሲኪድ ፈረንሳይዎች ተብዙ ጊዜያት ጀምረው ሁሉ ምስክሮች ቢቀርቡም ሁሉም ለነሱ ጥቅም በሚሆን አኳኋን (የሉይክን) ስም ጭምር ሁሉ ምስክሮች ቢቀርቡም ሁሉም በነሱ የተገዙና አፍምቦ የፈረንሳይ ነው እያሉ የሚመሰክሩ ሆኑ። እኛ

ደግሞ የኛ መሆኑን የሚያስረዳ አንድም (ኤንስቶሊሽን) ቤት ሠፈር የመሰለ ያደረግነው የለም። በዚህ አኳኋን ስሙም ተለውጦ ወደነሱ ስለሚያደርገው ምስክር ሁሉ የነሱ ስለሆነ የምንከራከርበት መንገድ አጣን"።

"በዲፕሎማቲክ ቃልሆነ በቀር በውሉ መሠረት የደምቡን ማግኘት የማይቻል መሆኑን ተተረዳሁ በኋላ ፓሪስ ሄድኩ እዚያም ተጠቅላይ ሚኒስትሩ መሲረኒ ማየር /ወዳጅ ነበር) ተገናኘቼ ሁሉንም አስረዳሁት። ፈረንሳይና ኢትዮጵያ ተድሮ ጀምሮ ያላቸው ወዳጅነት በፈረንሳይ ጥቅም በኢትዮጵያ ባቡር የጅቡቲ የኢትዮጵያ ኔቸራል ብር የፈረንሳይ አርኪዎሎጂ ሚሲዮን እንዲሁም የፖስተር ኢንስቲትና የፈረንሳይ ሉሲ መኖር ይህ ሁሉ እያለ ፈረንሳይ በአፍምቦ ምክንያት ከኛ ጋር መጣላት ጥቅም እንዳልሆነ እሱም በነገሩ አስብበታለሁ ብሎ ምላም ጋብዞኝ በሁለተኛው ቀን ተውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጋር ተሙሲ በዶ ጋር እንድነጋገር ለሱም ትዕዛዝ መሰጠቱን በቀጠሮውም ተበዶ ተገናኝተን ተነጋገርን። እሱም ወደኛ ተመልሶ ዲሊሚቴሽን እንዲደረግ መስማማታቸውን አስታወቀኝ። በንግግሩም ጊዜ አቶ አበበ ገብረ ጻድቅ የሚያስፈልገውን (ዶክሚ) ይዞ ተኔ ጋር ፓሪስ ይገኝ ነበር። በዚህ አኳኋን በፈረንሳይ ሱማሌና በኢትዮጵያ መካከል ውሉን ተከትሉ አፋምቦን ወደኛ አድርጎ የዲሊሚቴሹኑ ሥራ (በ--ተጀምሮ በ--)አለቀ/ዶኩሚንቱን ማየት/ ያን ጊዜም የፈረንሳይ ጋዜጦች የፈረንሳይ መንግሥት ያደረገውን ክሪቲክ አድርገው አገር በማይገባ ለኢትዮጵያ ተሰጠ ጃንሆይና አክሊሉ የፈረንሳይ ጠላት ናቸው...የሚል ካምፓኝ አድርገው ነበር። በፓርላማም ጉዳዩ ተነስቶ ክርክር ተደርጎ ነበር /ይህ ሁሉ ፈረንሳይ አርሺብ ይገኛል።/" ሲሉ ጽፈዋል።

## "ጋምቤላ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ያደረግሁት"

ንጉሠሴዎን 1954-557 በአጤ ምኒልክና በእንግሊዞች መካከል የሱዳንና የኢትዮጵያን ድንበር በተለይ የሚወስነው (በ---)የተፈረመው ውል የሚለው ጋምቤላ በእንግሊዞች እጅ ይቆያል ይኸውም እንግሊዝ እሱዳን እስካለች ድረስ ነው የሚል ነበር። በ1954 ተጃንሆይ ጋር እንግሊዝ የኀበኘን ጊዜ ለሚስተር ኤደን ጉዳዩን አነሳሁበት። ሱዳን በቅርብ ጊዜ ነጻ መሆኑ አይቀርም። ስለዚህ በውሉ መሰረት አሁኑኑ ጋምቤላን ብታስረክቡን በማለት! እሱም የሱዳን ነጻነት ገና ነው ሁለትና ሶስት ዓመት ቢያንስ ይወስዳል በውሉ መሰረት ሱዳንን እስከምንለቅ መጠበቅ አለባችሁ ብሎ አጥብቆ ተከራከረ። እኔም ሱዳን ነጻ መንግሥት እስክትሆን ጠብቀን በኋላ ተነሱ ወንድሞቻችን ጋር ጋምቤላን አስረክቡን እያልን መጣላት አንፈልግም/እናንተ መቼም ይህ ነው ሥራችሁ ስለዚህ አሁኑኑ አስረክቡን ብዬ አጥብቄ ጠየቅሁ። በመጨረሻም አንድ ፎርሙላ ላይ ስምምነት አድርገን ተለያየን። ይህም/ሱዳን ነጻ ተመውጣቱ ከሶስት ወር በፊት ጋምቤላን ለማስረከብ ሁለት መንግሥታት ተነጋግረው ጋምቤላን እንዲያስረክቡ።"

"ከሶስትና አራት ወር በኋላ አዲስ አበባንና ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ማርሻል ቲቶ ስለመጡ ተሳቸውና ተጃንሆይ ጋር ለጉብኝት ምጽዋ እንገኝ ነበር።



በረዲዎን ስንሰማ ታምስት ቀን በኋላ እንግሊዝ ለሱዳን ነጻነቷን የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ነበር። ሁለትና ሶስት ዓመት የተባለው ሁሉ ውሸት ሆነ። ጋምቤላን ሳይለቅ ለሱዳን አስረክበው ሊሄዱ መሆኑንና ተሱዳንም መንግሥት ጋር ኮንፍሊክት ክርክር እንደሚሆን ገልጾ ነበር። ጉዳዩን ለጃንሆይ አስረድቼ ወዲያውኑ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ/አርብ ቀን ነበር አንድ ኖት አሰናድቼ ቅዳሜ የንግሊዝ አምባሳደር ጠርቼ ኖቱን ሰጠሁት። የኖቱም ቃል የሚለው/ በውሉ መሰረት ጋምቤላን እንግሊዞች የሚይዙት ሱዳን እስካለ ድረስ ነው አሁን እንግሊዞች በድንገት ሱዳንን ስለሚለቁ በውሉና ተሱዳን ጋር በተስማማነው መሰረት ተሰኞ ጀምሮ/ የሁለት ቀን በኋላ/ ኢትዮጵያ ጋምቤላን ይይዛል/የሚል ነበር። እሱም ፕሮቴስ አድርጉ ለመንግሥተ የኖቱን ቃል አስተላልፋለሁ አለ።"

"ለሱዳን የውስጥ አስተዳደር ባለስልጣኖችም አንድ ቴሌግራም በአቶ መለሰ አንዶም በኩል/ያን ጊዜ የእንግሊዝን ኦፊሰር አሁን ካይሮ አምባሳደር/ አንድ ቴሌግራም ላክሁ ይህም የሚለው ለነጻነታችሁ ጥልቅ መልካም ምኞታችንንና ወደፊትም እንደወንድማማች አብረን እንድንሰራ! ጋምቤላ በኮሎኒአሊስቶች በኃይል ተይዞብን ስለነበር ተሰኞ ጀምሮ አኩፓይ ማድረጋችንን ግን ይህ ወዳጅነታችንን የማይነካና የሱዳንም ቆንሲልና ማናቸውም ቤትና ኤንስቶሌሽን ቢኖር ለጊዜው ለመቆየት መቻሉን የሚገልጽ ነበር። እነሱም በነጻነታቸው ለጊዜው በደስታ የተጥለቀለቁ ስለሆነ ተምስጋና ጋር በምናደርገው መስማማታቸውን የሚገልጽ መልስ ሰጡ።"

"እንደተባለው ሰኞ ባቅራቢያው የሚገኘው የፖሊስ ኃይል ጋምቤላ ገብቶ የኢትዮጵያን ባንዲራ አውለበለበ አድሚኒሴራሲዮኑንም ያዘ ምንም ኤንስደንት አልደረሰ። ተሶስት ወር በኋላ የሱዳን ዲሊጊሽን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሚመራ ጋምቤላ ስላላቸው ኤንስታሴሽን ለመነጋገር አዲስ አበባ መጡ። በንግግራችንም ጊዜ በቁጣ መልክ ለእንግሊዞች የፈቀዳችሁትን ጋምቤላን ለምን ለኛ ለአፍሪካኖች ተነፍጉናላችሁ ጋምቤላን መልሱልን በማለት ከሥረ ነገሩ መግባት ጀመሩ። እኔም እንግሊዞች ኮሎኒያሊስቶች አፍሪካን በሚከፋፈሉበት ጊዜያት በኃይል ፕሬሽን ያደርጉብን ነው አሁን ኮሎኒ ሁሉ ነጻ ይውጣ ሲባል እናንተ ይህን እንዴት ትጠይቃላችሁ ይልቅስ በወንድማማች መንፈስ የምትወስዱትን ኢቃ ዝርዝር ብንነጋገር ይሻላል ስትመጡም በዚህ ብቻ መሆኑን የተለዋወጥነው ኖት ያስረዳል።"

"ተዚያ በቀር ሌላ ጉዳይ ለመነጋገር የተስማማንበት ፕሮሲጀር አይፈቅድም አልኳቸው እነሱም ተቆጥተው ስብሰባውን ጥለው ወጡ/ ያን ጊዜ ተኔ ጋር ብላታ ዳዊት ምክትል ሚኒስትር እንዳልካቸው ዋና ዲሬክተር ነበሩ። በዚሁም እንዳልካቸው ደንግጠ ምን ይሆን ብሎ ጠይቆን ነበር ግድ የለም አሁን እንስማማለን ስለው እኔ መቼም ኤክስፔርያንስ የርስዎን ያህል የለኝም ብሎ አድንቆ ተወጡ በኋላ ለየአምባሳደሮች/ እንግሊዝ.አሜሪካን.እየዞሩ ስሞታቸውን ያቀርቡ ጀመር በኋላም እሱን ለብቻው ጠርቼ በረጅሙ አስረድቸው ተቆጣው ተመለሰ። አስፈላጊውን ስምምነት አደረግን ተዚያ በኋላ የጋምቤላ ጉዳይ በሱዳኖች ተነስቶ አያውቅም"።

## "በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል"

"በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል የሚወሰነውን ወሰን መሠረት በምን አኳኋን እንዲከለል እንዳደረግሁ እውጭ ጉዳይ እንደገባሁ ኢትዮጵያ ተሌሎች አገሮች ጋር ወሰን በኢንተርናሽናል ውል መሠረት በትክክል መወሰን ዋና ጉዳይ አርጌ ነበር ያየሁት። ይሂም በወልወል በደረሰብን ኤክስፔሪያንስ ነው። ተዚያም በኋላ ያፋምበ መጣ ትንሽ መንግሥት እንደመሆናችን መጠን የተከበብነው ያን ጊዜ በነኛው በኮሎኒያሊስቶች ስለሆነ አጥራችንን ደህና አርጎ ማጠር አስፈላጊ ነበር። ብዙ ጊዜ የወሰኑ ውል ታጤ ምኒልክ ጋር የተደረገው/+1897-/በገ የሆነ ፕረሴዜዎን የሌለው ነው። ኢትዮጵያ ተመወረሯ በፊት 1935 ታንድ አገር ብቻ ነበር ወሰናችን የተከለለው። ይኸውም ተእንግሊዝ ሶማሌ ጋር ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ነው ተጎረቤት አገር ጋር በየጊዜው (የፍርንቲኤር) ኤንሲደንት የነበረን/በኬንያ በኩል ተናንተ ጋር ያለ ኤንሲዴንት ፕሮቲስታሲዎን ያደረግንበት ወረቀት ይህን ቤት ይሞላል ብሉኝ ነበር። ይህን ሁሉ ለጃንሆይ ታስረዳሁ በኋላ መጀመሪያ ሉንደን ስሄድ በ1946 አንዱ ጉዳይ የተነጋገርኩበት ይህ ነበር። ተኔ ጋርም ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ነበሩ። ዲማርኬሽን ለማድረግ የንግሊዝ መንግሥት ተስማምቶ ይህንኑ ለመነጋገርና አንድ የዲሊጌሽን ፕሮተኮል ለመፈራረም በቅርብ ጊዜ አንድ ዲሊጌሽን ወደ አዲስ አበባ እንዲሚልክ አስታወቀ"።

"የእንግሊዝ ዲሊገሽን ተመጣ በኋላ ውሉን መሠረት በማድረግ ካርታ ላይ መስመሩን ለማስመተር አንድ ተእነሱና ተእኛ የተዋጣ (ኪሚስስድ)ኮሚሲዎን ተቋቋመ። ሥራቸውንም ጀመሩ። ተእኛ በኩል እነ ኮሎኔል ክፍሌ አቶ አበበ ገብረ ጻድቅ ሌሎችም ነበሩ። ብዙ ጊዜም ሥፍራውን እየሄዱ ይጎበኙ ነበር። በመጨረሻም የተስማሙበትን መስመር ለየመንግሥታቸው አቅርበው ተፈቀደ። ተዚህም በኋላ መሬቱ ላይ ዲማርኬሽን ተጀመረ። ብዙ አመትና ብዙ ገንዘብም ተፈጀ በኋላ ሥራው አለቀ። ተትንሽ ዓመት በኋላ ቀደዱማ የሚባለው የውሃ ጉድጓድ ሕዝቡ ጠቃሚዎችን ነው እንደ አድባርም የምንቆጥረው ነው ብሉ አቤት ስላለ ጉዳዩ እንዲታይ ተደረገ በኮሚሲዎን። የጉድጓዱ አከፋፈል የሚበልጠው ወደኛ እንዲሆን ዘጠኝ ሥፍራ ያለው ጉድጓድ ለነሱ ደግሞ ሁለት ሥፍራ ያለ ጉድጓድ ነበር። ሐሳቡ ውሃ እናወጣለን በማለት የእኛም የነሱም ሕዝብ ወሰን እንዳያልፍና ኤንስዴንት እንዳይነሳ ነው። በዚህ ጉዳይ የሕዝቡ ስሜት ስለባሰበት ቀደዱማን እንዲመልሱ ለእንግሊዞች አስረዳኋቸው። እነሱም የሚበቃ ውሃ ተኛ ይበልጥ አላችሁ ግን እንስብበት ምን ታደርጋላችሁ በሱ ፈንታ የሰጠነውን ያገር ክፍል መልሱና እኛም ቀደዱማን እንመልስ ብለው ጥያቄያቸውን በጉድ ፈዝ ተቀበሉ። በዚሁ አኳኋን ጉዳዩ ተፈጽሞ የዚያን ክፍል እንደገና ወረቀት ላይ ምልክት እንዲደረግ ሆነ"።

"ተዚያም በኋላ ታመታት በኋላ ኬንያ ነጻ ስትወጣ ድንበራቸውን ተከልሉ ስስለቆየ ተኗ ጋር በወዳጅነትና በወንድማማች መንፈስ እስታሁን እንኖራለን። ተፈረንሳይ ሱማሌ ጋር ያለን ወሰን እላይ በተባለ አኳኋን ስለተወሰነ <u>ተእንግሊዝም ሱማሌ ጋር ያለው ተጦርነት በፊት</u> አለቀ። ተኬንያም ጋር በዚህ



አኳኋን ሲያልቅ የሚቀረን ተጣልያን ሱማሌና ተሱዳን ጋር ነው። ተጣልያን ሱማሌ ጋር ያለንን ለመወሰን ገና ሱማሌ በዩናቲድ ኔሽን ሞግዚትነትና በጣልያን አስተዳዳሪነት ባለች ጊዜ ተ1950-1960 ዩናይትድ ኔሽን ሬዞሌሽን *እንደሚያዘውና በሱም መሠረት ለመወሰን ተጣልያኖች ጋር ብዙ ጉባኤ ተደርጎበታል። ብዙም ተደከሟል። ያን ጊዜ የኛን ዲሊጌሽን ለወሰኑ ጉዳይ የሚመራው አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ ነበር። ጣልያኖች የውሉን ትርጉም ኢንተርፕረቴሽን በማይገባ እየለወጡ ጉዳዩን ይጎትቱ ነበር።ያልተስማማንበትን በሬዞሌሽኑ መሰረት ወደ አርቤትረጅ ለፍርድ ብዙ ታክቲክና ሳቦታጅ እያደረጉ* ጉዳዩን ይጎትቱት ነበር።ሁሉንም ለመረዳት (ፕርስሼርባሱንና) የዩናይትድኔሽን ዶክሜንት ማየት ያስፈልጋል። ለዚህ ሁሉ አቤቱታችንን ለሰላም ማሕበር ማቅረብ አላቋረጥንም። ጉዳዩም ሳያልቅ ሱማሌ ነጻ ወጣች 1960 ጣልያኖች ጉዳዩን የሚጎትቱበትን አንድ ምክንያት ሱማሌዎችንም በመፍራት ነበር።"

## በጣልያን ሶማሌና በሱዳን በኩል ያልዘጉት ፋይል!

"ሱማሌ ነጻ ተወጣች በኋላ ወሰኑን ለመከለል በየጊዜው ፕሮፖዛል አቅርብንላቸው ነበር። የነሱም መልስ ኡጋዴን የኛ ስለሆነ አንዋሰንም ነው። በሱዳን በኩል ያለውን ብዙ ጊዜ ተተነጋገርን በመሰረተ ስምምነት ላይ ደርሰናል። ዶክሚንቱን ማየት" ሲሉ ጽፈዋል። ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉን ተክተው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት አቶ ከተማ ይፍሩ ሳይሆኑ አይቀርም። አቶ ከተማ ይፍሩ ደንበርን በተመለከተ የፈጸሙት ተግባር እንዳለ እርሳቸው ጽፈው የተዉት ሰነድ አላገኘሁም። ሌላው ብዙ ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቆይተዋል የሚባሉት ክቡር አቶ ምናሴ ኃይሌ ናቸው። አሜሪካ የሚኖሩ ሲሆን የሚያውቁትን እንደ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ እርሳቸው ቢጽፉ ታሪክ ቢናገሩ መልካም ነበር። ነገር ግን እንደሰማሁት ከሆነ ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም ተብሉ ነው። ምናልባት እርሳቸው በሕይዎት እያሉ የሚያውቁትን ቢጽፉ ሳይሻል አይቀርም። ምክንያቱም ቀስ እያለ በመውጣት ላይ ያለው "የአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች የጎንደርን መሬት ለሱዳን ሰጥተው ነበር" የሚለው ታሪክ እየወጣ ብልጭ ማለት ስለጀመረ የሚያውቁትን ቢጽፉልን መልካም ይሆናል። ከዚህ በመቀጠል በጣልያን ሶማሌ በኩል በእንግሊዞች የተተበተበውን፤ደግሞም የሶማሌ ኢትዮጵያውያን ማህበር ከኢትዮጵያ ጋር በፌሬዴሽን አብረን እንሁን ብሎ ያቀረበውን ጥያቄ ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ስላልተቀበሉ ሶማሌዎች ሲበሳጩ እንግሊዞች አንድ መርዘኛ ዘር ዘሩ።

ዶክተር ባሕሩ ዜ ድሌቦ <u>የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም</u> 1900-1966 መጽሐፋቸው ገጽ 159" ከዚህ በላይ የተነገሩት ማህበሮች የዋናውና የምክትል መሥሪያ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ሥራ አስኪያጆች በግንቦት 27 ቀን 1938 የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርነስት ቤቨን በአገሩ ፓርላሜንት ባደረገው ንግግር ከኢትዮጵያ የኦጋዴን ግዛት ጨምሮ በአፍሪካ ቀንድ በተለያዩ አካባቢዎች የተከፈሉ የሶማሌ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚገኙባቸው ቀበሌዎች በእንግሊዝ አስተባባሪነት በአንድነት መደራጀት አለባቸው በማለት

እስከዛሬ ድረስ በአፍሪካ ቀንድ መንግሥታት መካከል የፖለቲካና የአካባቢ ችግር ሲያስከትል ያለውን ጠንቀኛ አሳብ መሰንዘሩ ይታወሳል" ሲሉ ጽፈዋል። በሱማሌ በኩል ኢትዮጵያን እንደጠላት ማለየት ስለተጀመረ ነው ከላይ ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ "ሱማሌ ነጻ ተወጣች በኋላ ወሰኑን ለመከለል በየጊዜው ፕሮፓዛል አቅርብንላቸው ነበር። የነሱም መልስ ኦጋዴን የኛ ስለሆነ አንዋሰንም ነው" ያሉት ቅኝ ፈኘዎች የጋቷቸውን በመያዝ ነው።

ከዚህ ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 157-159 "የኢትዮጵያ የአገር ውስጥና የውጭ ጉዳዮች እንደዚህ ሆነው ሳሉ በእንግሊዝ ጦር ባለሥጣኖች በሚተዳደረው ሱማሊያ በሚያዝያ 27 ቀን 1935 የአገሩ ዜጎች የሶማሌ ወጣቶች ክበብ የሚል ማህበር አቋቁመው ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ለመሆን እንፈልጋለን በማለት ለእንግሊዙ ዋና አስተዳዳሪ ዊክሐም ጥያቄ አቀረቡ። አጤ ኃይለ ሥላሴን ንጉሣችን ናቸው ብለው ተናገሩ። በተጨማሪም በዘመኑ ለኢትዮጵያና ለሶማሊያ አንድነት የሚታገል በሶማሌ ተወላጅ ኡማር ኢብራሂም መሪነት የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነት ማህበር ተቋቁሞ አገርና ዓለም አቀፍ ትግል ያካሄድ እንደነበር አይዘነጋም በዚህ ወቅት የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነትን በሚመለከት የሱማሌዎች ጩኸት በሚል ርዕስ የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነት ማህበር በቀድሞ ኢጣሊያ ኮሎኔዎች ሊቢያ ኤርትራና የኢጣሊያ ሶማሊያ ጉዳይ ላይ በመስከረም 1939 በፓሪስ ከተማ ለተሰበሰበው የተባበሩት መንግሥታት ማህበር ያቀረበው የአቤቱታ ጥያቄ እንደሚከተለው ይነበባል በማህበሩ ቃል"

"እኛ የኢጣሊያ ሶማሊያ ይባል የነበረው ሱማሌ ተወላጆች ስለሰላምና ስለዓለም ሕዝቦች ነጻነት በፓሪስ ከተማ ጉባኤ ላሳችሁ ባለቃልኪዳን መንግሥታት ከእናት አገራችን ጋራ አንድ እንድንሆን ቁርጥ አሳባችን መሆኑን እየገለጽን ያገራችን ዕድል እስከ አንድ ዓመት ድረስ እንዲቆይ የቀረበውን አሳብ በፍጹም የማንቀበለው መሆናችንን በማክበር እናመለክታለን። በዘር በልማድ በባህል በታሪክ በኃዘን በደስታ ኢትዮጵያውያን ነን። እናት እያለችን ሞግዚት ልንቀበል አንችልም። ጉባኤው ሳይመለስ የኢጣሊያ ይባል የነበረው ሱማሌ ከእናቱ ከኢትዮጵያ ጋር አንድነትን እንዲያገኝ እንጠይቃለን። ፊርማ የኢትዮጵያና የሱማሌ አንድነት ማህበር ፕሬዚዳንት ኡማር ኢብራሂም"።

"የኢትዮጵያና የኤርትራ አንድነት ማህበርና የኢትዮጵያና የሱማሌ አንድነት ማህበር በሕብረት ከአዲስ አበባ ለፓሪሱ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ያቀረቡት የአቤቱታ ቃል ደግሞ እንደሚከተለው ይነበባል። በማህበራቱ የሕብረት ቃል። በኢትዮጵያ የኤርትራ አንድነት ማህበርና የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነት ማህበር ፓሪስ ላይ ለዕርቅ ወደ ተሰበሰቡት ለሃያ አንድ መንግሥታት እንደራሴዎች የተላከ! አቤቱታ! ክቡር ሆይ! ይህን የፈረምነው የኢትዮጵያና የኤርትራ አንድነት ማህበር እና የኢትዮጵያና የሱማሌ አንድነት ማህበር አባሎች ለኤርትራና ለሱማሌ ሕዝብ ሥቃይ ፍጻሜ እንዲደረግለት ለከፍተኛው ዕውቀትዎና ለትክክለኝነት መንፈስዎ ለሂሊናዎዎ ከዚህ የሚከተለውን አቤቱታ በማክበር ከእግርጌዎ አቅርበናል። በምሥራቅ



አፍሪቃ ጦርነቱ ከተፈጸመ አምስት ዓመት ሆኖታል። ነገር ግን በታሪክ በኹምግራፊ በትውልድ በጥሬት በአስተዳደሪ በመንፈስ የኢትዮጵያ የሆኑት በእንግሊዝ የጦር ኃይል አይሮፕላኖች በየቦታው በተበተኑት ጹሑፎች ነጻነት ከእናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር አንድ እንዲሆኑ ተስፋ ሰጥተዋቸው የነበሩት ኤርትራና ሱማሌ ጦርነቱ ስላልተፈጸመ በእንግሊዝ አስተዳዳሪነት ውስጥ የቀሩ ሁነዋል። የእነዚሁ አውራጃዎች ሕዝብ ይህንኑ አስተውለው የባለቃል ኪዳኖችን ድል መንሳት በፍጹም ልባቸው በመመኘትና በጸሎት በጸጥታ ጠበቁ። አገራችን ባለቃ ልኪዳን አባል ሆኖ ባለቃል ኪዳኖችም በ1945 (1937) ድል አደረጉ። ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል መፍቀዳቸውን ከመለመን አንድ ጊዜ እንኳን አቋርጠው ስለማያውቁት ስለኤርትራና ስለ ሱማሌ ሕዝቦችም የዕድላቸው ሁኔታና ገና በባለቃልኪዳኖች መወሰን ያለበት ጉዳይ ነው ተባለ"።
"ክቡር ሆይ! ኤርትራና ሱማሌ ሕዝብም መሬቱም በማናቸውም አስተያየት ኢትዮጵያዊ መሆንና ሕዝቡ አንድነት ሁኖ በፍጥነት ከኢትዮጵያ ጋር የመዋሐድ ምኞቱን ሲገልጽ መኖሩን መላልሰን እናስታውቃለን። እንዲህ ከሆነም ሕዝቡ ጠባብ በሆነ ወታደራዊ ደንብ አስተዳደር ሁልጊዜም በመጠራጠር ሌላ ረጅም ዘመን መኖር አይችልም። ከእናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር መዋሐድ በፍጥነት በመወሰን ለሥቃያቸው ፍጹም እንዲደረግ ከፍ ወዳለው ዕውቀትዎ አቤቱታችንን እናቀርባለን። ሕዝቡ ከሥቃይ ነጻ መሆን የሚገባው ጉዳይ በፍጥነት መወሰን እንደሚገባው ለማስረዳትም በቅርቡ ጊዜ አሥመራ ላይ የደረሰውን መዓት የሚነገር ጹሑፍ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከንልዎታል፤ ፊርማ" ይሉና" ከዚህ በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር አራቱ ኃያላን የአሜሪካ የሶቪዬት፤የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በመስከረም በፓሪስ ጉባኤ ተሰብስበው የቀድሞ የኢጣሊያ ኮሎኔዎች ጉዳይ ከየካቲት 1939 ጀምሮ በአንድ ዓመት በአራቱ ኃያላን መንግሥታት የጋራ ስምምነት ባያልቅ በመስከረም 1940 ለመንግሥቱ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ሙሳኔ ለማቅረብ እንደተስማሙ ይታወሳል። የኢትዮጵያና የኤርትራ የኢትዮጵያና የሱማሌ አንድነት ማህበራት በሕብረት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የአቤቱታ ድምጽ ለመንግሥታቱ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ በመስከረም 1939 አሰሙ"።

"እስከ 1940 ድረስ ሁሉ የሶማሌ ተወላጆች ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን አንድ ለመሆን ጥረት ያደረጉ እንደነበር ታውቋል። በዚህ አኳያ በመጋቢት 1933 የሶማሌ ወጣቶች ክበብ በአብዱልቃድር ሰኸውዲን መሪነት ራሱን የሶማሌ ወጣቶች ሊግ በማለት በአዲስ ስያሜ አደራጀ። በሀጂ ኢብራሂም ቃል የሶማሊያ ወጣቶች ሊግ መሥራች አብዱልቃድር ሰኸውዲን ለኢትዮጵያ ስለሶማሌ የወደፊት ፌዴሬሽን ጉዳይ ከለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ጋር ውይይ ለማድረግ የሊጉን የመልእክተኞች ቡድን አስከትሎ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የሊጉን የፌዴሬሽን አሳብ ባለመቀበላቸው የሊጉ ቡድን ከአዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላ በሊጉ በቢሮው ሰቅሎት የነበረውን የአጤ ኃይለ ሥላሴ ፎቶግራፍ አውጥቶ ጣለ"ብለዋል።

## ምዕራፍ 2

## ባለሥልጣኖች በጎንደር መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ማቀድ!

አዛውንቶች ጨዋታው ሞቅ ሲል አንዱ ልክፍክፍ አድርጎ ሲተወው "እያ ንገረን እንጂ የሚያስተምር ከሆነ እንማርበት የሚያስቅ ከሆነ እንሳቅበት ፥ ውሃን ከምንጩ ነው" ይላሉ:: ዋናው የዚህ መጽሐፍ መነሻ መሬት ስለሆነ የአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች ለሱዳን መንግሥት የጎንደርን መሬት ለመስጠት ቃል ገቡ የተባለው ሐሜት ሳይሆን እውነት ሳይሆን አልቀረም:: ታዲያ "ውሃን ከምንጩ" እንዳሉት መንስኤውን ፈልጌ ለማግኘት ብዙ ጥረት አድርጌአለሁ::

የሰማኋቸውን ሐሜቶች ለዚህ ምዕራፍ ማዳበሪያ እንዲሆኑ አድርጌያለሁ:: ሐሜቱን ለማረጋገጥ ብዙ ሰዎች ጥያቄ አቅርቤ ነበር:: ነገር ግን 12 ሰዎች ብቻ ሳስቀር ሌሎችን አልጠቀስኩም::ከ12 አንዱ ስማቸው እንዲነገር አይፈልጉም:: በእርግጥ ከሌሎች የበለጠ ታሪክ ያለው ከኒህ ግለሰብ መሆኑን ተረድቻለሁ:: ከነዚህ ሰዎች አነጋገር የተረዳሁት ነገር ቢኖር 3 ዓይነት ምክንያት መኖሩን ነው:: በዚህ በ3 አይነት ምክንያት መሬት ለሱዳን ሊሰጥ የታቀደ መሆኑን ነው:: እነዚህ 3 አይነቶች ምክንያቶች ከተለያዩ ክፍለ ሀገር ተወላጆች የተገኘ ነው::

አንባቢያን እነዚህን 3 ምክንያቶች ለያንዳንዳቸው ኒውስ አርዕስት በመስጠትና ዋቢ መጽሐፍት በመጥቀስ ከዚህ በታች እጽፋለሁ::

1ኛ "አጤ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ከሆኑ ጀምሮ ፀረ ጎንደር አቋም ነበራቸው ስለዚህ ጎንደር መሬቱ ለሱዳን ቢሰጥ እርሳቸው አይገዳቸውም" ይላሉ::

2ኛ "ባለስልጣኖች በደቡብ ኢትዮጵያ ቀላድ እንደጣሉበት ሁሉ በጎንደር በተለይ ቆላው ላይ ቀላድ ሊጥሉበት ወሰኑ:: ነገር ግን ጎንደሮች ከአጤ ኃይለ ሥላሴ÷ቀርበው ውሳኔው እንዲነሳላቸው ስላስፈቀዱ ባለሥልጣኖች ተናደዱ:: ስለዚህ የአገሪቱን ካርታ ለሱዳን በ250 ሺህ ብር ሸጡ "ይላሉ::

3ኛው "የአጤው ባለሥልጣኖች ከሱዳን መንግሥት ጋር ተነጋገሩ:: ያም ጀብሃን ሆነ ሌሎች ኢትዮጵያውያን የትጥቅ ትግል እንዳይሞክሩ ለማድረግም ጭምር ነው" ይላሉ::



## ምክንያት አንድ

ዳኛው ወልደ ሥላሴ ውጣ ውረድ የበዛበት ሕይወት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 25" በ1965 ዓም በጎንደር የታወቁ ባሕታዊ በየቦታው ሕዝብ በተሰበሰበበት ሥፍራ እየተገኙ ንጉሠ ነገሥቱን ሸዋ ሊገድላቸው ስለሆነ ወደ ጎንደር ቢመጡ እርሳቸውም ተርፈው ተለምነው ወደ ዙፋናቸው ይመለሳሉ ይህም ከሆነ በኢትዮጵያ ላይ የሚደርሰው እልቂት ይቀራል:: እያሉ ሲሰብኩና ሲያስተምሩ ታሪኩን ከ/ታምራት ይገዙ ሰምተው ለንጉሠ ነገሥቱ አድርሰው ሰውየውም የታወቁ ባሕታዊ መሆናቸውን ጭምር ገልጸው ደጋግመው ቢያሳስቡም ንጉሠ ነገሥቱ የጎንደርን ሕዝብ በድየዋለሁ አሁንም ደግሞ መልሼ ወደዚያ አልሄድም ሲሉ ጥያቄውን ሳይቀበሉት መቅረታቸውን" ሲሉ ጽፈዋል:: የጎንደር አባቶች አጤ ኃይለ ሥላሴ የጎንደርን ሕዝብ በድለውታል ይላሉ:: በዚህና በሌላው ምክንያት የጎንደር ሕዝብ ፀረ አጤ ኃይለ ሥላሴ ቅስቀሳ ሲያደርግ የነበረ መሆኑ ዛሬ ድረስ በሕይወት ያሉ ይመሰክራሉ:: የጎንደርን ሕዝብ አጤ ኃይለ ሥላሴ የበደሉት መሆናቸውን አስመልክቶ ከላይ ክቡር አቶ ዳኛው ወልደ ሥላሴ እንደገለጹት አጤውም አልካዱም::

የእርሳቸው አስተዳደር በጎንደር ሕዝብ ላይ ከ1933-1966 ዓም የልጅ እንዳልካቸው ካቤኔ ሲመሰርቱ ጄኔራል ነጋ ተገኝን መሾማቸው ካልሆነ በቀር 9 የክፍለ ሀገሩ ጠቅላይ ገዥዎች ተሹመው የሚመጡት ከአዲስ አበባ ሲሆን የጎንደር ሕዝብ በጉቦ ተዘርፎአል:: ይህን ጉዳይ በግልጽ ቀኛዝማች ምስጋናው ማስንቆአቸውን ሲቃኙ ክብር ተመስገን የኛ ጌታ ብለው አምላክን ካመሰገኑ በኋላ ስለጎንደር ሕዝብ በጉቦ መሰቃየት ሳይገልጹ ወደ ሌላ ጨዋታ አይገቡም ነበር:: ቀኛዝማች ምስጋናው፤
የጠገበው ሲሄድ የራበው ሲመጣ
ለጎንደር የሚያስብ እንዴት ሰው ይታጣ
ሁሉ በሽተኛ ሁሉ ራሴን ባይ
መልካም ሰው ለጎንደር ላይሾም ነው ወይ?
ሲሉ የክፍለ ሀገሩን ችግር ቁልጭ አድርገው ይናገሩ ነበር:: በዚህና በሌላውም ጉዳይ የጎንደር ሕዝብ በተለያየ ግዜ መሸፈቱ ይታወቃል:: በአጤው አስተዳደር ላይ ሲሸፍቱ ኘሽን ጢስ ወጋው እንደሚባለው ሕዝቡን አብረው ይገርፉትም ነበር:: በተለያየ ጊዜ የሸፈቱት የጎንደር ተወላጆች የአጤ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር በድሎናል በማለት ነው::

<u>የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሠራረት</u> 1855–1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 58 "ሰሜን ጎንደር ሕዝብ አስተዳደሩን በመቃወም የጎበዝ አለቃ ፊታውራሪ አጥናፉ መሸሻን መርጦ ከፍተኛ የተቃውሞ ውጊያ አድርጎአል" ሲሉ ጽፈዋል:: እኔ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ የተማሪው ማሕበር ወቅት በተለያዩ ክፍለ ሀገር የነበሩትን የሕዝብና የመንግሥት ችግሮች ዘርዝሮ ሲጽፍና የትግል መፈክር አድርጎ ሲነሳ

በጎንደር በኩል የደረሰውን ሳይጽፈው የቀረው ለምን ይሆን? ከታች የአቶ ነጋ ነወጠን በመንግሥት ተቃውሞ አድርገው በጹሑፍ አስረድተው በርሃ ገብተው የመንግሥት ወታደር ዘምቶ ሊይዛቸው ባለመቻሉ አጎታቸው ቢትወደድ አዳነ መኮንን በሽምግልና ማስገባታቸው እየታወቀ ሌላም የሕዝብ እንቅስቃሴ እንደነበር ግልጽ ሳለ ዝም የተባለበት ጉዳይ ሊገባኝ አልቻለም።

ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ ከንቲባ ገብሩ ደስታ የኢትዮጵያ ቅርስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 320-321 "በሐምሌ ወር 1940 በበጌምድር ጠቅላይ ግዛት የስሜን አውራጃ ሕዝብ የተጣለበትን ግብር እንደበዛበት ገልጾ እንዲቃለልለት አቤት ቢል ተገዶ እንዲከፍል ስለተወሰነበት መሪዎቹን መርጦ በመንግሥት ላይ ጦሩን አነሳ። በዚህን ጊዜ ሊያስገድዱት ጦር ሠራዊት ይዘው የሄዱትን የአውራጃውን ገዥና የወረዳ አስተዳዳሪዎች ድል አድርጎ ማርኮ በየዋሻው አሠራቸው። ሕዝቡ እንደማይገብር ከታወቀ በኋላ የታሰሩት እንዲፈቱ የተማረኩትም እንዲለቀቁ በሽምግልና ከስምምነት ቢደረስም ጦር ሠራዊት በብዛት ተልኮ ጦርነት ታዘዘበት። በዚህ ጊዜ መኮንን ጋረድ ሲዋጉ ሞቱ። ፊታውራሪ አጥናፉ መሸሻ ግን የተቻላቸውን ያህል ከተዋጉ በኋላ የተወሰኑ ሰዎች ይዘው ጦር ሠራዊቱን ወረው ንብረቱንም ዘረፉት። ከዚህ በኋላ አሥራ ሁለት ዓመት በሽፍትነት አገሩ ውስጥ እየተዘዋወሩ ቆይተው በምህረት ገቡ። በደጅ ጠኝነት ጥቂት ጊዜ አዲስ አበባ አሳልፈው ወዳገራቸው ተመለሱ። ፊታውራሪ አጥናፉ በሸፈቱበት ሰዓት በፈቃድ አዲስ አበባ ቆይቼ ስመለስ ስለፀጥታው ሁኔታ ሲመክሩ የነበሩት ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ፤ጄኔራል መርድ መንገሻና ኮሎኔል ክፍሌ ዳዊት ገብሩ ጎንደሬ ስለሆን ምሥጢር ተካፋይ ሆኖ ፀጥታው ሊጠበቅ ስለማይችል በምትኩ ሌላ መኮንን ይምጣ የሚል ሀሳብ አቀረቡ። ስለዚህ እኔ ወደ አዲስ አበባ ተጠርቼ ወደ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ስዛወር ኮኔል ይማም ጎሹ በምትኬ ወደዚያ ተላከ ዘመኑም 1941 ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ብ/ጄኔራል መልኬ ጌታሁን የትግል ፍጻሜ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 221 "ከቡር ጄኔራል ደበበ ኃይለ ማርያም የምድር ጦር ዋና አዛዥ ሁነው ከተሾሙበት ቀን ጀምሮ በመሃንዲስ መምሪያ ያለኝ አገልግሎት ጊዜ እንዳለቀ ለመገመት አዳጋች አልሆነብኝም። የትውልድ አገራቸው ጎንደር የሆኑትን መኮንኖች አይወዱም እየተባለ በሰፊው ሲነገር እሰማ ነበር። በኋላ ግን የምድር ጦር ዋና አዛዥ ሁነው ከተሾሙ በኋላ በራሴ ላይ የደረሰውንና ከዚህ በፊት የሰማሁትን ሳመዛዝነው ትክክለኛነቱን ለማመን ችያለሁ" ይሉና ገጽ 258 "ይህን እንደመንደርደሪያ ጠቀስኩት እንጂ ብዙ የተዛባ አሰራሮች ነበሩ። ለምሳሌ አገራችን በጭንቅ ላይ በምትገኝበት ሰዓት በቅናትና በምቀኝነት ተገፋፍተው ጄኔራል ነጋንና እኔን ከሶስተኛ ክፍለ ጦር ለማንሳት የተደረገውን ርብርብ ሳልጠቅሰው አላልፍም። ደጋግሜ መናገር አይሁንብኝ እንጂ ሶማሌ የሶቬት ህብረትን ከጀርባዋ አድርጋ የአገራችንን ወሰንና ክብር ትደፍራለች ተብሎ ከፍተኛ ሥጋት ስለነበር ኤርትራ ውስጥ ከሚገኘው ከ2ኛ ክፍለ ጦር በቀር በሙሉ ወደዚህ ግንባር ተደራቢ እየሆኑ መጥተዋል። የቀሩትም ቢኖሩ ተዘጋጅተው ለርዳታ እንዲጠብቁ ተደርጓል። ስለዚህ የኢትዮጵያ የጦር



ሠራዊት በሙሉ በኛ ትዕዛዝ ስር ነበር ማለት ትቻላል። ይህ በኛ ላይ ጥላቻ ባላቸው ሰዎች ዘንድ ለአገር አደገኛ መስሎ ታያቸው። አገራችን ያሳትን ጦር በሙሉ ለሁለት ጎንደሬዎችና ለክብር ዘበኛዎች አስረከብን በአንድ ሌሊት ገስግሰው አዲስ አበባንና እኛንም በቁጥጥራቸው ስር ሊአውሉን ይችላሉ እያሉ መንግሥት ለመገልበጥ እንደተነሳን እያስመሰሉ ያስወሩብን ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ሽኩም የማይከብደው ሕዝብ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 107 "በጎንደር ዝርፊያ ብዙ ባለሥልጣኖች እጃቸውን ሰድደዋል። የንጉሡ ዋና አድራጊ ፈጣሪ የነበሩና ባለሟል ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ሳይቀሩ የማይገባ ተግባር ፈጽመዋል። በግብፅ አገር የተማሩ ግብፆችና ሱዳኖች አፈንዲ የሚሏቸው ብላታ ፀሐይ ደስታ የጎንደር ግምጃ ቤት ሹም በነበሩበት ጊዜያት ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ በጎንደር ሆስፒታል ውስጥ የነበረውን ሕሙማን የሚታከምበትን መድኃኒት በ13 መኪናዎች አስጭነው ወደ አዲስ አበባ ሊወስዱ ሲሉ ወልደ ጊዮርጊስ ለሸዋ ሲያስብ እኔ ደግሞ ለጎንደር ማሰብ አለብኝ ብለው መድኃኒቱ እንዳይሔድ በመከልከላቸው ብላታ ፀሐይ ደስታ ከሹመታቸው ተሽረው በአገሪቱ ከፍተኛ የተማረ ሰው እጥረት በነበረበት ወቅት ወደ አዲስ አበባ ተወስደው በደጅ ጥናት እየተንገላቱ ዕድሜያቸው በአሳዛኝ ሁኔታ ተፈጽሟል። ተገኝ ሐበሻ የተባሉ ዳኛ ከአዲስ አበባ ዳኝነት ተሹመው ወደ ጎንደር ተልከው ሕዝቡን በጉቦ ስለ አስቃዩት ቀኛዝማች ምሥጋናው አዱኛ በሰምና ወርቅ ግጥማቸው

"ሰው ሁሉ እሚቀኜው እየቆጠረ ነው
አዘራረፍ ማወቅ እንደ ተገኜ ነው

ብለው ተቀኝተዋል። ከአዲስ አበባው መንግሥት በአስተዳዳሪነትም ይሁን በዳኝነት ተሹሞ ወደ ጎንደር የሄደ ሁሉ አንዱ ከሌላው የማይሻል ዘራፊና ቀማኛ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ስሜ አይነገር ያሉ አዛውንት "አጤ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ጎንደር ሲባሉ ሳለ ራስ ጉግሳ ወሌን በአውሮፕላን አስደብድበው ገድለዋቸዋል። ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር ቤተሰቦቻቸውን በመያዝ ከዱ። ከእንግሊዝ ተመልሰው በጎንደር ለመግባት ሲያስቡ የአርማጭሆ አርበኞች "የከዳ ንጉስ መልሶ አይነግሥ" በማለት መልክተኞቻቸውን አላስገባም በማለታቸው አጤው በጎንደር ላይ ቂም ያዙ። ጎንደር የነበረው ከጠላት የተማረከው ንብረት ልቅምቅም አድርገው ወሰዱት። ሊወሰድ የማይችለውን ጣልያን የሰራውን ቤት እንኳን እንዲፈርሱ ሆነ። በ1939 ዓም ጎንደር ቢመጡ ተነስቶ የሚሄድ ቢሆን የፋሲል ግንብ አዲስ አበባ በወሰድነው ብለው በመናገራቸው በጎንደር ላይ የነበራቸውን ጥላቻ ያመለክታል። አንዳንድ ሰዎች አጤው ጎንደርን ይወዳሉ ለዚህም በቤተ መንግሥቱ ብላታ አድማሱ በቤተ ክነቱ ሊቀ ሥልጣን አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህን በአየር ኃይል ጄኔራል አሰፋ አየነውን በወታደሩ ጄኔራል ነጋ ተገኝን እንዲቀርቡ አድርገዋል ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥቱ የቀረቡት ተወደው ሳይሆን ሕዝቡን ዝም ለማሰኘት ይቻላል ተብሎ በመታሰቡ ነው። ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም እንደሆኑ ሙሉ በሙሉ ጎንደሬም

አይደሉም ትግሬና የሸዋ ሰው ናቸው:: ሌሎች በጎንደር ላይ የሚደረገውን ሴራ የሚቃወሙ ሁሉ በዓይን ቁራኛ ሲጠበቁ መቆየታቸው አይዘነጋም:: የአጤው ባለሥልጣኖች በጎንደር ላይ ከነበራቸው ጥላቻ ብዛት የተነሳ የጎንደርን መሬት ለሱዳን ሊሰጡ የተስማሙት በገንዘብ የሸጡ በሕይወት አሉ:: እግዚአብሔርን ካልፈሩ ሊመሰክሩ ይችላሉ:: ይህ የመሬቱ መሸጥ ምክንያት ነው ሕዝቡ እንዲሸፍት ያደረገው" ሲሉ ነግረውኛል::

ስማቸው እንዳይነገር የፈለጉት አባት "አጤ ኃይለ ሥላሴ ገና ንጉሥ ሳሉ ጀምሮ ጎንደሮች ባንድ እንዳይቆሙ ለማድረግ ከፍፍሉን በንቀት ጀመሩት:: በጌምድሬውን "ፋርጣ" ይሉታል:: ፋርጣ ማለት የደብረ ታቦር የአውራጃው ከተማ ወረዳ ሲሆን ራስ ጉግሣ ወሌ ቤተ መንግሥታቸው የነበረው ደብረ ታቦር ሲሆን የስሜን ጎንደር ሕዝብ አብሮ እንዳይቆም በጌምድሬውን እንዲንቀው አደረጉ:: ከዚያም ደጃዝማች አያሌው ብሩ አጎታቸውን ራስ ጉግሣ ወሌን አብረው ወግተው ገደሉ:: ለደጃዝማች አያሌው ብሩ የተገባላቸው ቃል ኪዳን ስሜን ጎንደርንና በጌምድር ጎንደርን ራስ ተብለው ያስተዳድራሉ ተብሉ ነበር:: ራስ ጉግሣ ከሞቱ በኋላ ግን የተሰጣቸው ነገር የለም:: ለዚህም ነው የጎንደር ተጨዋቾች ማፈዝያ ቀኛዝማች ምስጋናው እያለው ሞኝ ሰው አማኙ ሰው አማኙ ካለ በኋላ ዘፈኑን ሲያስሙቁ ሰው አማኝ ሸዋ አማኝ ሸዋ አማኝ ይሉ ነበር:: የጎንደር ሕዝብ አንድ ሁኖ እንዳይቆም ቀደም ጀምሮ ስሜነኛው በጌምድሬውን እንዲንቀው ለማድረግ ብዙ ደክመዋል:: ብዙ ጥረዋል ነገር ግን ሁሉም ጎንደሬው አዲስ አበባ ሲገባ ፋርጤ ይባላል:: በዚያን ወቅት የዘሩት ዘር ዛሬ ድረስ ሊደርቅ አልቻለም:: በጎንደሬዎች በኩል መተማመን እንዲጠፋ እያደረጉ ናቸው:: ይህን የአጤ ኃይለ ሥላሴን ሴራ ደርግ ደምስሶ አንድ ጎንደር እንጂ ሁለት ጎንደር አይባልም ብሎ አጥፍቶት ነበር:: ዛሬ ደግሞ ወያኔ የአጤውን ሴራ አንስቶ በማራገብ ላይ ነው:: አንዳንድ የዋሕ ሴራው ያልገባቸው በበጌምድሬው ላይ ጥላቻ ያሳያሉ ይህ ተንኮል እንጂ እንኳን የጎንደር ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነው:: አስተውሉ ይህ ሴራ የተጀመረው ቀደም ሲል መሆኑን ተረድታችሁ ጎንደሬዎች እንጂ ስሜንና ደቡብ የሚባለውን ስያሜ ማጥፋት ይኖርባችኋል" ሲሉ ነግረውኛል::

ጎንደር ከ7 ጎሳ በላይ ሕዝብ የያዘ ሲሆን ሕዝቡም የተዋሐደ ነው:: እንኳን የጎንደር ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሕዝብ እንጂ አንዳንድ ፖለቲከኞች እንደሚሉት የተለያየ ሕዝብ አይደለም:: በአስተዳደር ጉድለት ነበር ይህ ሊካድ አይችልም ትክክል ነው:: ዛሬ ሰልጥነናል የሚለው ትውልድ በተለይም ከዚህ በውጩ ዓለም ያለው ሕዝብ ይህን ከፋፋይ ሴራ ማምከን ይጠበቅበታል:: እኔ የስማሁትን መጻፌ ለምክር ያመቻል በሚል እንጂ ቂምን ለማራገብ አይደለም:: በአንድ አካባቢ ስህተት ተፈጽሟል ብሎ መጻፍ ቂመኛ አልያም ከፋፋይ ሊያሰኝ አይችልም:: የአሜሪካ ሕዝብ በጥቁር ላይ በደል ያደረሰ መሆኑን ነጮች ታሪክ በመሆኑ እየነገሩ ነው:: ይህን የሚሉት ሌላ ስህተት እንዳይፈጸም ለማድረግ ያለፈን ታሪክ ጠብ ርግፍ አድርገህ ትተህ ለሚመጣው እጅና ጓንት ሁነን አገራችን እናሳድግ ለማለት ነው::



ለዚህም ነው የአሜሪካ ሕዝብ "ምን ይሰራልኛል እንጂ ምንድነው ቀለሙ" የሚለውን ትቶ እንሆ አቶ ራክ ሁሴን አባማን ለርዕሠ ብሔርነት መረጠ:: ከዚህ በላይ የጠቀስኩት የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በጎንደር ላይ የፈጸሙትን የዛሬው መንግሥት እየፈጸመው በመሆኑ ያነን ለአንባቢ ዘርዝሮ ለማቅረብ ነው:: ይህ በዚህ እንዳለ የአጤው መንግሥት በጎንደር ላይ ቀላድ ሊጥልበት ወሰነ:: ቀላዱን የማይቀበሉ መሆናቸውንና የአጤውን አስተዳደር በመንቀፍ በአቶ ነጋ ነወጠ፣አመጽ በስወር ተካፋይ የነበሩ የሚያውቁትን የነገሩኝን ለአንባቢ አቀርባለሁ::

## ምክንያት ሁለት

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ "በኢትዮጵያ የክፍለ ሀገረ ገዥዎች ስብሰባ ላይ ያልተያዘ መሬት ያላችሁ ተብሎ ጠይቀው ነበር:: በዚህ ወቅት የጎንደር ክፍለ ሀገር ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ በጎንደር ትርፍ መሬት የለም ብለው መለሱ:: በኋላ ግን እርሳቸው ተነስተው ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ጎንደር ጠቅላይ ገዥ ሁነው ሲመጡ አሁንም ይህ ጥያቄ ሲመጣ እርሳቸው ያልተያዘ መሬት እንዳለ ገለጹ:: እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ በጎንደር ዙሪያ አውራጃ ገዥ የነበረው ግለሰብ በራሱ አውራጃ ብቻ ያለውን ሳይሆን በጭልጋ አውራጃ በጎንደር ዙሪያ አውራጃና በወገራ አውራጃ ያለውን የበርሃውን መሬት ሳይቀር ግልጥልጥ አድርጎ ማስታወሻ ወደ አዲስ አበባ ላከ" ሲሉ ገልጸውልኛል:: የኒህ ግለሰብ አባባል የሚያጠናክር ምስክር አገኘሁ::

በአቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌና አቶ ሊቁ እጅጉ ተመሳሳይ ታሪክ ነግረውኛል:: "የአገር ግዛት ሚኒስትር ያልተያዘ መሬት መኖሩን አስታውቁን የሚል ደብዳቤ ጎንደር ላከ:: ቀደም ሲል ጎንደር ዙሪያ አውራጃ ገዥ የነበሩት የአጤ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ደጃዝማች ካሣ መሸሻ ቴዎድሮስ ትርፍ መሬት የለም እያሉ ይጽፉ ነበር:: ኋላ እርሳቸው ጡረታ እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ተሰፋዬ አሰናቀ የጎንደር ዙሪያ አውራጃ ገዥ ሁነው ሲሾሙ ከሁመራ እስከ መተማ ያልተያዘ መሬት መኖሩን ዘርዝረው ለአገር ግዛት ምኒስትር ጻፉ:: ከዚህ በኋላ የአዲስ አበባ ባለሥልጣን መሬቱን ቀላድ ሲጥሉበት ወሰኑ:: የባላባት ስለሆነ ቀላድ አትጥሉብትም ብለው ተቃውሞ ማሰማት ጀመሩ:: ይህን ይቃወማሉ የተባሉት ግለሠቦች ከክፍለ ሀገሩ እንዲነሱ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር እንዲዛወሩ ተወሰነ:: ለምሳሌ አቶ ነጋ ነወጠ፣ ወሎ እንዲዛወሩ የተጻፈላቸውን ማዘዣ ሳይቀበሉት ቀርተዋል:: በጎንደር ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን የሁመራውን በተመለከተ ደግሞ መላዕከ ሰላም ሲሳይ አየለ ከዚህ በታች የተጻፈውን ተናግረው ነበር:: እኔ ጉግሣ መጽሔት ሳዘጋጅ ላሰ አቶ ዋዲት ከበደ ነበሩ ጥያቄና መልሱን ሰርተው የላኩልኝ:: ጥያቄ የምለው የአቶ ዳዊት ከበደ ሲሆን መልስ የምለው ደግሞ የመላከ ሰላም መሆኑን ማስገንዘብ እወዳለሁ::

መልዓከ ሰላም ሲሳይ አየለ <u>ጉግሣ መጽሔት</u> ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ገጽ 12" ሆኖም ሁኔታው ጥሩ ስላልነበረ የወልቃይት ባላባቶች እና ሌሎችም አብረው መከሩና የኔ ታናሽ ወንድም አብሮ ነበር እንድነት መክረው የመሬቱን

እርስትነት ቢጠይቁ በወቅቱ የወልቃይትን መሬት ያካፋፍሉ የነበሩት በየቦታው ያሉ የጭቃ ሹሞች መሬቱ በቀላድ የሚመራ እንጂ በባላባት ርስትነት የሚመራ አይደለም አሉ:: ጥያቄ በቀላድ የሚመራ ሲሉ ምን ማለት ነው? መልስ "በቀላድ የሚመራ ማለት መሬቱ በመንግሥት የሚተዳደር ማለት ነው:: በውኃላ ጉዳዩ ጎንደር ላይ እየታየ ሳለ ደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ መሬቱ የወልቃይት ርስት መሆኑን አስመስክረው ያንን የምስክር ወረቀት ይዘው ወደ ጎንደር ሳይሄዱ ክረምት ሆነ በነሀሴ ደግሞ ተሁመራ ወደ ጎንደር መገናኛ የለም:: በዚህ መሀል ጎንደር ላይ ወልቃይት በመንግስት የሚተዳደር ነው:: ተብሉ ውሳኔ ተሰጠ ይሄ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አዲስ አበባ አቤት ለማለት ሄድን:: እኔም ጭምር ያለሁበት ነው:: አዲስ አበባ መጣን:: ከዚያ የአገር ግዛት ሚኒስትር ምላሹን ስንጠብቅ ሶስት ወር ሞላን:: ከሶስት ወር በኋላ በወቅቱ ሚኒስትር ዴኤታ የነበሩት ደጃዝማች ሰለሞን አብርሃ ምንም ሳይፈርሙ አቤቱታችሁን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ክቡር አክሊሉ ሀብተ ወልድ አስተላለፉ:: እዚያም ምላሽ ሳይሰጠን ዘገየ:: ወደ ቢሾፍቱ ሄድን:: ጥያቄ ቢሾፍቱ ማለት ደብረ ዘይት? መልስ አዎ ደብረ ዘይት::"

"ጥያቄ እዚያ ለምንድነው የሄዳችሁት? መልስ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቤት ለማለት ነዋ! ጃንሆይ ወደ ቢሾፍቱ እንደሚሄዱ ቀደም ስላወቅን መንገድ ላይ ጠብቀን ችግራችንን የወልቃይትን ጉዳይ አስረዳን:: ጃንሆይም ቤተ መንግሥት ቅረቡ ብለውን ሄዱ:: ሆኖም ግቢ ሳንቀርብ በፊት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረብነው ደብዳቤ ምላሽ መጣ:: ጥያቄ ምን ተብሉ? መልስ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ዴኤታ ሰዩም ሀረጎት ፊርማ ወልቃይት በነበረበት አስተዳደር ይቆይ የሚል ውሳኔ ተሰጠን:: እኛም ቤተ መንግሥት ቀርበን አቤቱታችንን ለጃንሆይ ሳናቀርብ ወደ ጎንደር ተመለስን:: ጥያቄ ውሳኔው በዚያው ፀና? መልስ ከዚያ ደግሞ በ1959 ዓም ጃንሆይ ወደ አስመራ እንደሚመጡ ሰማንና ወደ አስመራ ሄድን:: አስመራ ጃንሆይ ፊት ቀረብን:: አሁንም ያንኑ የወልቃይትን ጉዳይ አንስተን ርስታችን ነውና ይመለስልን ብለን ጠየቅን:: በዚህን ጊዜ ጃንሆይ ይሂ ጥያቄ በየሄድንበት እየቀረበ ነው ይላሉ:: በዚያን ጊዜ የጎንደር ጠቅላይ ገዥ የነበሩት ኮሎኔል ታምራት እዚያው ስለነበሩ ተነስተው ርስታቸውን የወሰደባቸው የለም ይላሉ:: ጃንሆይ እንዴት ነው? ብለው ግራና ቀኙን ሲጠይቁ በወቅቱ የኤርትራ አገረ ገዥ የነበሩት ልዑል ራስ አስራተ ካሳ እኔ አገሬ ነው አውቀዋለሁ!በቤጌምድር እና በስሜን በቀላድ/በመንግሥት የሚተዳደር መሬት የለም:: የባላባት ርስት ነው:: ብለው ለጎንደር ባላባቶች መሰከሩ:: በሌላም በኩል ራስ እምሩ እኔም አውቀዋለሁ፣ቆላው ሆነ ደጋው የባላባቱ ርስት ነው አሉ:: ጃንሆይም በሄሊኮፍተር ቦታው ድረስ ሄደው አዩ:: እኛ ሳናውቀው ይሄ ሁሉ ልማት እየተካሄደ ነው ብለው ተገረሙ::"

"ጥያቄ መሬቱንስ ለመንግሥት ወይስ ለባላባቱ ወሰኑ? መልስ በ1959 በጥር ወር ላይ እንግዲያው እንደጥንቱ በባላባት ይተዳደር አሉ:: ከዚያ በኋላ እስተ ደርግ ጊዜ ድረስ የጎንደር ርስት ሆኖ ቆየ:: ትናንት እኮ ነው ወያኔ ገብቶ! ጥያቄ ያን ጊዜ ታዲያ የናንተ ክርክር የትግራይ ነው ወይም የጎንደር የሚል አይደለም? መልስ የጎንደር ለመሆኑማ ማንም ክርክር የሚያነሳ የለም::



በአውሬ የተሞላ ጥቅጥቅ ያለ ደን ነበር:: ጥንት ጀምሮ የጎንደር ነገሥታትና ባላባቶች እዚህ እየመጡ ነበር ዝሆንና አንበሳ ሌላም አውሬ የሚያድኑት! የእኛ ክርክር የነበረው መንግሥት አያዘውም ነው:: እነሱ ያኔ በደቡብ ኢትዮጵያ እንዳደረጉት በቀላድ እንዲተዳደር ነበር:: ያ ደግሞ በደቡብ ብዙ ችግር ያመጣ ነው:: በቀላድ እንዲተዳደር ያደረጉት ቆላና ደጋውን ለማለያየት ነበር::

ጥያቄ እና ለባላባቱ ከተሰጠ በኋላ ምን የተደረገ ለውጥ ነበር? መልስ ለባላባቱ ከተሰጠ በኋላማ ምርቱም አደገ:: በመኸር አንድ ኩንታል በሃያ እና በሃያ አምስት ነበር የሚሸጠው:: በሰቲት ሁመራ ሼል የሚባል ድርጅት ነበር:: በትንሹ ነበር የሚያስረክበው ልዑል ራስ አስራተ ካሳ ለምንድነው ጉልበታችሁን በከንቱ የምታፈሱት አሉን:: እንዲያውም ማሕበር አቋቁማችሁ ለልማት ብድር ብትጠይቁ መንግስት ገንዘብ ይፈቅድላችኋል አሉንና ማህበር አቋቋምን:: ጥያቄ ማህበራችሁን ማን ብላችሁ ሰየማችሁት? መልስ የሰቲት ሁመራ ሁለገብ የገበሬዎች ማህበር አልነው:: ማህበሩን አቋቁመን አዲስ አበባ መጥተን ለልማት ባንኩ አመልክትን ብድር አገኘን:: የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስትሮች ሳይቀሩ ወልቃይት ድረስ መጥተው አብረው እየሰሩና እያረሱ ብዙ ምርት ተሰበሰበ:: መንግስት ሕዝብ ነጋዴና ገበሬው ተጠቀመ:: በአንድ ዓመት ውስጥ አስራ ሁለት ሚሊዮን ብር ተገኘ:: ጥያቄ ምንድን ነበር የሚመረተው? መልስ ጥጥና ማሽላ በብዛት ይመረት ነበር:: ወዴትስ ነበር የሚላክ የነበረው? መልስ ጥጥና ማሽላ በብዛት ይመረት ነበር" ሲሉ ከዚያ በአስመራ በኩል በመርከብ ወደ አውሮፓ አገሮች ይላክ ነበር" ሲሉ መልሰዋል::

አቶ ነጋ ነወጠ፤ በጎንደር ዙሪያ አውራጃ የአርማጭሆ ባላባት ሲሆኑ በቆላው አገር ቀላድ አይጣልበትም በማለት ተቃውመው በርሃ ገብተዋል:: እኚህን ሰው የመንግሥት ወታደር ዘምቶ ሊያገኛቸው የማይችል በመሆኑ አጎታቸው ቢትወደድ አዳነ መኮንን ናቸው ሽምግለው ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ጋር ያስታረቋቸው:: እኚህ ሰው የአጤውን መንግሥት ድክመት አንድ ባንድ ዘርዝረው በመጻፍ ለሕዝብ ማድረሳቸውን በወቅቱ ተባባሪ ነበራችሁ ተብለው የታሰሩ ዛሬ አሜሪካን የሚገኙ ነግረውኛል::



አቶ ነጋ ነወጠ፤

በተለይ የአጼ ኃይለ ሥላሴን አስተዳደር በመንቀፍ በአቶ ነጋ ነወጠ፤ የተዘጋጀውን ጹሑፍ ረድታችኋል ወይም ተባብራችኋል በማለት ታስረናል:: ለምሳሌ አቶ ገብሩ ካሳ፤ አቶ ፀጋ በላይ፤አቶ ፍስሐ መኮንን፤አቶ ዘዋለ ዘገየ፤አቶ አክሉግ አስካል፤አቶ አዲሱ አበበ፤አቶ ገሪማ ታፈረና አቶ አንዳርጌ እጅጉና ስማቸውን የዘነጋሁት በአቶ ሰሎሞን ከድር የፀጥታ ሚኒስት ትዕዛዝ ከጎንደር ተይዘን አዲስ አበባ ተወስደን ታሰርን:: አንዳንዶቹ አዲስ አበባ የነበሩ ከዚያው ታሰሩ" ብለው ሲነግሩኝ እኔ "የታሰራችሁበት መንስኤው ምንድን ነበር? በማለት ስጠይቃቸው አቶ ወልደ ገብርኤል "እኛ ዋናው መንስኤው የጎንደር መሬት ቀላድ አይጣልበትም በማለት ነው:: የአጤ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር በጎንደር ሕዝብ ላይ የሚያደርገውን አፈና ብቻ ሳይሆን ዋናው ዓላማችን የአጤው አስተዳደር በተለይ ካቢኔአቸው መቀየር አለበት በሚል ዋና ዋና ምክንያት ዘርዝረን በመግለጻችን ነው:: ይህን ታሪካዊ ጹሑፍ በመላ ኢትዮጵያ ሌሊት እንዲበተን ተደርጓል" ሲሉ ነግረውኛል:: አቶ ወልደ ገብርኤል የነገሩኝ አዲስ አበባ ሕደው ከታሰሩት መካከል ዛሬ አሜሪካን ያሉ አቶ ፀጋ በላይ፤አቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌ፤አቶ አዲሱ አበበና አቶ አክሉግ አስካል፤ አቶ አንዳርጌ እጅጉ፤ ናቸው:: ለዚህ ምዕራፍ ማዳበሪያ ታሪኩን የነገሩኝም አቶ ሊቁ እጅጉ፤ አቶ ጫቅሌ ቁምነገሬና አቶ ኖራሁን ጫንያለው፤ አምሳ ለቃ (ደጃዝማች) አፈራ አዳነ ተመሳሳይ ታሪክ ነግረውኛል:: አቶ ፀጋ በላይ በወቅቱ ሲያደርጉት የነበረውን እጠር ባለ መልኩ ጽፈው ልከውልኛል:: እርሳቸው የቅስቀሳ ጹሑፍ እየጻፉ ለሕዝብ ያዳርሱ መሆናቸውን መገንዘብ ችያለሁ:: ከዚህ በታች ያለው የአቶ ፀጋ በላይ ጹሑፍ ነው::

## እንብበህ ለሚያነብ ስጠኝ!

"ከኤርትራ እስከ ወለጋ በሱዳን የሚዋሰነው መሬት ለሱዳን ተሰጠ! ኢትዮጵያውያን ሆይ! ዛሬ ኢትዮጵያ ሕዝቧ በርክቶ በቴክኖሎጅ የተፈለሰፈ መሣሪያ በእጅ እያለ መሬታችን እንዴት ለሱዳን ይሰጣል? ኢትዮጵያውያን ወገኔ አባቶቻችን ያሳለፉትን ዘመንና ታሪክ እናስታውስ:: ደጉ ንጉሠ ነገሥት አጤ ዮሐንስ አንገታቸውን የሰጡበትን ደንበሯን ጠብቆ ያቆየነን ሀገር ለባዕድ ስትሸጥ እንቅልፍ እንዴት እንተኛለን? ለሀገር ለዳር ደንበር ዝመት ተነስ! ተነስ ተነስ እንነሳ"

"የሚል እየጻፍኩ በጎንደር ጤና ጥበቃ ኮሌጅ በፋሲለደስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በከተማው በማስበተን በየመጠጥ ቤቱም ቅስቀሳ የሚያደርጉ ሰዎች በማዘጋጀት ከፍ ያለ ንቅናቄ ተጀመረ:: በኮሌጁ ውስጥ መረጃዎች ኖረው በኔ ላይ ከፍተኛ ክትትል ተደረገ፥ ለአለቃየም ለአቶ ጌታሁን አሰጉ በኔ ክትትል ስለሚያደርጉ ትብብር እንዲያደርግ ተገልጾለት ሥራ የሚመለከት መስሎ እኔን ይዞ ወደመካዝኖች መንገድ ጀመርን:: ዘወር ብሎ ተመልክቶ በሱዳን በተሰጠው መሬት ሕዝቡን የሚቀሰቅስ እሱ ነው ተብለሃል ልትያዝ ነው ተጠንቀቅ ሲል ገለጸለኝ:: ተመልሰን ወደቢሮአችን ገባን 16 ገጽ ለመለዮ ለባሹ ለማበተን የተጻፈ ነበር:: ከቢሮየ አውጥቼ ሌላ ቦታ አስቀመጥኩት:: በማግስቱ



እጀጠባብ ሞዴ ሱሪ ኩታ ለብሶ ነጋዴ መስሎ ከደረጃ ላይ ቁጭ ብሎ ስገባ ስወጣ ይመለከተኝ ነበር:: እኔ ወጥቼ ሳልመለስ ከቢሮዬ ገብቶ ይፈትሻል:: ነገር ግን ምንም ሳያገኝ ይቀራል:: ሁለት ቀን በዚህ ዓይነት ሞክሮ ሳያገኝ ቀረ:: በ3ኛው ቀን መኖሪያ ቤቴ በ2 መትረየስ በ6 ልዩ ልዩ ጠበንጃዎች የያዙ ወታደሮች ተከብቤ አድሬሮለሁ::

ከንጋቱ 12 ሰዓት ሲሆን በር ተንኳኳ ተነስ ታጠቅ የሚል ድምጽ ሰማሁ:: እኔም ልብሴን ለበስኩና በር ከፈትኩኝ:: ወዲያው እጅ ወደላይ ተባልኩኝ የታዘዝኩትን ፈፀምኩ:: ልጆቼንና ባለቤቴን ወደውጭ አስወጡአቸው:: ወደቤት ክርስቲያን የሚሄዱ ሰዎች ሁለቱን አላውቃቸውም 3ኛው ግን ፊታውራሪ ነጋሽ አሉላ በድንገት ይዘው እኔም አብረን ወደቤት ገባን:: እየጻፍኩ የምትበትነው ወረቀትም ልትበትን የምትጽፈውንም ወረቀት አምጣ አሉኝ:: የፃፍኩትም የበተንኩትም ወረቀት የለም:: የሚል መልስ ሰጠኋቸው:: እነሱም አልጋየን ፍርናሹን ትራሱን ሳይቀር እያገላበጡ ፈተሹ ሳጥን ከፈቱ ወረቀት አገኙ:: አይተው መልሰው ተውት::

አንዲት ማስታወሺያ ደብተር አገላብጠው አዩ እርሷን ወስዶ ወደ 1ኛ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰድኩ ከቀኑ 8 ሰዓት ድረስ እዚያ ቆየሁ:: ከዚያ ወደ ፖሊስ ማሰልጠኛ ት/ቤት ተወሰድኩ:: ብቻየን መሳሪያ የያዙ ፖሊስ ጠባቂ ተደርጎ (ከመኪና ማቆሚያ) ጋራጅ ተቀመጥኩ:: ምግብ የለም ማታ ከትልቅ ማርቸዲስ መኪና ላይ ውጣ ተባልኩ:: ለፍጥኝ እጄን አስረው ቁጭ እንዳልኩ ከስፖንዳው ጋር ጥለው አሰሩኝ መንቀሳቀስ አልችልም:: ከ3 ቀን በኋላ ምርመራ ተጀመረ:: ሻለቃ ሰሎሞን እባላለሁ ሲለኝ ሳየው ነጋዴ መስሎ መስሪያ ቤት ይመጣ የነበረው መሆኑን አረጋገጥኩ::

እውነቱን ብትነግረኝ ጥሩ ነው አለኝ:: የሰራሁት ካለ እነግርሃለሁ ያልሰራሁትን ደግሞ ሰራሁ ብዬ አልልም አልኩ:: ፖሊስ ተጠራ ውሰደው አለ:: ውጭ ስወጣ መልሰው አስ ስገባ በበሩ ተጠግቶ ቆይቶ በጥፊ መታኝ ወዲያው እጄን በጨርቅ ጠምጥሞ በፊቴ አሰረኝ:: 2ቱን እጄን ፈርቅቆ ጉልበቴን መሃል አስገባ አይኔን በሻሽ ተሸፍኖል የእንጨት ኳስ በአፌ ገብቷል በእግሬ መሀል ብረት አስገብተው ብረቱን ለሁለት ሲያነሱት ራሴ ወደታች እግሬ ወደላይ ሆኖ እግሬን ይቀጥቅጠዋል:: እያረፈ ይቀጠቅጠኛል: እጁን እየሰደደ ብብቴን ያያል:: ላበት የለውም ሲል ኮሉኔል በለጠ የተባለው በል አውርደው ፈረስ ገሱዶ ቢሞት እዳው የኛ ነው አለ::

በግርፋት ላይ እንዳለሁ ንገረን ስንልህ የምትነግረን ካለ በአንገትህ ሺቅብ ምልክት አሳየን የማትነግረን ከሆን በትክሻህ አሳየን ተባልኩ:: ትክሻየን እየነቀነቅሁ ወረድኩ በመሠረቱ በዚህ መሬት ምክንያት የተያዝነው 1ኛ እኔ ፀጋ በላይ 2ኛ አቶ ፍስሃ መኮንን 3ኛ አቶ አበበ አዲሱ 4ኛ አክሉግ አስካል 5ኛ አንድ ቆለኛ ስሙን አላውቀውም:: 6ኛ አበበ የተባለ የክቡር ቢትወደድ አዳነ ዘመድ ጎንደር አለ! እዚህ ጎንደር 3 ወር ሙሉ ከታሰርኩ በኋላ አዲስ አበባ ተወሰድኩኝ:: 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ ከባድ ወንጀል ምርመራ ውስጥ በግርፋት

ከተባቂዎች በኋላ በጎጂው ቢትወደድ አዳሬ መካነን ከጃንሆይ አቤቱታ አቅርበው በዋስ ይፈቱ ተባሉ:: ታሳሪዎቹ 25 ቀን 1965 ዓም በተፈታበት ወቅት መሬቱን በይዞታው እንዲቆይ ተፈረደ::

“አዲስ አበባ ተመልሼ በታሰርኩበት ወቅት የምንበላውና የምንጠጣው ሁሉም ይልኩልን የነበሩትን ማመስገን እወዳለሁ:: እንዲሁ አቶ በውጣለም ቢቶ ነው የመጣላችሁ እዮብ ሰርጎ ምናና አራት በበሚ ወር ይመጣልን ነበር:: እንደኛዋ ሴት ናት ስሟ አበታወቀችም ለብርስ 2.2 ዲሽ ቅሌት በራይ ዋጊ አስከንፌታ ድረስ ይልኩልን ነበር:: እነዚህ ሰዎች ለሀገራቸው ለወገናቸው የነሩ በመሆናቸው ውለታቸው ሊረሳ አይገባም:: ከዚህ በላይ በእኔና በሌሎች ኢትዮጵያውያን የደረሰብን ችግር ለአገራችሁ ዳር ድንበር ተቆርቆራችሁ በመሆናችን ነው:: እኛ ደግሞ መሬታችን ለሱዳን አይሰጥምብንም በማለታችን ነው:: እኛ የታሰርንበትን ታሪክ ያህ ሲሆን የዛሬው ትውልድ ለአገሩና ለዳር ድንበሩ ይቆረቆር ይሆን?

የአሁኑ ትውልድ ግን ሀገር ወዳን ምን እንደሆነ የሚያውቅ አልመሰለኝም:: ከበላ ከጠጣ መኪና መሬ ከወለደም ለአገር ደንታ የለውም:: ቢትወደድ አዳሬ ወልደ ሚካኤል “ቁሜ ሕይወቱ ኢትዮጵያዊ ነኝ፤ ሙቶም አጽሜ ኢትዮጵያዊ ነኝ” ያሉት አርጅታችውን ኢትዮጵያዊነታችውን እንዳይከዱ ለማሳሰብ የተጠቀሙበት ምክር ሲሆን እኔም ለተተኪው ትውልድ የምለው ቀደም ለሱዳን ሊሰጥ ታገዶ የነበረው መሬት በሕይወቱ እስካለሁ የኢትዮጵያ መሬት ነው:: ሙቶም አጽሜ የኢትዮጵያ መሬት መሆኑን ያምናል:: ስለዚህ የዛሬው ትውልድ የአባቶቹን መሬትና አንድነት ዳር ድንበሩን ማስጠበቅ እንዳለበት እመክራለሁ” ሲሉ ገልፀዋል::



አቶ ቢጋ በላይ



በሁመራ በኩል በአምዳይት ሱዳኖች ገፍተው ሲመጡ ሕዝቡን ልጅ ተድላ ወልደማርያም አስተባብረው ዘመቻ ሲጀምሩ የመንግሥት ወታደር ሲደርስ ሱዳኖች አፈገፈጉ:: ነገር ግን ሕዝቡን ያስተባበሩ ልጅ ተድላ ወልደ ማርያም ናቸው ብለው በአቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌ ሲነግሩኝ ሁመራ የነበረ ሰው ስለዚህ የሚያውቅ ካለ ብዬ ስጠይቅ አቶ ክንፈ ተሰፋዬ “ልጅ ነኝ ብቻ ልጅ ተድላ ወልደማርያም ሲያስተባብሩ አስታውሳለሁ” ሲሉ ነግረውኛል:: በወቅቱ አዲስ አበባ ከንጉሡ ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበራቸው ተብሎ የሚነገርላቸው የዛሬው ብፁዕ አቡነ መልከ ጸዴቅ “ጠቅለል ባለ መልኩ የጎንደርን መሬት ሕዝቡ ታግሎ አስቀርቷል:: እገሌና እገሌ ናቸው ብዬ ስም ጠቅሼ መናገር አልችልም ነገር ግን ሕዝቡ በየደረጃው ታግሎ መሬቱን ማስቀረቱን መመስከር እችላለሁ” ሲሉ ነግረውኛል::

ሱዳኖች በሁመራ በኩል ገፍተው ሲመጡ ሕዝቡ ከመለሳቸው በኋላ እንደገና ወደ አብደራፊ ፊታቸውን በማዞር የኢትዮጵያውያንን ልማት አውድመዋል:: ይህ በአብደራፊና በሁመራ የተደረገውን አጠር ባለ መልኩ አስር አለቃ አባይነህ መሸሻ ደግሞ እንዲህ ይላሉ:: ይህ ከዚህ በታች ያለውን ታሪክ የነገሩኝ አስር አለቃ አባይነህ መሸሻ ናቸው::

የአስር አለቃ አባይነህ መሸሻ፣ “ሱዳኖች በአብደራፊ በኩል የኢትዮጵያውያንን ላይ ጉዳት አደረሱ:: በተለይ የቤተ እስራኤላውያን ልማት ዘርፈው በመሄዳቸው አብደራፊ ነዋሪ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሱዳን ተሻግረው ብድር ለመመለስ ሲሉ ብዙ ልማት አጥፍተዋል:: ሕዝቡን አስተባብረው የዘመቱት አቶ ዋክሹም ነወጠ፣ አቶ ነጋ ነወጠ፣ የአስር አለቃ አሞኜ፣ አቶ ታፈረ ኃይሌ፣ አቶ አቦሃይ ጫኒያለው አቶ ዘቀለ ጀንበር፣ የሻለቃ በየነ ልጅ ስሙን የዘነጋሁት የመቶ አለቃ ሌሎችም ስማቸውን የዘነጋሁት ሱዳኖችን ደብድበው መልሰዋል:: ይህ ከሆነ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ፀጥታ አስከባሪ ወደ ሁመራ ረደም፣ ገላን ዘራፍ፣ አብደራፊ ሽመሊጋራ እስከ መተማ ድረስ ላከ:: ከተላኩት መካከል አንዱ እኔ ነኝ”::

“ሁመራ የገባነው መስከረም 19 ቀን 1959 ዓም ሲሆን ወዲያው እኛ ወደ አብደራፊ ተላክን:: ወዲያው 3ኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ጄኔራል ተሾመ እርገቱ ከአስመራ ጎንደር ከዚያም መተማ በሽመሊጋራ አድርገው አብደራፊ መጡና ሱዳንን በሉት ብለው ስላዘዙ መሀል ድረስ ገብተን ወናኛቸው:: ከዚህ ወዲህ በደንበር የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ ሠራዊት ተቀመጠ:: የተወሰኑ ሰቪል የመንግሥት ሰራተኞች ገዳሪፍ ድረስ ሕደው ከተወያዩ በኋላ በአካባቢው ሰላም ሆነ:: በጠቅላላው ከሁመራ እስከ መተማ ለሰፈረው ሰራዊት ሆነ የመንግሥት አስተዳደር አዛገፎ የጎንደር ክፍለ ሀገር ጠቅላይ ገዥ ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ሲሆኑ ፀጥታውን በሚመለከት ደግሞ የጎንደር ክፍለ ሀገር የፖሊስ ሰራዊት አዛዥ ጄኔራል ስዩም ገሰሰ እገዛ ስር ነበር”::

“እነዚህን ለም ቦታዎች ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ሲሰጥ ጉንብስ ቀና እያለ መሆኑን ሰምተናል:: ወደ ኋላ ልመለስና ሁመራ ስገባ በወቅቱ ከገላን ዘራፍ በግምት 200

ኪሎ ሜሬት ቅልፈው ሱዳን ድንበር ላይ የሚያለሙ የትግራይ ልጆች ነበሩ:: በተለይ አቶ ተስፋዬ አድዋ፤አቶ ተስፋዬ ሊንሳ፤ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ከሁመራ ባላባቶች ጋር ተስማምተው መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ሱዳንን ገርፈው የሰደዱ ሲሆኑ ልማታቸውን አስከብረው ኑረዋል:: እኔ እስከማውቀው ድረስ የወልቃይት ልጆች ለአገራቸው ያደረጉት ልማትና ድንበር ጥበቃ ሊያስመሰግናቸው ይገባል:: ስማቸውን የማስታውሰው ፊታውራሪ ሰረበ ለማ፤ አቶ ጌታቸው ይርጋ፤ አቶ አበሃ አብተው፤ መላከ ሰላም ሲሳይ አየልኝና ሌሎች ብዙ ጀግኖች ተዋግተው አገራቸውን አስከብረው ነበር::"

"ዛሬ እንሆ እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸውን በጥቂቱ የጠቀስኳቸው ግለሰቦችና የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ ተዋግቶ ያስቀረውን መሬት ለሱዳን ሊሰጡ ነው:: ለሚቀጥለው ትውልድ የምመከረው ነገር ቢኖር ከሁመራ እስከ ጋንቤላ 1600 ኪሎ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ታስቧል:: እኔ ዛሬ እድሜዬ ከ70 ዓመት በላይ ነኝ:: ስለ ሀገሬ ግን እንገበገባለሁ:: እበሳጫለሁ! ስለዚህ ዛሬ 20 ዓመት የሞላህ ወጣት አትርሳ አለብህ አደራ:: ቀደም የነበሩ አባቶችህ አንድ ሁነው ተባብረው ኢትዮጵያን አቆዩን እኛም በአቅማችን ተዋግተን አቆየን:: ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ሲሰጥብህ እንደ ቀድሞዎች አባቶቻችን "እብሚ ለሀገሬ" ብለው ተነስና አንድነትህ አስከብር አደራ እልሃለሁ" ሲሉ ገልጸውልኛል::

እንግቢያን በአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች ቀላድ አትጥሉብትም ሲባሉ ለሱዳን ሸጠዋል ይባላል:: እነዚህ አንዳንድ ግለሰቦች ከግል ጥቅማቸው ጋር አያይዘው በግዴለሽነት መሬቱን ለሱዳን ሊሰጡ በመታሰቡ የአካባቢው ሕዝብ የገጠሩ በሕይወቱ የከተማው በሥነ መንግሥት ተከራክሮ ያስቀረ መሆኑ ታሪክ የነገረን ሲሆን ዛሬም ይህ ተመሳሳይ ድርጊት በመፈጸም ላይ መሆኑን ማስገንዘብ እሻለሁ::

የአስር አለቃ አባይነህ መሸሻ!



## ምክንያት ሶስት

አቶ ዘውገ ፈንታ፤ "የኢትዮጵያን የሚያውቁት የደህንነትና የአገር ግዛት፣ የፖሊስ ጽፈት ቤት እንዲሁም ውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ባለሞያዎች ናቸው:: የተሳለውን ካርታ ርቀቱንና ርዝመቱን የሚያውቁት" በማለት በወቅቱ የገጸ ምድር ካርታ ድርጅት ሠዓሊው አስረድተውኛል:: በእርሳቸው አገላለጽ "አንድ እስክርቢቶ ጭረት ያረፈባት በጣም ብዙ ኪሎ ሜትር ስለሚሆን በትክክል መጠኑን ልነግርህ አልችልም:: ምክንያቱም የሀገር ጉዳይ ነው" ብለውኛል::

ግለሰቦች ይህን ካርታ በ250 ሺህ ብር ለሱዳን ሸጠዋል:: የሚባለውን ወሬ ደጋፊው ብዙ ነው:: የአቶ ዘውገ ፈንታን አባባል ሻለቃ ጌታቸው የሮም ወሬ ሳይሆን ትክክል ነው በማለት ከመጽሐፋቸው ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል መቶ አለቃ በቀለ ወ/ጊዮርጊስ፤ መሆናቸውን ገልጸው ነግረውኛል::: በገንዘብ ተሸጧል ከሚለው ላይ የሁሉም አንድ ሲሆን አቶ ዘውግ፤ ጄኔራል ነው ሲሉኝ ሻለቃ ጌታቸው የሮም ደግሞ መቶ አለቃ ነው አሉኝ:: የአቶ ዘውገ አባባል " ካርታውን ሰርተን እንደጨረስን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ስልክ ተደውሎ ካርታውን ለማንም እንዳይሰጥ በተለይ እገሌ እንዳይወስድ ምስጢር ነው ብለው አስጠነቀቁኝ" ሲሉ ነግረውኛል:: እኔ አቶ ዘውግን ከውጭ ጉዳይ ሚንስትር ስልክ ደውሎ ማን እንዳስጠነቀቃቸውና ለእገሌ አትስጥ ተብሎ የተነገራቸውን ስም ይንግሩኝ እንድሆን 3 ቀን በተለያዩ ጊዜ ጠይቄያቸው ከላይ ያሉትን መድገም ካልሆነ በቀር አስጠንቃቂውንም ሆነ እንዳይወስድ ስም ተጠርቶ የተነገራቸውን ስም እንዲነግሩኝ ብጠይቅ ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም:: ይህ በገንዘብ ተሸጧል የሚለውን ወሬ ሳይሆን ትክክል ነው ጎንደር ድረስ ተሰምቷል ሲሉ አቶ ወልደ ገብርኤል ደግመውኛል::

ሻለቃ ጌታቸው የሮም <u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 106-107 "ብወሎ ጠቅላይ ግዛት ደሴ ከተማ ተወለዱ:: የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም በተወለዱበት በደሴ ከተማና በኋላም አዲስ አበባ በመምጣት በከፍተኛ ነጥብ አጠናቀዋል:: በዚሁ መሠረት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ገብተው በመማር ላይ እንዳሉ በነበራቸው የወታደርነት ፍላጎትና ዝንባሌ የዩኒቨርስቲውን ትምህርታቸውን አቋርጠው በ1960 ዓም ሀረር ውስጥ በነበረው የጦር ሰራዊት አካዳሚ ት/ቤት ይገባሉ::"

"ከሀረር ጦር አካዳሚ በትምህርታቸው የላቀ ውጤት በማስመዝገብ በ1964 ዓም በክብር ተመርቀው የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ ያገኛሉ:: በትምህርታቸውና በአካል ብቃት እንቅስቃሴያቸው ከፍተኛነት ከተመረጡበት ወጣት መኮንኖች አንዱ በመሆን ወደ አርሚ አቪየሽን በረራ ሥራ ላይ እያሉ በ1966 ዓም በተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ ሣቢያ የመንግሥት ሥልጣን ለመቆጣጠር ብቻውን ወታደራዊ ቡድን ውስጥ ይገባሉ:: በዚሁ ቡድን ውስጥም እየሠሩ ሳለ በ1967 ሕዳር 14 ቀን ቀደም ብለው በእስር ላይ በነበሩበት